ገለኞቹ

ከሕሊና ማኅደር

ጅ
204

ከ ወ/ማርያም

ብ ል ጭ ታ

ከሕሊና ማኅደር

ቅንብር — በሊሊያን ኤችለር ዎትስን

ትርጒም — በመንግሥቱ ወ/ማርያም

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
፲፱፻፹፪

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
KURAZ PUBLISHING AGENCY

ስልክ / Tel. 11 27 19

ፖ. ሣ. ቁ. / P. O. Box 30933

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Addis Ababa
Ethiopia

መብቱ፡ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

የሽፋን ሥዕል—ሉቃስ አማረ

ለባለቤቴ

ለወርቅነሽ ዱባ ጂማ

እያንዳንዱ ትውልድ፡ ዘመናት ባወረሱት ሰፊ ሀብት እየተገለገለ ይደሰታል ። ያንን ሰፊ ሀብትም በአዲስ ዕውቀት እያዳበረ ለመጪው ትውልድ ያስተላልፋል ።

ቶማስ ማኮሊ.

204

ማውጫ ገጽ

ስለ አዘጋጅዋ - - - - - - - - - 7
መግቢያ - - - - - - - - - - 8

ክፍል አንድ

ደስታና እርካታ - - - - - - - - 11
ጆን ባሮውስ - - - - - - - - 14
ቤራን ዎልፍ - - - - - - - - 22
ዊሊያም ላዮን ፌሊፕስ - - - - - - 27
ፍሬድሪክ ሉሚስ - - - - - - - 31

ክፍል ሁለት

ወኔና ጀብዱ - - - - - - - - 41
ፖል ሃሚልተን ሄይን - - - - - - 44
ዊልያም ኧርነስት ሄንሊ - - - - - 50
ሐሮልድ ራስል - - - - - - - 56
ዴቪድ ግሬይሰን - - - - - - 64
ሜሪ ሮበርትስ ራይንሃርት - - - - 72
ሮበርት ፋልከን ስኮት - - - - - 76

ክፍል ሦስት

ጥረትና ውጤታማነት - - - - - 81
ጆውኩይን ሚለር - - - - - - - 85
አርኖልድ ቤነት - - - - - - - 91

ኤድዋርድ ሮውላንድ ሲል - - - - - - 97
ኤ. ጇ. ክሮኒን - - - - - - - 102

ክፍል አራት

ሥነ ምግባርና ስብዕና - - - - - 109
ዊሊያም ሼክስፒር - - - - - - - 113
ጀምስ ሌን አለን - - - - - - - 117
ሂጶቅራጥስ - - - - - - - - 123

ክፍል አምስት

ፍቅርና ማኅበራዊ ኑሮ - - - - - - 129
ኤልሳቤጥ ባሬት ብራውኒንግ - - - - 132
ጆን ሃዋርድ ፔይን - - - - - - 138
ሳም ዋልተር ፎስ - - - - - - - 144

ክፍል ስድስት

እርጅናና የጉዞ ፍጻሜ - - - - - 153
ማርከስ ቱሊዩስ ሲሰሮ - - - - - 158
ሰር ዊሊያም መሎክ - - - - - - 163
ጀምስ ጐርዶን ጊልኪ - - - - - - 170
ሄንሪ ዎድስዎርዝ ሎንግፌሎ - - - 176

ስለ አዘጋጅዋ

ሲሊያን ኤይችለር ዎትሰን ሰዎች ራሳቸውን በራሳቸው መርዳት እንዲችሉ በማበረታታት ሰፊ ልምድ ያካበተች ዕውቅ ጸሐፊ ናት ። በማኅበራዊ ሕይወት ላይ ከሚያተኩሩና ሥራዎቻቸው በስፋት ከሚጠቀሱላቸው ጸሐፊዎች መካከል አንዷ ስትሆን ፣ «የሥነ ምግባር መመሪያ» እና «የሰው ልጅ ባህሎች» የተሰኙትን ተወዳጅ መጻሕፍትንና ሌሎች ሥነ—ምግባራዊ ጭብጦች ላይ የተመሠረቱ ቀስቃሽ ሥራዎችን አበርክታለች ።

«ብልጭታ ከሕሊና ማኅደር» የተሰኘው መጽሐፍዋ ለዓመታት ጥናት ያካሔደችበት የመጨረሻ ገጸ በረከቷ ነው ።

መንግሥቱ ወ/ማርያም

መግቢያ

እኛ የዘመኑ ትውልድ የቆምነው የብዙ ዘመናት ትውልድ ቀስ በቀስ ገንብተው ባቆዩልን ታላቅ የሥልጣኔ ምኩራብ ላይ ነው ። የትናንት አባቶቻችን ራሳቸውንና ዓለማቸውን ለማሻሻል ያደረጓቸው ጥረቶችና የጨበጧቸው ውጤቶች ፤ የሕልሞቻቸውና የውሳኔዎቻቸው ፣ የሞትና ሽረት ትግሎቻቸው ፣ የውብ ሥነ ጽሑፎቻቸውና የቅርሳ ቅርሶቻቸው ሁሉ ወራሾች ነን ።

«ብልጭታ ከሕሊና ማኅደር» ከበርካታ ቀስቃሽ የሰው ልጅ ጽሑፎች መካከል ጥቂቱን ይዞልን ቀርቧል ።......ሥራዎቹ ዓላማን የተመረኮዙ ፣ ጠቃሚና አመራማሪ ናቸው ።......ጥንታዊ ይሁኑ ዘመናዊ ፣ ጥልቅ ይሁኑ ግልጽ ፣ ሁሉም ስለሚገጥሙን ጭንቀቶች ፣ ግጭቶችና የሕይወት ውጣ ውረዶች ያወሳሉ ። ሁሉም ሊደርስብን ስለሚችሉ ፣ አንዳንድ ፈተናዎች ምላሽ ለመስጠት ይሞክራሉ ።

«አንድ ሰው ፣ አንድ ጥሩ መጽሐፍ ለማበርከት በአንድ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ከተካበቱለት ጽሑፎች ከፊሉን እንኳ ማገላበጥ ይኖርበታል» ሲል ሳሙኤል ጆንሰን እንደ ጠቆመው ሁሉ ፣ «ብልጭታ

ከሕሊና ማኅደር»ን ለማቀናበርም አያሌ ቤተ መጻሕፍትን መጐብኘትና በሺህ የሚቆጠሩ መጻሕፍትን ማንበብ አስፈልጓል ።

እንዲህ የመሰለ ሥራ ሁሉንም አንባቢ ሊያረካ አይችል ይሆናል ። ቃዲያ ፡ ለሁሉም የየፍላጐቱን ማቀናበር አዳጋች መሆኑ አያጠያይቅምና አንባቢ ደካማ ጐኑን ከዚህ አንጻር እንዲመለከተው የአደራ ድርሻ ይጣልበታል ።

«ብልጭታ ከሕሊና ማኅደር» በአቅራቢያ ተቀምጦ በተፈለገ ጊዜ የሚሳብ ፡ ዛሬም ሆነ ነገ ቀንጨብጨብ የሚደረግ እንጂ ፡ በአንዴ ተነብቦ ገሸሽ የሚደረግ መጽሐፍ አይደሎም ። ለሰዓታትም ሆነ ለዓመታት የሚያገለግል ፡ እንደ መልካም ባልንጀራ ተዘውትሮ የሚጐበኝ ፡ የማይነጥፍ የሥነ ምግባር መርሕና የርካታ ምንጭ ነው ።

መጽሐፉን በማቀናበር የተደሰትኩትን ያህል አንባቢም እንደሚደሰትልኝ ከልብ እየተማመንኩ ፡ «ለመሰብሰብ የቻልኩት ከተበብ አዝመራ ጥቂት ፍሬዎችን ፡ በስፋቱና በጥልቀቱ ወሰን ከሌለው የእውነታ ውቅያኖስ ጥቂት ጠብታዎችን ብቻ ነው» በሚለው የማርቲን ሉተር አባባል እደመድማለሁ ።

ሊሊያን ኤልችለር ዎትስን

☆ ☆ ☆

በሳል አባባልን ከቶ ማን ቸል ይላል?
ሕሊናን ሰርስሮ ያስራል ፡ ያስደምማል ።

ወይ. ሠርያ ወደ. አካል ከደ.ም ተዋሕዶ
ሰውን ያስመስላል ጉርፍ ያስተኛው ስርዶ ።

ራሊ.ፕ ጀ.ምስ ባይ.ሲ

☆ ☆ ☆

የሰው ልጆች ደ.ስታና ጥበብ የሚከማቹት በመ ጻሕፍት ውስጥ ነው ።...... ምንጊዜም እያንጸባረቁ ፍሬዎቻቸውን በማስራጨት ለዘመናት አያሌ ሐሳቦ ችንና ተግባራትን ያመነጫሉ ።

ፍራንሲ.ስ ቤከን

☆ ☆ ☆

ክፍል አንድ

ደስታና እርካታ

«ብዙ ሰዎች የሚደሰቱት ራሳቸውን ለደስተኝነት ባዘጋጁት መጠን ነው»

አብርሃም ሊንከን

ሰዎች ለዘመናት የደስታን ምንነትና የምትገኝ በትን ጥበብ ለመግለጽ ሲጥሩ ኖረዋል ። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ጸሕፍት እሌፍ አእላፍ ቃላትን አስፍረ ዋል ። የየዘመናቱ ባለቅኔዎችና ቄሶች ፡ ፈላስፎችና ሳይንቲስቶች ፡ ምሁሮች ፡ ...... ስር ፊሊፕ ጊብስ ፡ «የሰው ልጅ ዘላለማዊ ጥረት» ሲል የሠየመውን የደስተኝነትንና የአመርቂ ሕይወትን መንገድ ለመ ተለም ብዙ ሞክረዋል ።

ግን ደስታ ምንድናት? ለተለያዩ ሰዎች የተለያዩ ትርጉሞች እንደሚኖራት ግልጽ ነው ። ከጥንት ጊዜ ጀምሮም ሰዎች ደስታን በተለያዩ መንገዶች ሲፈ ልጓትና ሲያገኟት ቆይተዋል — በሥራ ላይ ፣ በቤተ ሰብ ዙሪያ ፡ በጓደኛ ልብ ውስጥ ......ወዘተ ።

ሆኖም የየንዳንዱ ዘመን ፈላስፎች የተስማሙ በት አንድ ነጥብ አለ ። ይኸውም...... «እውነተኛ ደስታ የምትመነጨው ስለ ሕይወት ከሚኖረን ግን ዛቤና ከየራሳችን ውስጣዊ ምንነት ነው» የሚለው ቱም ነገር ሲሆን ፡ ስለ ደስታ ከሠፈሩት በሚሊዮን ከሚቆጠሩ ሐሳቦች ጥንታዊዉና ጊዜ የማይሽረው እውነታም ይኸው ነው ። የደስተኝነት መንፈስ በደማችን ካልሰረፀ ምንም ዐይነት የሀብት ክምችትና የመዝናኛ ሥፍራ ደስታን ሊያስገኝልን አይችልም ።

ከጥንት ጊዜ ጀምሮ እስካለንበት ዘመን ድረስ ዕውቅ ፈላስፎች ስለ ደስታ ከሰነዘሯቸው አባባሎች ምርጥ ምርጡን እነሆ ።

☆ ☆ ☆

ጆን ባሮውስ

«የደስታ ምንጩ ሥራ ነው ።»

ባለቅኔው ጆን ባሮውስ ፡ መስኮቱ ላይ ቆም ብሎ ሲቃኝ አንድ ጐረቤቱ በቤቱ ጥግ ሲያልፍ ተመለከተ ። ሰውዬው በደስታና በርካታ መንፈስ ሳይሆን በትካዜና በጭንቀት አቀርቅሮ ነበር የሚንገላወደው ።

ለዚህ ሁኔታው ያበቃው ምን እንደሆነ ጆን ባሮውስ ተረዳለት ። ሰውዬው የሚወደውና የሚመስጠው ፡ ጊዜውን ትርጉምና አቅጣጫ የሚሰጥለት ምንም ዐይነት ሥራ አልነበረውም ።

«ሥራ ያጣ ሰው ለሥቃይ የተዳረገ ነው» ሲል ባሮውስ ማሰላሰል ያዘ ። የደመቀ የወፎች ኅብረ ዝማሬን እያዳመጠና ለስላሳ የነፋስ ሽውታ እየተመገበ ባሮውስ በጉዳዩ ላይ ሲያሰብበት ቆየ ።

የሥራን ክቡርነትና ሕይወት አዳሽነት ከእርሱ ወዲያ የተገነዘበ አልነበረም ። በአንድ ወቅት እርሱው ራሱ በሥራ እጦት ለሥቃይ ከተዳረጉት ምስኪኖች መኻል አንዱ አልነበር? ያኔ ሕይወት ጣዕሟን

ነፍ.ጋዋለች ፣ ባዶና ግትር ሆናባታለች ። ያኔ መብላ ትም ሆነ መተኛት ፣ መጫወትም ሆነ መግባባት ተስኖት ነበር ።

ሥራ ነፍስ ዘራለት — እርሻ ላይ የመማሰን ፣ የማረስና የመጐልጐል ፣ የመዝራትና የመትከል ፣ የማረምና የመኰትኰት ...... ተግባራት ፣ ለም አፈር ጨብጦ በጣቶቹ መኻል የመናኘት ሥራ እርሱነቱን ከሚኖርባት ዓለም ጋር እንዳዋሐደለት በሚገባ ያው ቀዋል ።

የጨበጠው እርፍ ፣ እንደሚያርሰው መሬት ፣ እርሱነቱንም አለስልሶለታል ። ያን ምሬቱንና መሰ ላቹቱን ፈነቃቅሎለታል ። እንደ ኩሬ ውሃ ተኪትሮ በት የነበረ መንፈሱን እንዲንኳለልለት ረድቶታል ። ሥራ ሕይወቱን አልምልሞለታል ።

በጸደይ ወራት ወንዞች ሲጠሩና ሲፍለቀለቁ የእርሱም ልብ ይፍለቀለቃል ። አዕዋፍ ከየተሰደዱ በት ተመልሰው ሲጠራሩና በኅብረት ሲዘምሩ ፣ እር ሱም በመንፈስ ያጅባቸዋል ። አሻግሮ የሚታኞቸው ሸንተረሮች ውበትን ተላብሰው ሲመለከት ፣ እርሱም ሞገሳቸውን ይላበሳል ። የዕድሜ ልክ ሞያውን እን ዲተቀዳጀ ልብ ያለውም ያኔ ነበር — በግብርና ከተ ሠማራ በኋላ ።

ጆን ባሮውስ ፣ ከመስኮቱ ሥለስ ብሎ እያዘገመ ወደ ጠረጴዛው ኼመራ ። ከዚያ በኋላም ብዕሩን አሹሎ በተከታታይ ስለ አዕዋፍ ፣ ስለ አበቦችና ስለ ገጠር ሕይወት ያጐረፋቸው ድርሰቶቹ ዓለም አቀፍ ዝናን

አተረፉለት ። ግጥሞቹና መጣጥፎቹ ደስታንና እፎ
ይታን አከሉለት ።

ደስታ ፡ እንደ ሕልም በግ እልም የሚትልና ዘወ
ትር ከአጠገብ የምትገኝ መሆኗን ለሰዎች ለማስረ
ዳት ምንኛ ተጣጣረ! ግን ፡ በዙሪያው የነበሩት ሁሉ
ተስፋ በሚያስቆርጥ መንገድ እየዋተቱ፡ ሕይወታ
ቸውን ሲከትሩት መመልከቱ አላስችል ብሎት የደ
ስታ ምንጩ ሥራ ፡ መንፈስን የሚመስጥ ሥራ መሆ
ኑን ለማስገንዘብ ቆርጦ ተነሣ ።

«ከማንኛውም ሁሉ በላቀ ሁኔታ ደስታን የሚ
ለግሥ አንድ ነገር አለ ፤ ምን ይሆን?...... በጣም ቀላ
ልና በእጅ የሚገኝ ነው ። ይህን ምስጢር ለጨረታ
ላቀርበው ብችል ምን ያህል ሰው በጐረፈ ! ዋጋውም
ምንኛ በናረ! ብልሆች ብቻ ናቸው ምንነቱን የሚያ
ውቁት ። አንዳንዶቹ ጤንነት ፡ ወይም ገንዘብ ፡ ወይም
ባልንጀራ ፡ ወይም ይህን ወይ ያን ሀብት ይሉ ይሆ
ናል ። ግን ፡ እነዚህ ሁሉ ተሟልተው ደስታ አትኖ
ርም ። ዝናና ሥልጣንም ደስታን አያስገኙም ። ጤን
ነት ፡ ገንዘብ ፡ ባልንጀራ ፡ የሞቀ ቤት ...... ሁሉም
አስፈላጊ ቢሆኑም ደስታን ፡አያጐናጽፉምና ከእነዚህ
ሁሉ የሚልቅ አንድ ነገር አለ ። ያ ነገር — ምን
ይሆን? ሕመምተኛው ጤና ፡ ደሀው ሀብት ፡ ምሁሩ
ዕውቀት ፡ እልቅና የሚሻው ሥልጣን ፡ የደከመው
ደግሞ ዕረፍት ይል ይሆናል» በማለት ማስተማሩን
ጀመረ ።

«በሕሊናዬ ከያዝኩት ምስጢር ውጭ ለዘለቄታ
ደስታ የሚያበቃ ምንም ነገር የለም ። በእርግጥ

ያለምግብና መጠጥ ፣ ያለልብስና መጠለያ የተሟላ ደስታ አይኖርም ። ታዲያ እነዚህም ተሟልተው ደስታን መሻት አይቀር ! ተቀዳሚው የደስታ ምንጭ 'አርይታ ያገኘ አዕምሮ ነው'ም ይባላል ። ግን እርይታ ያገኘ አዕምሮ ምን ይሆን?

«ዐይነተኛውን የደስታ ምንጭ ምንነት አሁን ስነግራችሁ ቅር ትሰኙ ይሆናል ። የተለመደ ፣ በቅርብ ያለ ፣ ብዙ ሰዎች በእጃቸው ያስገቡት ፣ ግን አስደሳችነቱን ያልተገነዘቡት ጉዳይ ነው ። ወይ ከአቅማቸው በላይ ሆኖባቸዋል ፣ ወይ የሚጥማቸው ሆኖ አላገኙትም ። ጅረት የሚሻው ዋነኛው ነገር ምንድን ነው? ሳያቋርጥ መንኳለሉን ይሆናል ። ከተከተረ ጣጣ ይወልዳል ። ሰውም እንዲሁ የማያቋርጥ እንቅስቃሴን ይሻል — የአካል ፣ የመንፈስ ፣ የጭንቅላት ። ስለዚህ የደስታ ምንጩ ሥራ ፣ የሚጥም ሥራ ነው ። ሰዎች ሁሉ ከሥራ ቢታገዱ ዓለማችን ምንኛ የሥቃይ ቋት በሆነች!

«ሥራ የደስታ ምንጭ መሆኑን ፣ በእርሱም በመጠመዳቸው ሕልውናቸውን ከመገዝገዝ መቆጠባቸውን የሚገነዘቡ በጣም ጥቂቶች ናቸው ። ደስታ የምትቀርበው አጥብቀው የሚሿትን ፣ ስለርሷ የሚያብጠለጥሉትን አይደለም ። በፍለጋ የሚደረስባት ዕቃም አይደለችም — አመች ሁኔታን በመፍጠር እንጂ ። መከተልን እንጂ መምራትን አታውቅም ። ፊት ፣ ፊት ካለችም እርሷን ለመቅደም መሞከሩ አይበጅም ።

«በሙሉ ልብ ተመስጦ ፡ ያለ የሌለ ኃይሉን በሚጥመው ሥራ ላይ የሚያውል ሰው ምንኛ የታደለ ነው!» እያለ የፍልስፍና አቅጣጫውን ጠቆመ ።

ከራሱ ሕይወት አመርቂነት በመነሣት ነበር ጆን ባሮውስ ይህን የጻፈው ። «ወፎችና ባለቅኔዎች »፡ «እንበጣዎችና የዱር ማር»፡ «ወቅቶችና ምልክቶቻቸው»፡ «የተፈጥሮ አካሔድ »...... ከመጻሕፍቱ ጥቂቶቹ ሲሆኑ ስለ አዕዋፍ ፡ ስለ ዕፀዋትና ስለ አራዊት የደረሳቸው መጣጥፎቹ በጣም ተወዳጅነትን ስላተረፉለት ፡ ታዋቂውን ምሁር ሄንሪ ዴቪድ ቶሮን ለመተካት እንደበቃ ይወሳለታል ።

መልካም ሕይወት እንዳሳለፉ እንደ ሌሎች እያሌ ሰዎች ፡ ባሮውስም በእስተርጅናው ፍልስፍናውን ከሌሎች ጋር ለመካፈልና የደስታ ምስጢሩንም ለማስተላለፍ ወስኖ «ተንቀሳቀሱ!» ሲል አበረታታ ። «ሕይወታችሁን አትክተሩት!» ሲል አስተማረ ።

ለሕይወት አስፈላጊዎቹ ቁም ነገሮች ሥራ ፡ ፍቅርና ተስፋ ናቸው ።

ጆሴፍ ኤድሰን

☆ ☆ ☆

ከልብህ ከተማማርህ ድርሻህ አያመልጥህም ። ቀላል ይሁን ከባድ ፣ ማሽላ መዝራት ይሁን ታሪክ መመዝገብ ፣ ሥራህ ትክክለኛና ከስሜትህ የመነጨ ከሆነ ግፋበት ። ለሕዋሳትህም ሆነ ለአዕምሮህ ርካታን ይለግስሃል ። ለድል አድራጊነት የተፈጠርክ ነህና በተደጋጋሚ ስላልተሳካልህ አትዘናጋ ። ለጥሩ ተግባር ሽልማቱ ውጤቱን ማየቱ ነው ።

ራልፍ ዋልዶ ኢመርሰን

☆ ☆ ☆

ደስታ የምትንጸባረቀው ፣ ባአመዛኙ ከተጨባጭ ተግባር ነው ። ደስታ ከምኞትና ከትዝታ ብቻ ትገኛለች ብሎ መገመት ከስሕተት ላይ ይጥላል ። እንዲያ መገመትማ ውብትን ለመብላት እንደ መጓጓት ይቆጠራል ። ደስታ ሰዎች በሥራ ተጠምደው ማየትን ትወዳለች ። ላብን ፣ ድካምን ፣ መሥዋዕትነትን ታፈቅራለች ። የምትገኘውም በተንጣለለና ባሸበረቀ አዳራሽ ውስጥ ሳይሆን በማሳዎች ላይ ፣ በፋብሪካዎች አካባቢ ፣ ቅልጥፍናን በሚያንጸባርቁ ጠረጴዛዎች ዙሪያ ስታንዣብብ ነው ። በጨዋታ ተውጦ እርሱነቱን በዘነጋ ሕፃን እናት ላይም ቂጢጥ ብላ ትታያለች ። ከሚመስጥ ተግባሩ ቀና ብሎ ለሚፈልጋት ሰውም ፍንትው ትልለታለች ። ግን ተግባሩን ዘንግቶ ለረጅም ጊዜ ትክ ብሎ ከሚመለከታት ሰው ቀስ በቀስ ትሠወራለች ።

የአካል እንቅስቃሴን የሚጠይቅ ከባድ ያለ ተግባር ጠቃሚ ጐን አለው ። በስመመን ኒማሽለብ

ያድናል ። ከአካፋዩ ጋር ሳጐነብስ ፡ አጐንብሽ ስሰ ቀስቅ ፡ ስቅስቂ ሳነሣ ፡ እንሥቼ ስገለብጥ ...... እንዲያ ያለውን እንቅስቃሴዬን ሳላዛባ ፡ ጊዜዬን ጠብቄ ስደ ጋግም በሐሳብ ከመዋጥ አመልጣለሁ ።

ታዲያ አንዳንዴ ፡ ከረፋዱ ላይ ፡ ቀና ስል አካ ባቢዩ ፈክቶ ይታየኛል ። ልዩ ትርጉምና ውበት ኢነብበትና የተሟላ እርይታና ልዩ ደስታ ይሰማኛል ።

ዴቪድ ግሬይሰን

☆ ☆ ☆

መቀመጥ መቆመጥ መሆኑን ከመገንዘብ ጥበብ እን ደምትመነጭ ሁሉ መልካም ሕይወትም ከሥራ ፡ ከፍቅርና ከዕቅ ትፈልቃለች ።

ኤልበርት ሃባርድ

☆ ☆ ☆

በየማለዳው ከመኝታ ዬ ስነሣ ገጼን በፈገግታ አብርቼ እያንዳንዷን ዕለት በሞቀ ሰላምታ በመቀበል ፡ ዓላ ማና ግቤን በጥሞና በማስተዋል ፡ ልቤን በፍቅር ፡ በጨዋነት ፡ በሩኅሩኅነትና በትሕትና ሞልቼ ተግባ ሬን በቅንነት በማከናወን ፡ ውሎዬ የማታ ማታ የማ ለግሰኝን ርካታ በጉጉት በመጠባበቅ ፡...... እንዲህ

በመሰለው ሁኔታ ነው ዕድሜዬን ለመግፋት እም ሻው ።

ቶማስ ዴከር

☆ ☆ ☆

መከናወን ያለበት ተግባር በየዕለቱ ከፊት ለፊታችን ተደቅኖ በማግኘታችን ደስ ሊለን ይገባል ። ወደድንም ጠላንም ፡ በመታዘዛችንና የታዘዝነውንም በመፈጸማችን ትዕግሥትን ፡ ብስለትን ፡ ታታሪነትን ፡ ቁራጥነትንና ሰነፎች ጭራሽ የማያውቋቸውን ሌሎችንም አያሌ ጸጋዎች እንደምናካብት ልብ እንበል ።

ቻርለስ ኪንግስሊ

☆ ☆ ☆

ቤራን ምልፍ

«ደስታን ለማግኘት ፡ ከራሳችን ወጣ ብለን እንመ ልከት ።»

ከራሱ ከቤራን ባስተቀር በክፍሉ ውስጥ ማንም አልነበረም ። ነገር ግን ፡ በሰው እንደ ተሞላ ሁሉ ክፍሉ ሁካታ ሠፍኖበት ቤራን ግራ ተጋብቶ ይቁነ ጠነጣል ።

«እባክዎ ይርዱኝ ...... ምን ዋጋ አለው!...... ራሴን መግደሌ ነው!.....» ይለዋል አንዱ ። «ብቸኝ ነት ያጠቃኛል ፡ ዶክተር!..... ጓደኛ ለማፍራት ጊዜ አጣሁ! .....» ይለዋል ሌላው ። አንዱ ደግሞ ፡ «ሥራዬ አንገሸግሾኛል! .....» በማለት ምሬቱን ያኘርጉደጉደዋል ።

ይህን የመሳሰሉ የዋይታ ድምፆች በዙሪያው ያስተጋባሉ ። ቤራን ሠላሳኛ ዓመቱን ገና መዝለሉ ነበር ። ታዲያ በዕድሜው ገና ለጋ ቢሆንም ፡ በአዕ ምሮ ሐኪምነቱ የሌሎችን ሥቃይ አዘውትሮ ይካ ፈል ነበርና እርጅና እየተጫጫነው መጥቷል ። የሕ ይወት ምሬት ስለሚያንገሸግሻቸውና ጭፍን ፍርሃት ስለሚያርበደብዳቸው ፡ እየተከዙና እየተቅበዘበዙ ርዳታውን ሲሹ እርሱ ዘንድ ስለሚጐርፉት የአዕምሮ

ሕሙማን ዘወትር ያሰላስላል ። በመጨረሻም ከአንድ መደምደሚያ ላይ ደረሰ ።

ይኸውም ፡ ሰዎች የጋራ የሆነ አንድ ዐይነት ዝንባሌ እንዳላቸውና ያም ዝንባሌያቸው ራስ ወዳድነት እንደሆነ መገንዘቡ ነበር ። አንዳንድ ሰዎች ደስታ የምትሸሻቸው ከራሳቸው ውጭ ማየት ስለሚሳናቸውና ስለ ሌሎች ደንታ ቢስ ሆነው ስለ ራሳቸው ብቻ ስለሚያብጠለጥሉ ፡ አንዳንዶቹ ሊያገኙ የማይችሉትን ስለሚመኙ ፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ሌላን ለመምሰል ስለሚዋትቱ ፡ ራሳቸውን ለመከራ ይዳርጋሉ ከሚሉ ቁልፍ ሐሳቦች ላይ ትኩረቱ ዐረፈ ።

ስለዚህ ፡ ሰዎች ከራሳቸው ወጣ በማለት የማኅበራዊ ሕይወት ተቋዳሽ ሆነው ለመደሰትና ሌሎችንም ለማስደሰት ጥረት እንዲያደርጉ ለመገፋፋት ሲል አንዲት ወረቀት ብድግ አደረገ ። ከበስተአናቷም «ደስታ ምንድን ናት?» የሚሉ ሦስት ቃላትን አሰፈረ ። ዐይኖቹን ወደ እነዚያ ቃላት እየወረወረ መልሱን በሕሊናው ሲያጠነጥን ቆይቶ ድንቀፍ ሳያደርገው የሚከተለውን መልእክት አስቀመጠ ።

«ደስታን እንደ ተቀበረ ማውሮ ወርቅ እያለሙ እርሷን በተአምር ለማግኘት መቅበዝበዙ አያዋጣም ። ደስታ የምትሰፍነው ፍሬያማ ሕይወት በሚመሩ ሰዎች ልብ ውስጥ ነው ። እንደነዚህ ያሉትም ሰዎች አተኩሮ ላስተዋላቸው እንጨት ሲልጉ ፡ ሲጽፉ ፡ ሲያስተምሩ ፡ ሲኮትኩቱ ፡ ...... ነው የሚገኙት ። አዝራር እንደ ጠፋባቸው ሁሉ በየሥርቻው ሲንጐዳጐዱ አይታዩም ።

«የግል ፍላጎቱን ለማርካት ሲል ብቻውን የሚራወጥ ሰው በጠባብ አመለካከቱ የሌሎችንም ብሩህ መንፈስ ስለሚመርዝ አይዞህ ባይ የለውም። በዚህም ምክንያት የማኅበራዊ ሕይወት ጸጋን ተገፍፎ እርቃኑን ይቀርና ፣ ውሎ አድሮ ፣ ራሱን ከመከራ አዘቅት ውስጥ ያገኘዋል ።

«ለራስ ብቻ መኖር ምንጊዜም ራስን ለአደገኛ ወጥመድ መዳረግ ፣ የገዛ ሕይወትን አቅጣጫ የሞት ያህል ማጨለም መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ።

«በማኅበራዊ እንቅስቃሴ መሳተፍ ሥነ-ልቦናዊ ጠቀሜታ አለው ፤ የኅብረተሰብን ሕይወት ከማገም ቱም በላይ ፣ ራስንም ከሌሎች ጐን በልበ—ሙሉነት ለማሰለፍ ይረዳልና ።

«እስቲ ለማግኘት የምትመኘውን ሁሉ በአዕምሮህ ደርድር ። ከዚያም 'እነዚህን በእጄ ካስገባሁ ሌላው ቢቀርስ?' በል ። ወይም 'ግላዊነቴና የበታችነት ስሜቴ እንዳገኝ ከሚያስገድዱኝ ነገሮች ከፊሉን እንኳ አላሟላሁም?' ብለህ ራስህን ጠይቅ ።

«ፍላጎትህን መግታት ካልቻልክ ፣ በዝናና በሥልጣን ከማንም በላይ ልቀህ ለመታየት በጭፍን የሚያንደረድርህን አዕምሮህን መግዛት ካቃተህ ፣ ምኞትህ ሁሉ የውሃ ሽታ ሆኖ በደስታ ፋንታ ሐዘንንና ጸጸትን እንዳትገበይ!......

«እውነተኛው ደስተኛ ሰው ለሌሎችም ደስታን እያመነጨ በተስፋ የሚራመድ ሰው ነው ። ተስፋ

ደግሞ በሁሉም ሰው ልብ የምታበራ ፡ ከማኅበራዊ ግዴታ ፡ ከማኅበራዊ ብርታትና ዓላማ ጋር የተቆራኘች ናትና በተጨባጭ የማኅበራዊ ሕይወት ተሳትፎ መኮትኮትና መለምለም አለባት ። ወደ አስደሳች ሕይወት የሚያመራው ዋናው ጉዳዳናም ይኸው ነው ። ይኸው ብቻ ነው ፡ የአመርቂ ሕይወት መሠረቱ ።»

የዶ/ር ምልፍ የሥራ ዘመን ማጠሩ ያሳዝናል ። የሞተው በሠላሳ አምስት ዓመቱ ሲሆን ፡ በዚያች ባጭር ጊዜ ቆይታው ብዙ ሰዎች ማንነታቸውን እንዲገነዘቡና ደስተኛ እንዲሆኑ ረድቷል ።

ከማኅበራዊ ኑሮ ከተፈናቀሉ ሰዎች ጋር በመዋል ካካባተው ልምዱ በመነሣት ፡ ያስተላለፈው መልእክቱ ዛሬም አስተዋጽአው ከፍተኛ ነው ።

ለሌሎች ካላሰብንና የምንችለውን ካላደረግንላቸው ፡ ከደስታ ምንጮች አንዱን እንዳደረቅን እንገንዘብ ።

ሬይ ሊመን ዊልበር

☆ ☆ ☆

ደስታና ሽቶ አንድ ናቸው ። ለሌሎች ሲያርከፈክፏቸው ለራስም ይተርፋሉና ።

ራልፍ ዋልዶ ኢመርሰን

ገንዘብ ምግብን እንጂ የመመገብ ፍላጎትን ፡ መድኃኒትን እንጂ ጤንነትን ፡ አጃቢን እንጂ ጓደኛን ፡ ግልጋሎትን እንጂ ታማኝነትን እንደማይገዛ ሁሉ ፈንጠዚያን እንጂ ዘላቂ ሰላምና ደስታን አያስገኝም ።

ሄንሪክ ኢብሰን

☆ ☆ ☆

ገንዘብና ገንዘብ የሚገዛቸውን ነገሮች ሁሉ ማግኘት መልካም ነው ። ታዲያ ፡ ዐልፎ ዐልፎም እንኳ ቢሆን ፡ በገንዘብ የማይገኙ አያሌ በረከቶችን እንዳላጣን መገንዘብ ብቻ ሳይሆን ማረጋገጡም ይበጃል ።

ጆርጅ ሆራስ ሎሪመር

☆ ☆ ☆

በወቅቱ፡ የምትሠነዘር ቃል ምንኛ መልካም ናት!

መጽሐፈ ምሳሌ

☆ ☆ ☆

ዊሊያም ላዮን ፌሊፕስ

«ማድማዳዎቹ በውብ ሥዕሎች ባሸበረቁ የአዕምሮ ጓዳ የሚኖር ሰው ምንኛ የታደለ ነው!»

ዊሊያም ላዮን ፌሊፕስ ረጅምና የተደላደለ የሕይወት ዘመኑን ለማገባደድ ተቃርቧል ። ደራሲ ፣ ሐያሲ ፣ በዬል ዩኒቨርሲቲ ተወዳጅ መምህር ሆኖ ለብዙ ዓመታት ባገለገለበት ወቅት በአስተሳሰቡ የአያሌ ወጣቶችን ሕይወት ለማረቅና ለመኮትኮት በቅቷል ። ከራሱ ፍሬያማ ሕይወት የመነጨ ፣ በማንኛውም ሁናቴ ላይ ለሚገኝ ሰው በመርሕነቱ ደስታንና ርካታን የሚለግስ አንድ መልዕክት እንዲያስተላልፍ በአንድ ወቅት ተጠየቀ ።

ፕሮፌሰር ፌሊፕስ ፣ ወደ አሳለፋቸው ዓመታት አማተረ ። በኮሌጅ የመጨረሻ ዓመት ተማሪ በነበረበት ወቅት የደስታን ምንነት ከምን ጊዜውም በላቀ መንገድ የገለጸችለት አንዲት አባባል አለችው ። ዘንግቷት አያውቅም ።...... ያኔ በሕልም ዓለም የሚዋትት ገና ለጋ ወጣት እንደ መሆኑ ፣ ያች በጥሞና ያዳመጣትና ሕይወቱን ቀይሳለት በሒሊናው እንደ ተንቦገቦገች የምትኖረው አባባልም ፣ «በጣም ደስተኛ ነው የሚባለው ሰው በጐና ብሩህ ሐሳቦችን

በሕሊናው የሚያወጣና የሚያወርድ ሰው ነው» የምትል ነበረች ። አብራው በመኖርና የአመለካከት አድማሱን በማስፋት ሕይወቱን ቀርፃለታለች ። በዕድሜው እየበሰለ በሔደም መጠን ጠቀሜታዋ እየጐላ ታየው ። የገዛ ሕይወቱን እንዳዳበረችለት ሁሉ ፡ የሌሎችንም ሕይወት መሥመር ለማስያዝ በመምህርነት ጥያው ተጠቀመባት ።

«......የደስታ ምንጭ የምትሞላውና ሳታቋርጥ የምትፈሰው ፤ ከውስጣችን በሚፈልቁ ብሩህ አስተሳሰቦችና ስሜቶች ነው» ይል ነበር ለተማሪዎቹ ። ......«ይህን ነጥብ ዛሬውኑ በለጋነታችሁ ዘመን ልብ በሉት ። ዘለቄታ ያለው ደስታን ለማግኘት ከፈለጋችሁ አዕምሮዋችሁን በብሩህ አስተሳሰቦች አበልጽጉ ፤ ምክንያቱም ባዶ ጭንቅላት ጨለማ የዋጠውና በቀላሉ የሚፈራርስ ቀፎ ነው ። ባዶ ጭንቅላት ከደስታ ይልቅ ፊንጠዚያ ላይ ያተኩራል ።......

«ገና ከጠዋቱ ብሩህ አስተሳሰቦችን ማሰላሰል ከያዝን ፡ በዕድሜ እየገፋን ስንሔድ ደስታችንም እየመጠቀ ይሔዳል ። ሕይወትን በሥርዓት መምራት ማማ እንደ መውጣት ይቆጠራል ። ከማማው አጋማሽ ላይ ስንደርስ እይታችን ከቀድሞው ሰፋ ይላል ፤ አሻቅበን በተጓዝን መጠንም የምናየው የበለጠ እየጠራና እየሰፋ ይመጣል ።

«ይህ ነው የትምህርት ዋንኛ መሠረቱ ። የበሰለ ትምህርት ሰብዕናን ያዳብራል ። አዕምሮን ያበለጽጋል ። ደስታንም ያጎናጽፋል ።...... ለእርጅና ዘመና

ችን መድኅን ፤ ለደከሙ ጉልበታችን አለኝታ የሚሆን ንና ከአውሬነት ባሕርይ የሚያላቅቀን ትምህርት ነው ። ስለዚህ በወጣትነት ዘመኑ ዕውቀትን የሚ ያካብትና ጥበብን የሚካን ሰው ሕሊናውን አዳብሮ ፤ ግድግዳዎቹ በተዋቡ ሥዕሎች ባሸበረቁ የአዕምሮ ጓዳ ውስጥ ለመኖር በመቻሉ ዕድለኛ ነው ......»
የሚል ነበር ትምህርቱ ።

የደስታን ገጽታ አጣርቶ የሚያሳየው ይህ የዊሊያም ላዮን ፌሊፕስ ፍልስፍና ለመጀመሪያ ጊዜ ብቅ ያለው በአንድ ጋዜጣ ላይ ነበር ። ከዚያም ወዲህ ተደጋግሞ ታትሟል ። እዚህ የቀረበው በቁንጽል ቢሆንም ፤ አቀጣጫውንና መስሕብነቱን ለመገንዘብ እምብዛም አያዳግትም ።...... ያ ተወዳጅ መምህር ዛሬ ድምፁ ባይሰማም ፤ መልዕክቱ አያሌ ወጣቶ ችን እየቀሰቀሰና እየመራ ነው ።

የዕውቀት ብልጭታ ያሞቅናል ፤ በጉ ሲቃ ነውና ።

አ ቢ ድ

☆ ☆ ☆

ትምህርት በፍሥሐ ዘመን ጌጥ ፤ በመከራ ዘመን መጠለያ ፤ በእርጅና ዘመን ደግሞ ምርኩዝ ናት ።

አርስጣጣሊስ

☆ ☆ ☆

በቀለም ጠብታ ቃላት ይገዝፉና ፣
እንደ ጤዛ ፈክተው በሰው ልጅ ሕሊና ፣
በወግ ይሥሉታል በምናቡ እንዲመጥቅ
ስክኖ እያስተዋለ በጥልቅ እንዲራቀቅ ።

ሎርድ ባይረን

☆ ☆ ☆

በበሳል አስተሳሰቦች አዕምሮዋችሁን አበልጽጉ ።

ቤንጃሚን ዲዝራኤሊ

☆ ☆ ☆

ዐዋቂ ሰው ማን ነው? ከሌሎች የሚማር ።

ታልሙድ

☆ ☆ ☆

ፍሬድሪክ ሎሚስ

«መንፈስህን አድስ— ዘግየት ሳትል አልቀረህም»

ዶ/ር ፍሬድሪክ ሎሚስ ለሐያ አንድ ዓመታት በአዋላጅነት ያለ በቂ ረፍት ያገለገለ ታታሪ ሰው ሲሆን ፡ በእነዚያ ዓመታት ውስጥ የእያሌ እናቶችን ጭንቀት በጥሞና እየዳመጠና በእንክብካቤውና በምክሩ ፍርሃታቸውን እያስወገደላቸው በሰላም እንዲገላገሉ ረድቷቸዋል ። የሰው ሥቃይ ጠልቆ የሚሰማው ርኅሩኅ ሰው በመሆኑ ፡ ርዳታውን ለሚሹ ሁሉ እርሱነቱን ስለሚሠዋ ለራሴ የሚለው እምብዛም ጊዜ አልነበረውም ። የእርሱ ዓለም ፡ «በወሲብ ላይ የተመሠረተና በፍቅር ግፊት የሚሽከረከር ፡ ደስታና ፍርሃት የዋጡት ዓለም ነበር»— እርሱ ራሱ እንደ ገለጸው ።

በአንድ ወቅት አንድ ውሳኔ ላይ ደረሰ ። ለሐያ አንድ ዓመታት ያጋጠሙትን ነገሮች በሚያሰላስልበት ወቅት ፡ የሕክምና መሣሪያዎቹን በድንገት እስጥሎ ብዕር የሚያስጨብጠው አንድ ሁኔታ ገጠመው ። መንሥዔውም አንዲት ደብዳቤ ነበረች ።

ከቀደምት ጽሑፎቹ አንደኛው ፡ «በአትክልት ውስጥ» የተሰኘው ሥራው ሲሆን ፡ ጭብጡ

የተመሠረተውም ከቻይና በተላከችለት በዚያች ዶብዳቤ ላይ ነበር ።

«ውድ ዶ/ር» ይላል ፡ የዚያች ደብዳቤ መግ ቢያ ። « ደብዳቤዬ ስትደርስዎ ግር እንዳይልዎ ። በመጨረሻዎቹ ስሞቻችንም እርስዎና እኔ ሞክሼ ዎች ስለሆን ፡ ያሠፈርኩት የመጀመሪያ ስሜን ብቻ ነው ።

«አያስታውሱኝ ይሆናል ። ከሁለት ዓመታት በፊት በሚሠሩበት ሆስፒታል ተኝቼ ነበር ። ሆኖም የተመደበልኝ ዶክተር ሌላ ነበር ። ልጄንም በተገላ ገልኩበት ዕለት አጥቼዋለሁ ። ታዲያ በዚያኑ ቀን ያ ዋለደኝ ዶ/ር ወደ መኝታ ክፍሌ መጥቶ ‘ሞክሼሽ የሆነ አንድ ዶ/ር ስምሽን ከመዝገብ ላይ አይቶ ስለ አንቺ ጠይቆኝ ነበር ። ምናልባት ዝምድና ይኖራ ችሁ ይሆናል ። ሊጎበኝሽም ያስባል ። ግን ለጊዜው ማንንም ለማነጋገር አለመፈለግሽን ነግሬዋለሁ ። ......ይምጣ እንዴ?, አለኝ ። መስማማቴን ገለጽኩ ለት ።

«እርስዎም ወዲያውኑ ወደ ክፍሌ ጐራ ብለው እጄን ይዘው ካጠገቤ ተቀመጡ ። ብዙም አላነጋገ ሩኝም ። ሆኖም ከአመለካከትዎና ከድምፅዎ አወራ ረድ ለእኔ ማሰብዎን ተገንዝቤ ከመቅፅበት ተጽናናቻ ለሁ ። ከዚያች ዕለት ወዲህም ለዳግመኛ ጊዜ አል ተያየንም ። ነገር ግን ፡ ስለ እርስዎ ማንነት ነርሶቹን ጠይቄ ፡ ከዚያ ሆስፒታል ቀንና ማታ እንደማይለዩ ሰምቻለሁ ።

ድረግ ካቀድንበት ሥፍራ ስንደርስም ፣ እንዳጋጣሚ ሆኖ ፣ ባህብታምነቱ የታወቀ አንድ ሰው ተቀብሎን በተንበሸበሸ መስተንግዶው ያዝናናን ጀመር ።

ታዲያ ፣ አንድ ቀን እኛም በተራችን ያን ሰው በ'ጐልፍ' ጨዋታ ልናዝናናው በማሰብ ብንጋብዘው፣ «አዬ ወንድሞቼ! ዐልፎ ዐልፎ ነው እምጫወተው ። ባዘወትረው ግን ደስ ባለኝ ! ፈረሶችም አሉኝ ። ታዲያ በምወደው በፈረስ ግልቢያ እንኳ መንፈሴን ለማደስ ጊዜ አጣሁ ። አሁን ደግሞ ፣ ባለቤቴ ልጆቻችንን ይዛ እንደ እናንተው ለመዝናናት ራቅ ወዳለ ሥፍራ ሔዳለች ። አብሬያቸው ለመሔድም ፈልጌ ነበር ። ግን የግማሽ ቀን እንኳ ረፍት የለኝም ። ለእንዲያ ያለው ኑሮ ከእኔ ይልቅ ተላላኪዬ የታደለ ነው» በማለት እሮሮውን አሰማን ።

«ጌታው» አልኩት ፣ «እኔ እዚህ ድረስ ለምን እንደ መጣሁ ታውቃለህ?»

«ምናልባት ብዙ ሥራ የለብዎ ይሆናል ፣ ወይም ጊዜና ገንዘብ ተትረፍርፎዎ ነው» አለኝ ።

«አይደለም» አልኩት ፣ «ብዙ ሥራ ነበረብኝ ። የተትረፈረፈ ጊዜም ሆነ ገንዘብ የለኝም ። በዚህ በሚያምር በረንዳህ ላይ ዛሬ ባልንጀራዬና እኔ ተቀ ምጠን ለመጫወት የበቃነው ፣ ባያት የማላውቃት አንዲት ሴት ከቻይና እምብርት ፣ ከፒኪንግ ከተማ ፣ በነሐስ ላይ ተቀርፆ የተመለከተውችን አንድ ጽሑፍ ልካ ስለ ቀሰቀሰችን ነው ።»

ወዲያውኑ ወደ አንድ የልብ ጓደኛዬ ስልክ ደውዬ ወደ ቢሮዬ እንዲመጣ ነገርኩት ። እንደ ዶሪ ስም ለረፍት ከአካባቢያችን ለመውጣት እንዳቀድኩ አሜውቸው አብረን እንድንሔድም ጋበዝኩት ።

ታዲያ ፤ እርሱ ስለ ግብዣዬ አመስግኖኝ ሥራ የተቆለለበት መሆኑን በመዘርዘር ፤ ለአንዲት ሳምንት እንኳ ለማረፍ እንደማይችል አወሳኝ ።

ያችን ደብዳቤዬን አነበብኩለት ። ራሱን ነቀ ነቀ ። «አልችልም» አለኝ ። «ብችል ደስ ባለኝ ! አዝናለሁ ፤ ባይሆን ሌላ ጊዜ...... አንድ...... ሌላ ቀን......» ሲል ቃላቱ ተንጠባጠቡበት ። «ምን ነበር ያለችው ያች ሴት?» አለኝ ፤ እንደገና በድንገት ። 'ዝግየት ሳትል አልቀረህም?' አዎ !......» በማለት ጥያቄውን ለራሱ በራሱ መልሶ እንደ ተቀመጠ በሐሳብ ተጓዘ ። በመካከላችን ዝምታ ሠፈነ ። ባለፈው ሌሊት እኔ ሳደርግ እንዳደርኩት ሁሉ ፤ እርሱም የተቆለለበትን የወቅቱን ተግባር ከሚቀረው አጭር የሕይወት ዘመኑ ጋር እያነጻጸረ ሲመዝን ታየኝ ።

በመጨረሻም ፤ «ቅድም የነገርኩህን ሥራ ከፍጻሜ ለማድረስ ባለጉዳዮቼን ስጠብቅ ሦስት ወር ሆነኝ ። ይበቃኛል ። አሁን ደግሞ በተራቸው እነርሱ ሲጠብቁኝ ይችላሉ ። ለመነሣት የምትፈልገው መቼ ነው?» የሚል ጥያቄ አቀረበልኝ ።

አብረን ተጓዝን ። ባሳለፍናቸው ቀናት ብዛትና በጉዞዋችን ርቀት መጠን ሸክማችን እየቀለለን ፤ አካላችንና መንፈሳችን እየታደሰ ሔደ ። ቆይታ ለማ

ቀን ፣ ከሥራ እንደ ተመለሱ እስቲ ለአንዳፍታ ብቻ ዎን ሆነው በዚህ ጉዳይ ላይ ያስቡበት ።

ማርገሪት»

አብዛኛውን ጊዜ ሰላማዊ እንቅልፍ ይወስደኝ ነበር ፣ የስልክ ጩኸት እስካልቀሰቀሰኝ ድረስ ። በዚያን ዕለት ማታ ግን ስባንን አደርኩ ፣ ያ የንሐስ ላይ ጽሑፍ እየታየኝ ። ከአንዲት ከማላስታውሳት ሴት ደብዳቤ ስለ ደረሰኝ ፣ እንዲያ በመሆኔ ራሴን መልሼ መላልሼ በመውቀስ ነገሩን ለመርሳት ሞከ ርኩ ። ግን አልሆነልኝም ። «አዎ ፣ ዘግየት ሳትል አልቀረህምና አስብበት!» የሚል የራስ በራስ ወቀሳ ፋታ ነሣኝ ።

በማግሥቱ ጠዋት ፣ ወደ ቢሮዬ ሔጄ ረዘም ላለ ረፍት እንደምወጣ ለሥራ ባልደረቦቼ ነገርኳቸው ።

በከባድ ኃላፊነት የተጠመደ ማንም ሰው ለረ ፍት ውጣ ማለቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ። ከዚህ በፊት ፣ እንዲሁ ከመሥሪያ ቤቴ ለረፍት ራቅ ብዬ ሳለሁ ፣ በባልደረቦቼ ብቃት ባልጠራጠርም ፣ ነገሮች ሁሉ ተበላሽተው እንደሚቆዩኝ ሥጋቼ ነበር ። ሆኖም ስመለስ የጠበቁኝ ሕሙማን ብዛት ትቻቸው ከሔድ ኩት በላይ አልነበረም ። አብዛኞቹም የመሻል ምል ክት ይነበብባቸው ነበር ። እንዲያውም ብዙዎቹ መኖር አለመኖሬን እንኳ የተገነዘቡልኝ አልመሰለ ኝም ። እንዲህ በቀላሉ በሌሎች ልተካ መቻሌን ማወቁ ቢከነክነኝም ፣ መልካም ትምህርት ሆኖኛል ።

ታሪኩን በዝርዝር አወጋሁት ። እንደ ጓደኛዬ እርሱም ቃላቱን እንድደግምለት ጠየቀኝ — «መን ፈስህን አድስ ፣ ሳትዘገይ አልቀረህም ።» ያን ዕለት በሐሳብ ተጨብጦ ዋለ ።

በማግሥቱ ጠዋት ፣ ባረፍንበት ሆቴል መተላለፊያ ኮሪዶር ላይ ስንገናኝ ፡ «ዶ/ር» ብሎ ጠራኝ ። «እንዴ ይቆዩኝ ። ዕንቅልፍ ሳይወስደኝ አደርኩኮ! እርስዎ ራስዎ እንዳሉት ፣ አንድ ያልተጠበቀ ሰው የሌላን ሰው የሕይወት አቅጣጫ በድንገት መለወጡ እንግዳ ነገር ነው ፣ አይደል? እኔም ወደ ባለቤቴና ልጆቼ ዘንድ ለመሔድ ቴሌግራም ልኬያለሁ» አለኝ።

እጁን ትከሻዬ ላይ ጣል አድርጎም፡«ያን ጽሑፍ ያሠፈሩት ጣቶች የብስ አቋርጠው ፣ ባሕር ሰንጥቀው እንዲህ ሊኮረኩሩን የቻሉት ምንኛ ረጃጅም ቢሆኑ ነው!» በማለት አሣቀኝ ።

......ከዚያ ወዲህ አብሮኝ የሔደው ጓደኛዬና እኔ ብዙ ዓመታት አሳልፈናል ። እስከ ቅርብ ጊዜም ድረስ ጤነኛና ጠንካራም ነበር ። ታሞ በተኛበትም ጊዜ የቀሩትን ጥቂት ዓመታት ከእልጋው ሳልርቅ ተካፍያለሁ ። እናም ደግሞ ፣ ደጋግሞ ይለኝ የነበረው «ፍሬድ ፣ ያን የመሰለ ረፍት በመውሰዳችን እንዴት ደስ ብሎኛል ይመስልሃል! እንኳንም ያልዘገየን!»

ይህ ነው እንግዲህ ፣ ቻይና ውስጥ በሚገኝ በአንድ የአትክልት ሥፍራ ፣ በነሐስ ላይ የተቀፀረው

ጽሑፍ መልእክት ። ስለዚህ ምናልባት ዘግየት ሳንል አልቀረንምና እኛም እስቲ በጉዳዩ እናስብ በት ።

ብዙ ሰዎች፣ከአድማስ ማዶ በመቃኘት ገና ወደፊት — ጊዜ ሲያገኙ — ለመደሰት ያልማሉ ። ዛሬን ከሌሎች ቀናት ሁሉ የሚያልቃት አንድ እውነታ አለ ፤ ያም በእጅ የገባች መሆኗ ነው ።

ቻርልስ ኮልተን

☆ ☆ ☆

ደስታ በቀጠሮ አትጠመድም ። እርሷን እንዳመጣጧ ማስተናገድ እንጂ ለነገ ፤ ለመጪው ዓመት ፤ ለወዲያኛው ዓለም እያሉ መግፋት አያዋጣም ። የመጪው ዓመት ሕይወት እንዲሠምር የዘንድሮው መሟላት አለበትኮ! ዛሬ በአግባቡ ካልተያዘች ነገ አታስተ ማምንም ።

ቶማስ ዲሪየር

☆ ☆ ☆

ደስታ ባእያንዳንዷ ቀንና ሰዓት ደም ሥር የምትገኝ ኳለል መሆኗን የምንገነዘበው..... ዋይ ነዶ!..... በጣም ዘግይተን ነው ።

ስቲፈን ሊኮክ

☆ ☆ ☆

በጣም አስከፊ ከሆኑት ድርጊቶቻችን መኻል አንዱ ደስታን ገሸሽ ማድረጋችን ነው ። መስኮቶቻችን ሥር የፈኩትን ጽጌረዳዎች ችላ ብለን ከአድማስ ባሻገር ያለ የሚመስለንን ውብ የአትክልት ሥፍራ እናልማለን ።

ዴል ካርኔጊ.

ክፍል ሁለት

ወኔና ጀብዱ

«መፍራት ያለብን ራሱን ፍራቻን ብቻ ነው ።»

ፍራንክሊን ሩዝቬልት

የተድላና የምቾት ኑሮ ምንጊዜም አይለየንም ብለን መገመት አንችልም ። ከችግር ፣ ከጭንቀትና ከፍርሃት ጋር የምንፋጠጥበት ፣ በሐዘንና በሌሎች ሳንካዎች እርምጃችንን የምንገታበት ጊዜ ያጋጥመናል ። የሕይወት ግዴታዎች ናቸውና ማንኛችንም ብንሆን ከእነዚህ ልናመልጥ አንችልም ።

«የሕይወት ጉዞን በተራሮች ጫፍ ላይ ብቻ በመረማመድ እናገባድድም ። በጉዞዎችን ላይ ወንዞችና ሸለቆዎች ያጋጥሙናል ። አንዳንዴ አዙረው በሚደፉ ቁልቁለቶች ስንንደረደር ፣ አንዳንዴ ደግሞ እልህ አስጨራሽ አቀበቶችን እንጋተራለን» በማለት ጆን ባሮውስ እንዳስቀመጠው ሁሉ ፣ ሮበርት ሉዊስ ስቲቨንስንም «የረጋ መንፈስ አይወናበድም ፤ አይናወጽም ። ዶፍ እንቅስቃሴውን እንደማይገታው የሰዓት እጇታ ምንጊዜም ሚዛኑን ጠብቆ ተግባሩን ያከናውናልና» በማለት የወኔን ኃያልነት ይጠቁማል ።

«ብዙ ሰዎች ጥርጣሬና ፍርሃት በሚያስከትል ባቸው የመንፈስ መላሸቅ በሽታ እየተለከፉ ሲዝለፈለፉ እንዳየሁ ሁሉ በዓላማ ጽኑነት ሲፈወሱም ተገንዝበ ደስ ብሎኛል» ሲል ሪቻርድ ካቦት የወኔን አስፈላጊነት አጉልቶ ለማሳየት ሞክሯል ። ሌሎች ባለቅኔዎችና ፈላስፎችም ፣ ይህንኑ ጉዳይ በተለያዩ መንገዶች ሲገልጹልን ኖረዋል ።

በተለያዩ ዘመናት ከተሠነዘሩት አያሌ ቀስቃሽ የወኔና የትዕግሥት ታሪኮች መካከል ጥቂቶቹን እነሆ።

☆ ☆ ☆

ፖል ሃሚልተን ሄይን

«......... ይህም ያልፋል ....»

በጥንት ዘመን ጭንቀት የዋጠውና ችግር ከየ አቅጣጫው ያፈጠጠበት አንድ የሩቅ ምሥራቅ አገር ንጉሥ ፡ ጠቢባኑን ሰብስቦ አንድ ግሩም ጥቅስ እንዲ ፈጥሩለት አዘዛቸው ። ጥቅሱ በደስታም ይሁን በሐ ዘን ወቅት ከዐይኖቹ የማይርቅ ፡ እጥር ምጥን ያለና በቀለበቱ ላይ ሊቀረፅ የሚችል መሆን እንደሚኖር' በት አስገነዘባቸው ።

ጠቢባኑ ለረጅም ጊዜ ጉዳዩን ሲያወጡና ሲያ ወርዱ ከቆዩ በኋላ ጥልቅ የሆነ ፡ ለፍሥሐም ሆነ ለመከራ ጊዜ የሚያገለግል ፡ እውነትን የሚያንጸባ ርቅና ጊዜ የማይሽረው ፡ ማንም ሰው የዕድሜ ልክ መመሪያው ሊያደርገው የሚችል ጥቅስ ይዘው ንጉሡ ዘንድ ቀረቡ ።

«በሰላምም ሆነ በቀውጢ ወቅት ፡ በየትኛውም ሥፍራ አዕምሮን የሚያስገዛ ነውና ይቀበሉን» በማ ለት ንጉሡ በቀለበቱ ላይ እንዲያስቀርፅ ያቀረቡለት ብሂል ፡

«ይህም ያልፋል»

የሚል ነበር ይባላል ።

ይህ ታሪክ ለዘመናት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ ኖሯል ። ለአንድ ንጉሥ የተፈጠረ ይሁን አይሁን ያረጋገጠ የለም ። ማረጋገጡም አስፈላጊ አይደለም ። ቁምነገሩ ጥቅሱ ጥልቅ ፡ ተጨባጭና ጊዜ የማይሽረው መሆኑ ነው ። በማንኛውም ሰው ልቦና ሥርጾ ገብቶ በየትኛውም ወቅት መልእክት ማስተላለፍ መቻሉ አያጠያይቅም ። ስለሆነም ላዘኑ ጥናትን ፡ ለፈሩ ድፍረትን ፡ ሐሞታቸው ለፈሰሰ ወኔን ፡ ለተጨነቁ ተስፋን ፡..... እየለገሰ ኃይሉን ሲያስመሰክር ይኖራል ።

አንድ ቀን አንድ ጋዜጠኛ ፡ ከላይ የተጠቀሰውን ታሪክ አንብቦ ስለ ተመሰጠ ፡ በአንዲት አጭር ድር ሰቱ ውስጥ አካትቶ ለሕዝብ አቀረበው ። በሕዝብ ዘንድ ያሳደረው ስሜት የጋለ ነበርና ጋዜጠኛው ቀጠል አድርጎም «ይህም ያልፋል» በሚል ርዕስ አንዲት ግጥም አፈለቀ ።

ይህም ያልፋል

ሐዘን አሰጠመህ? እስቲ ባክህ ርሳው ፤
ጭብጥ ፡ ከርምት አትበል—አላፊ ጣጣ ነው ።
ደስታ ፈነቀለህ? ፈንጠዚያ አታብዛ ፤
እልም ይላል ተንኖ እሱም እንደ ጤዛ ።
አደጋ አጋጠመህ? አዕምሮህ እንዳይዝል ፤
ተስፋን የሙጥኝ ካልክ አይዞህ! ጭልጥ ይላል ።
ማጣት ከፋ አስመኘህ? ምን ቢያብከነክንህ
አንድ ነጥብ ልብ አርግ—እርሱም ያልፋል ጥሎህ ።

ዝናህ ገነነና ደመቅህ እንደ ፋና?
«ሰው ጤፉ!» እንዳትባል — አላፊ ነውና!
የትም ሥፍራ ብትደርስ ፡ ምንም ነገር ብትሆን ፡
«ይህም ያልፋል» ብለህ መዝን እንተነትክን ።

ያዚህች አጭር ግጥም አፍላቂ ፖል ሃሚልተን ሄይን ሲሆን ፡ ግጥሟ ከብዙ ሰዎች ቦርሣና ኪስ ለዓመታት ሳትለይ ተደጋግማ የምትነበብ ተወዳጅ በረከት ለመሆን በቃች ።

ዛሬም በመንፈስና በአካል ለቆሰሉ ፡ ተስፋ ላጡ ሰዎች የብርታት አስተዋጽኦዋን እያደረገች ነው ። ዐልፎ ፡ ዐልፎም በጋዜጦችና በመጽሔቶች ብቅ ትላለች — አንዳንዴ ርዕሷን ቀይራ ፡ ወይ ረዝማ ወይ አጥራ ፡ ወይም ለወቅቱ ተስማሚ በሆነ መንገድ ተለውጣ ።...... መልዕክቷ ግን ምን ጊዜም ያው ነው ።

ሬይ ስታናርድ ቤከር የተባለ ሰው ፡ ታሞ በመማቀቅ ላይ እያለ ትውስ ብላው ደጋግሞ ካነበባት በኋላ ፡ «የማያልፍ ነገር የለም — ውጋትም ቢሆን» ሲል ማስታወሻ ደብተሩ ላይ አሥፍሯት እፎይታን እንዳስገኘችለት መስክሯል ።

ሮበርት ሉዊስ ስቲቨንሰን ፡ በሳምባ ነቀርሣ እየተሠቃየ አካሉ ዝሎ ሳለ እፎይታን ትለግሰው ዘንድ ይደጋግማት ነበርና ሥቃዩን እያስታገሠችለት የድርሰት ሞያውን እንዲገፋበት ረድታዋለች ። «በየቀኑ አንዳንድ ምዕራፍ ለመጻፍ ተነሣሥቻለሁ» በማለት

ልክ እንደርሰው በሕመም ቢጠወልግም ፡ ሕይወቱን በወኔ ይመራ ለነበረና ዊሊያም ሄንሊ ለተባለ ጓደኛው ገልጾለታ ል ።

አብርሃም ሊንከንም ለማያምንበት አገል የሰ ላም ድርድር እጁን ባለመስጠቱና ለቆመለት ዓላማ ያለእንዳች ማወላወል በመገዛቱ ፡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ጥላቻንና ዘለፋን በሚያወርዱ በት ወቅት «ይህም ያልፋል» እያለ ራሱን ያጽናና እንደ ነበር ይነገራል ።

ማንኛውም ነገር — የተፈጥሮም ይሁን ሰው ሠራሽ — እንዴት እንደሚለዋወጥ እስኪ ልብ ብለን እናስተውል ። የዓለማችን መሠረታዊ የተፈጥሮ ባሕርይ ዝንተዓለም ሲንኳለል በሚኖር ጅረት ይመ ሰላልና ፡ ማንኛውም ነገር በማያቋርጥ የለውጥ ሒደት ውስጥ ማለፉን ብቻ ሳይሆን አንዱ ለሌላው የማያቋርጥ የለውጥ ማራት መሆኑንም እንገንዘብ ።

ማርክስ ኦሬሊየስ

☆ ☆ ☆

የመጣው ቢመጣ ፡ ወቅቱ ምን ቢጨልም —
ሰዓቱ ይከንፋል ፡ ጊዜ እንደሁ አይቆምም ።

ዊሊያም ሼክስፒር

☆ ☆ ☆

በርጋታ ተራመድ ቀውጢ ቀን ሲገጥምህ ፡
ትዕግሥትን ተመርኩዝ ፡ ሕሊናህን ስለህ ።
ዛሬ ጭልጥ ብላ ስትሆን ትናንትና ፡
ዞረህ ታያታለህ አልፈሃታልና ።

ዊሊያም ኩውፐር

☆ ☆ ☆

የለም — ብዙ አትዘን ኑሮ ቢመርህም ፡
ላንተ ብሶት ብሎ የማለዳ ሰማይ መፍካቱን
አይተውም ።
ጸደይ አትሸሽግ ላንተ ሐዘን ብላ ፤
ጽጌረዳ ደርቃ አይበቅል አሜከላ ።

የለም — አትብከንከን ኑሮ ቢቸክህም ፤
ጊዜ እንደሁ ይሮጣል ላንተ ሲል አይቆምም ።
ዛሬ ቢያስቃይህ በጉምዛዛ ቃና ፡
ከመቅጽበት ያልፋል ሊባል ትናንትና ።

የለም — አትንሰቅሰቅ ፤ መጭው አዲስ ሕይወት፡
ገና ያልተነኩት የፍሥሐ ዓመታት ፡
ቡቡ ሰው ነህ ብለው እንዳይታዘቡህ ፤
ላፈሰሱት ዕንባም እንዳያፍሩ ዐይኖችህ ።

ሳሮጂኒ ናይዱ

☆ ☆ ☆

«ይህም ያልፋል!» በለኝ ልቤ ሆይ ደጋግመህ ፡
የምታምጠው ጭንቅ ፡ ያመቅኸው ብሶትህ ፤

ሥቃዩ ጊዜያዊ መሆኑን ነገረኝ ፤
ነገ እፎይ እንደምል እባክህ አብሥረኝ ።

«ይህም ያልፋል!» በለኝ ፡«በራሱ እልም ይላል፣
እንደነፋስ በንኖ እንደጣይ ይጠልቃል»
በልና ንገረኝ ፡ «ይመጣል እፎይታ!»
ሁሉን የሚያስረሳ የሰላም ሽለብታ ።

ደጋግመህ ንገረኝ ልቤ ስትል ላንተው ፤
«ይህም ያልፋል!» በለኝ እንደ ትናንትናው ፤
ጥሎኝ እንደ ጠፋው ነቅሎ ሰቀቀኑን ፡
እንዳረጀው ውጋት እንዳፈጀው ሐዘን ።

ሰማይ እንደሚደምቅ በኮከቦች ፍካት ፡
ሌት ቀን እንደሚሆን በተፈጥሮ ዑደት ፡
ነፋስ ያነጠፉት ማር ቀና እንደምትል ፡
ብሶት ይሁን ቁጣ — በለኝ ፡ «ይህም ያልፋል!»

ግሬስ ኖል ክሮዌል

☆ ☆ ☆

ዊሊያም ኧርነስት ሄንሊ

«የዕጣዬ ባለቤት ነኝ እኔው ራሴው ፤
እኔው ነኝ መንፈሴን አቅጣጫ አማስይዘው ።»

ዐሐይዋ ወደ መኝታ ክፍሉ በአንድ ጥግ በኩል ገብታ ፍንትው ብላለች ። ወጣቱ በአልጋው ላይ እንደ ተጋደመ ድምቀቷን ተመለከተና ፊቱን እንደ ገና ወደ ግድግዳው መለሰ ። ሆስፒታል ከገባ ሁለት ዓመታት አልፈውታል ። ዶ/ር ሊስተር የተባለ የቅርብ ሐኪሙ ሁለተኛውን እግሩን ከመቆረጥ ለማትረፍ ከፍተኛ ጥረት እያደረገለት ነበር ። ወጣቱ ቀደም ሲል ለብዙ ኦፕራሲዮን ተዳርጓል ። ቁጥሩን በውል ባያውቀውም ፣ ቢያንስ ለሐያ ጊዜ ይሆናል ፣ በሐያ አራት ወራት ውስጥ ለኦፕራሲዮን አካሉን ያቀረበው! ግን አልተበገረም ።

እንደገና ወደ ፀሐይዋ ብርሃን ቃኘት አደረገና ፈገግ አለ። ቃላት በሕሊናው ውስጥ እየቃጨሉበት፣

የዕጣ ፋንታ ፍርጃ በጥፍሩ ቢያንቀኝም ፣
ግንባሬን አልቋጥር! ሙሾም አላወርድም »
የሚል እንጉርጉሮ እንዲያንቆረቁር ገፋፋት ።

ያ ወጣት ዊያሊያም ኧርነስት ሄንሊ ይባላል ። በሐያ አምስት ዓመታት እጭር የሕይወት ዘመኑ እንደርሱ ለሥቃይ የተዳረጉ ሰዎች ቢኖሩ በጣት የሚቆጠሩ ናቸው ። ከሕፃንነት ዕድሜው ጀምሮ ሥር በሰደደ የአጥንት ካንሰር በሽታ ይሠቃይ ስለ ነበር በጊዜው በተለመደው መፍትሔ መሠረት አንድ እግሩን አጥቷል ። ሁለተኛው እግሩም ይህንኑ ዕጣ ነበር የሚጠብቀው ። ከዚህ ክፉ ዕጣ ለመትረፍም ነበር ረጅም ጊዜ የአልጋ ቁራኛ የሆነው ። ዶ/ር ጆዜፍ ሊስተርም አዲስ የሕክምና ብልሃት እየሞከ ረለት ነበር ።

በበሽታ ፣ በድህነት ፣ በመከራና በጉስቁልና ...... የሰው ልጅን የቻይነት ብቃት በሚመዝኑ በበርካታ የሕክምና ሙከራዎችና ቀዶ ጥገናዎች መሠቃየት ነበር የሄንሊ ሕይወት — እርሱ ትዝ እስከሚለው ።

«ተስፋ አልቆርጥም!» ይል ነበር እንደ ተጋ ደመ ፣ ራሱን ለራሱ ቃል ሲያስገባ። «ምንም ልሁን ምን ፣ አልበገርም!» ይል ነበር ደግሞ ደጋግሞ ራሱን ሲያጽናና ። ያ ወኔውም ወደ ሕያውነት አሸጋገረው።

ከዚያ የውጋትና የሥቃይ ሕይወቱ ፣ የደረሰ ፀትን አሠቃቂ በትር በቻይነትና በልበ ሙሉነት ካመቀበት ሕዋሳዊ ጓዳው አምጦ ወኔን ከሚያጐሉና መንፈስን ከሚያመጥቁ ውብ ሥነ—ግጥሞች አንዱ የሆነውን «ኢንቪክቱስ»ን ወለደ ።

«ኢንቪክቱስ» የላቲን ቃል ሲሆን ፣ትርጕሙም በእንግሊዝኛ «ኢንቪንስብል» ነው ። ወደ አማርኛ

ሲመለስም «የማይበገር» ማለት ይሆናል ። ስለዚህ ግጥሙም «አይበገሬው» የሚል ርዕስ ተሰጥቶታል ።

አ ይ በ ገ ሬ ው

በድቅድቅ ጽልመቱ፡ ካሰጠመኝ ሌሊት ፡
ከእንጦርጦስ ጨለማ መድረሻ አልባው እዝቅት
ባማልክት ኃይል ይባል—በምን ይሁን በምን ፡
አልጠራጠርም በድል መወጣቴን ።

የዕጣ ፋንታ ፍርጃ በጥፍሩ ቢያንቀኝም ፡
ግንባሬን አልቋጥር! ሙሾም አላወርድም ።
ሕሊናዬ ቢቆስል በክፉ ዕጣ ናዳ ፡
እኔ እንደሁ ወይ ፍንክች — ያበጠው ይፈንዳ!

ከሥቃይ ማዕበል ፡ ከእንባ ጐርፍ ጀርባ ፡
የጽዕረ ሞት ጥላ ሊያፍነኝ ቢያደባ ።
ያመታት መከራ ቢከመር ለትንግርት ፡
ይየኝ ፡ እየዋለሁ — አልበገርለት!

ጉዞዬ ቢያስመርር ሆኖ የዳበሳ ፡
የታሪክ ማኅደሬ ፍዳዬን ቢያወሳ ፡
የዕጣዬ ባለቤት ነኝ እኔው ራሴው ፤
እኔው ነኝ መንፈሴን አቅጣጫ ማስይዘው ።

«አይበገሬው» ታትሞ በተሠራጨበት ወቅት በዓለም ዙሪያ ፡ በተለይም እንግሊዝኛ ተናጋሪ በሆኑ አገሮች ፡ ተማሪዎች ሳይቀሩ በቃላቸው ይወጡት

ነበር ። ......ሐዘን ፣ ሥቃይና ፍርሃት ላጠመዳቸው እያሌ ሰዎች የገጠማቸውን የዕጣ በትር በወኔ እንዲቋቋሙ ፣ በደረሰባቸው ጣጣ ሳይበረግጉ በልበ ሙሉነት እንዲራመዱ ረድቷቸዋል ።

ሄንሲ እስከ ዕለተ ሞቱ ሌሎች እያሌ ግጥሞችን ደርሷል ። ሕያውነትን ያተረፈለት ግን ፣ «አይበገሬው» ነው። ከጨለመ የግል ሕይወቱ ማኅደር የመነጨ ብርሃን እንደ መሆኑ መግቢያ ለጨነቃቸውና ተስፋቸው ለመነመነ ብዙ ሰዎች ተስፋን እየፈነጠቀላቸው አዲስ ሕይወት እንዲጎናጸፉ አበረታትቷቸዋል ።

«አይበገሬው» ዛሬም ሆነ ወደፊት የሁሉም ሀብት ነውና የሰው ልጅ ካካበታቸው የሥነ ጽሑፍ ቅርሶች ጋር ለመደመር በቅቷል ።

የጅረቶች ብዛት ፣ የዝናብ መዓት ...... የውቅያኖስን ጣዕም እንደ ማይበርዙት ሁሉ የመከራ ውርጅብኝም የቆራጥ ሰው ሕሊናን በድን አያደርገውም— እንዲያ ያለ ሰው የኃያልነት ሚዛኑን ይጠብቃልና ።

ሴኔካ

☆ ☆ ☆

ትዕግሥት የሕይወት ፈተናን መወጣጫ መሰላል እንጂ ሌላ ምን ልትሆን ትችላለች?

ዊሊያም ኦስለር

ትዕግሥትና ወኔ የማያሸንፉት ምንም ነገር የለም ።

ራልፍ ዋልዶ ኢመርሰን

☆ ☆ ☆

አልማዝ ሳይሞረድ እንደማያንጸባርቅ ሁሉ ፣ ሰብዕ ናም ያለ መከራ ቦግ አይልም ።

ኮንፊሽየስ

☆ ☆ ☆

ሲታገል የሚታይ ተስፋው ስትመነምን ፤
አሚያጣጥም ደፍሮ ጕምዛዛ ሕይወትን ፤
ሕልሙ ሲደበዝዝ ጭንቀትን የማያውቅ ፤
እርሱ ነው ኃያል ሰው ከልብ የሚደነቅ ።

ቤን ጆንሰን

☆ ☆ ☆

ሕይወት የምትመዝነው በዘመን ብዛቷ ሳይሆን በም ታስመዘግበው የወኔ ክብደቷ ነው ።

ጆን ጋልስዎርዚ

☆ ☆ ☆

በዓለማችን ላይ አሻራቸውን እየተውልን ካለፉት ስመጥር ምሁራን ሥራዎች ጋር ራሳችንን ካላስተዋወቅን የሕይወትን ጣፋጭ ጣዕም ራሳችንን በራሳችን መንፈጋችን ነው ።

ጀምስ ማርቲና

☆ ☆ ☆

ስለ ሕይወት መመራመሩ ሳይሆን የገዛ ሕይወትን መምራት መቻል ነው ቁምነገሩ ። የሌሎችን ስሕተቶች ተገንዝበው ራሳቸውን ከስሕተት የሚያርቁ ሁሉ ከጸጸት ነጻ ናቸው ። ምክንያቱም ውኸንብር በስፈነባት ዓለማችን ውስጥ ዋነኛው የታሪክ መገ1 ገብ ፣ የሰው ልጅ ልምድ ፣ እንደ ማንኛውም የዕውቀት ዘርፍ ተጨባጭና አስተማማኝ ነው ።

ራይ ሌመን ዊልበር

☆ ☆ ☆

ሐሮልድ ራስል

«የታጣው ሳይሆን የተገኘው ነው ለቁምነገር የሚውለው ።»

የሚጠብቀውን ሰቀቀን አስቀድሞ እንዳወቀ ውና ለማየት እንደ ዘገነነው ሁሉ ፤ ወጣቱ ቀስ በቀስ ነበር ከተንጋለለበት የሆስፒታል አልጋው ላይ ቀና ያለው ።

ሁለት እጆቹ የሉም!

በፋሻ የተጠቀለሉትን ክርኖቹን ተመለካከታ ቸውና በሥራ አካላቱ ቅዝቃዜ ተሠራጨበት ። ደነዘ ዘው ። እጆቹ የሉም ። አካለ ስንኩል ሆኗል ።

«ምኑን ሰው ሆንኩት?» በሚል ምሬት ተዋጠ ። «ሰው ያለ እጆቹ ምን ማድረግ ይችላል? ሕይወቴ አከተመች!» አለ በልቡ ።

ግን ተሳስቷል ። ሕይወቱ ገና አላከተመችም ነበር ። እንዳውም ብሩህ የፍሥሐና የድል ዘመኑ ከበስተፊቱ ነበር የሚጠብቀው ። እጆቹን ማጣቱ ወደ አላለመው የድል ጐዳና የሚያመራው ሆነ ።

ያለ እጆቹ የቀረው ያ ወጣት ሐሮልድ ራስል ነው ። ኮከብ የፊልም ተዋናይና ዕውቅ ደራሲ እንደ ሚሆን ፤ የልጅነት ጊዜ ፍቅረኛውን አግብቶ አያሌ ሰዎች ያልታደሉትን የተደላደለና አርኪ ሕይወት እንደሚጠብቀው ያኔ ሊገምት አልቻለም ። የሚያ ውቀው እጆቹን ማጣቱንና «ተስፋ ቢስ» መሆኑን ብቻ ነበር ።

ሐሮልድ ራስል ፤ በእጆቹ ላይ ጉዳት የደረሰበት በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት በአየር ወለድነት ልምምድ በማድረግ ላይ እንዳለ ነበር ። እጆቹን ባጣ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ውስጥ በተስፋቢስ ነትና በሽንፈት ስሜት ተጨነቀ ። ሰው ሠራሽ እጆች ከገቡለት በኋላም ሆስፒታሉን ለቅቆ ፤ ከሰዎች ጋር ተደባልቆ መኖርን እንደጦር ነበር የፈራው ። በእን ዚያ ወራት ውስጥ ቢኖር ፤ ቢሞት ደንታ አልነበረ ውም ።

ከዕለታት አንድ ቀን ፤ ቻርሊ መኩንጋል የተባለ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ሁለቱ እጆቹን ፤ ያጣ ሰው ሐሮልድን ሊጎበኝ ከሆስፒታሉ ከተፍ አለ። ሐሮልድን ጠጋ አለውና ፤«ለገዛ ሕይወትህ ዋን ኛው እንቅፋት አንተው ራስህ ነህ ። ምሬትህንና ፍርሃትህን ማስወገድ አለብህ» ሲል መከረው ።

እጆቹን ማጣቱን አምኖ መቀበል እንዳለበትና ያለ እነርሱ መኖርን እንዲለማመድ አበክሮ አስጠነቀቀው ። ከኢ.መርሰን ጽሑፍ የወሰደውንና ራሱን ያጽናናበትንም አንድ ጥቅስ እንዲህ ሲል አካፈለው ፡— «ለምታጣው አንድ ነገር የምታተርፈው ሌላ ነገር አለ» አለው ፤ ጥቅሱ ለሐሮልድም እንደሚጠቅመው በመገመት ።

አባባሉ ሐሮልድን ወዲያውኑ ረድቶታል ። ግን በቅርብ ቀናት ውስጥ ሆስፒታሉን ለቅቆ ወደ ቤቱ መሔድ እንደሚኖርበት ሰውዬው ሲመክረው ሐሮልድ እንደገና በድንጋጤና በጥርጣሬ ተርበደበደ ። «ምን ላደርግ? እንዴትስ ሆኜ ልኖር?» ራሱን ችሎ ከሌሎች ሰዎች ጋር በእኩልነት ደረጃ መቆሙን ሲያስብ ጭንቀት ተሰማው ።

«በዕእምሮህ ልትቀርፀው የሚገባህ አንድ ነገር አለ ፤ ሐሮልድ» አለው ሰውየው ። «አካለ ስንኩል እንጂ ሽባ አይደለህምኮ!»

«አካለ ስንኩልነትና ሽባነት ልዩነታቸው ምኑ ላይ ነው? ሁለቱም ያው ናቸው» ሲል ሐሮልድ አሰበ ። ግን ናቸው? ልዩነታቸውን ከመዝገበ ቃላት አገኘ ።

«ሽባነት ፥ አንድ ሰው አካሉ ሙሉ በሙሉ ደንዝዞ አንድን ተግባር ለማከናወን ከሚሳነው ደረጃ ላይ መድረሱን» የሚጠቁም ሲሆን ፥ «አካለ ስንኩልነት ግን ፥ አንድ ሰው በአካል ጉድለት

ምክንያት አንድን ተግባር ለማቀላጠፍ ባይችልም ከፍጻሜ ለማድረስ የማይታገድ» መሆኑን ተገነዘበ ። «አሃ! ለካስል ዩኑት አላቸው አለ» በልቡ ።

«ስለዚህ ተስፋ አለኝ! ኑሮን በአሸናፊነት ለመወጣት እችላለሁ! ጉዞዬ አድካሚና አዝጋሚ ቢሆን ብኝም ድል ማድረጌ አይቀርም!» አለ ለራሱ ። የሚፈልገው ምርኩዝ ይኸው ብቻ መሆኑን አጢኖ ቻርሊ መኩንጋል እንደ መከረው ሕይወቱን ከተለየ አቅጣጫ መመልከት ጀመረ ። ከዚያች ወቅት አንሥቶም አዕምሮውን ለዚያ ዓላማና ግብ አስገዛ ። አካለ ስንኩል እንጂ ሽባ አለመሆኑን አመነበት ። ላጣው ነገር ምትክ የሚሆን ሌላ ነገር እንደሚያተርፍ ተማምኖ ትግሉን ቀጠለ ።

ይህ አዲስ አመለካከቱ ምንኛ አስገራሚ ለውጥ አስከተለበት!......ቀስ በቀስ ግን ፣ በአስተማማኝ ሁኔታ ሐሮልድ ራስል ከጨለማ የሐሳብ ባሕር ውስጥ ወጥቶ በድል ብርሃን ተጓዘ ። «ከሕይወታችን ዘመናት አስደሳቾቹ ዓመታት» የሚለውን ፊልም በመሪ ተዋናይነት እንዲሠራ ተመርጦ አድናቆትን አተረፈ። ሁለት የሆሊውድ ከፍተኛ ሽልማቶችን ለማግኘት በቃ ። የሕይወት ታሪኩንም አሳትሞ እንደ ተዋናይነቱ በደራሲነቱም ዝናን አገኘ ። ዝናው እንደርሱው አካለ ስንኩል ለሆኑ ሰዎች ዐይነተኛ ርዳታ እንደ ሚሆናቸው ተገንዝቦም ሊያወሳላቸው ቆርጦ ተነሣ ። በሬዲዮና ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወረ ተሰጥዎቹንና ችሎታዎቹን ለማካፈል ቻለ ።

ስለዚሁ ባስፈረው ጽሑፍ እንዲህ ይላል ።

«ኢመርሰን ይመስለኛል ፡ 'ድክመት በአመዛኙ ጥንካሬም ይሆናል' ያለው ። በሆስፒታል አልጋዬ ላይ ስነቃና እጆቼን ማጣቴን ስገነዘብ ይህን አባባል ለማመን አዳግቶኝ ነበር ። ከዚያ ወዲህ ግን ፡ ደግሜ ደጋግሜ አስቤበት እውነታነቱን ተቀብያለሁ ።

«የኢመርሰን አባባል እምብዛም ልብ የሚስብ ልና አዲስ ነገር እንዳልሆነ ይገባኛል ። ከሰው ልጅ ጋር አብሮ የኖረ ሐቅ ነው ። ኢመርሰንም ፡ እንዲያ ለማለት የመጀመሪያው ሰው እንዳልሆነ እርግጠኛ ነኝ ። ሆኖም ሰው በምድር ላይ እስከሚኖር ድረስ ሊባል የሚችልና መባልም ያለበት ቁም ነገር ነው ። በዚህም አልን በዚያ ምክንያት ፡ እያንዳንዳችን በዕ ድሜ ዘመናችን ቢያንስ ለአንድ ጊዜ በእሳት እንፈ ተናለን ። ቆርጠን ከተነሣንም በአሸናፊነት እንደም ንወጣ እርግጠኞች መሆን አለብን ። አለበለዚያ መቅለጣችን ነው ።

«ማንኛውንም ታሪክ — አልባሌና ከቁጥር የማይገባም ቢሆን — የራሱ የሆነ ትምህርት ወይም ምን ልቦናዊ መልእክት ይኖረው አይኖረው እንደሁ መመዘኑ ተገቢ ነው ። የሰው ሕይወት እንደ ዕቃ ተጠቅልሎ በቀላሉ 'ይህን ይመስላል' ለማለት አይ ቻልም ። ግን ብታምኑኝም ባታምኑኝም ፡ ሕይወቴ የኢመርሰንን ጥልቅና ቋሚ እውነታ ስታረጋግጥ በሚገባ ይታወቀኛል ። እጅ የለሽ በመሆኔ ይጫነኝ የነበረው ድክመቴ ፡ ያ የበታችነት ስሜቴ ከመቼውም የበለጠ ኃይል ለግሶኛል ። ያኔ ግን ፡ ይህ አልተከሰተ ልኝም ነበር ። እጆቼን እንደገና ማግኘት ብችል

በጣም ደስ ባለኝ ! ለዳግመኛ ጊዜ ሊጣቸውም አል ሻም ። ግን እንዴ አጥቻቸዋለሁ ።

«ቢኖሩኝ ደግሞ ዛሬ ያገኘኋቸውን አያሌ ውብ ነገሮች አጣ ይሆናል ። ሀብትን በተመለከተም ፣ ዛሬ ከምንጊዜም በተሻለ ደረጃ ላይ እገኛለሁ ። ቁምነገሩ ያ አይደለም ። ከዚያ እንደ አዘቅት ከሚያስፈራ ጨለማ ሕይወት ያወጣኝን ፣ በገንዘብ የማይተመንና ክቶ ላገኘው የማልችለውን መንፈስ ጠንካራነትን ማግኘቴ ነው ቁም ነገሩ ።

«አስደሳች ሕይወትን የሚያቀዳጅ አቋራጭ መንገድ የለም ። አለ የሚል ቢኖር ይቀልዳል ። ወይ ይዋሻል ። እኔም የተመሰከረለትና እጥር ምጥን ያለ ፣ እንዲህ ነው የምለው የራሴ ዘዴ የለኝም ። ግን አንድ መልዕክት ለማስተላለፍ እወዳለሁ ። ከአጉል ጸጸትና ሽንፈት ለመራቅ እንደሚረዳ ስለ ተገነዘብኩ እንጂ ፣ ያም ቢሆን ፍጹምና አቋራጭ መንገድ ነው ማለቴ አይደለም ። የማካፍላችሁ መልዕክቴም ይኸው—'የታጣው ሳይሆን የተገኘው ነው ለቁም ነገር የሚውለው ።' ብዙዎቻችን ራሳችንን ለእውነታና ባወቅቱ ለሚጠበቅብን ተግባር ከማስገዛት ይልቅ ፣ እምቅ ኃይላችንና ውድ ጊዜያችንን እንዴ ላጣነውና ዳግመኛም ለማናገኘው ጉዳይ እናባክነዋለን ።

«ሞራል ከማንኛውም የሚልቅ ኃይል ነው ።...... ተሸነፈ ፣ አከተመለት ፣ እስከናካቴው

ወደቀ ፤ ደቀቀ — የተባለን ሰው እየቀሰቀሰ መሰናክ ሎቹን ሁሉ በማዘለል ለድል ያበቃል ።»

......የሐሮልድ ራስል ታሪክ በዘመኑ እንደርሱው አካል የገጠማቸውን ሁሉ ውስጣዊ ሕይወት ያዳስ ሳልና«...... እኔም ተስፋ አለኝ!» በማለት ብዙ ሰዎች ተንፈስ ብለዋል ። «እኔም አንድ ቀን ባለድልና ደስተኛ እሆን ይሆናል!......» እንዲሉ አነቃቅቷ ቸዋል ።

ዛሬም መልዕክቱ እያነቃቃ ፤ አካለ ስንኩላን በራሳቸው እንዲተማመኑ ፤ ጥርጣሬያቸውንና ምሬ ታቸውን እንዲያስወግዱ እየረዳቸው ነው ።...... «የታ ጣው ሳይሆን የተገኘው ነው ለቁም ነገር የሚው ለው ።»

በጣም አስቸጋሪው አካለ ስንኩልነትን ማሸነፉ ሳይሆን የሚያስከትለውን የመንፈስ ጭንቀት ማስ ወገዱ መሆኑን ተገንዝቢያለሁ ። ዓለማችን አንድን ሰው የምታስተናግደው ፤ ያ ሰው ለራሱ በሚሰጠው የክብር ደረጃ መጠን መሆኑንም ደርሼበታለሁ ። በአካለ ስንኩልነቱ የሚያፍርና ራሱን ዝቅ የሚያደ ርግ ሰው ከሌሎች የሚያገኘው ያንኑ ይሆናል ። ግን ራሱን ካከበረ በሌሎችም ዘንድ ይከበራል ።

ሚጀር አሌክሳንደር ሴቨርስኪ

(አሌክሳንደር ሴቨርስኪ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት አንድ እግሩን ያጣ ሰው ሲሆን ፡«ድል በአየር ኃይል ክንድ» በተሰኘው መጽሐፉ ታዋቂ ሊሆን በቅቷል ።)

☆ ☆ ☆

ፍርሃትህን ለራስህ በጉያህ ሸሽግ ፤ ወኔህን ግን ከሌሎች ጋር ተካፈል ።

ሮበርት ሉዊስ ስቲቨንሰን

☆ ☆ ☆

ቀደም ያሉት አባቶቻችን የመኖርንና የመሞትን ምንነት አስተምረውናል ። እኛም ወራሾቻቸው መሆናችንን እንዘንጋ ።

ሲድኒ ዳርክ

☆ ☆ ☆

ዴቪድ ግሬይሰን

«.....ዋነኛው የብርታት ምንጩ ሕሊናዬ ነበርና..... አካሌ ምንም ዐይነት ስቃይ ቢደርስ በት መጨነቅ እንደሌለብኝ ተሰማኝ ።»

ሬይ ስታናርድ ቤከር አሳሳቢ ቀዶ ሕክምናውን ጨርሶ በውጋት እያቃሰተ ሆስፒታል አልጋው ላይ ጋደም ብሏል ። ዶክተሮቹ የተቻላቸውን ሁሉ እንዳ ደረጉለትም ያውቃል ። ሆኖም ሥቃዩን ፥ ያን የማያ ቋርጥ ውጋቱን እንዴት ይቋቋመው?

ቤከር ዕውቅ ጋዜጠኛ ፥ ደራሲና የታሪክ ተመ ራማሪ ነበር ። «ዴቪድ ግሬይሰን» በሚል የብዕር ስሙ በሚያቀናብራቸውና የተፈጥሮን ውበት በሚ ገልጹ ጽሑፎቹም ዝናን አትርፏል ።

ቀስፎ በያዘው ውጋት በሚያቃስትበት ወቅት በሕሊናው የሚያውጠነጥነው ተሽሎት እንደ ውት ሮው ቤከር ወይም ግሬይሰን እየተባለ የሚወደውን ሥራውን ለመቀጠል መቻል አለመቻሉን ነበር ። ደወል ጫን አድርጎ አስታማሚውን ጠራትና ውጋ ቱን የሚያስታግሥበት ኪኒን እንድትሰጠው ጠየ ቃት። ለጥቂት ጊዜም ሽለብ አደረገው ፤ ግን ሌሊቱን ሙሉ እንዳቃሰተ ነጋለት ።

ማለዳ ላይ በአትራቢያው ያስቀመጣትን «አስ ላሰል» (ሜዲቴሽን) የተሰኘች አነስተኛ የማርከስ ኦሪሊየስ መጽሐፍ አነሣ ። መጽሐፏ ለብዙ ዓመታት ስታጽናናው የኖረች እንደ መሆኗ በየሔደበት ተለይ ታው አታውቅም ። ወደ አሰመረበትና በቃሉ ወደሚ ወጣው አንድ ገጽ ገልበጥ አደረገ ።

«ልብ እንበል ፤ የሕመም ሥቃይ ክብርን አይቀ ንስም ፡ ወይም የሕሊናን በላይነት አያስረሳም ።

«እንደውም አብዛኛው ዓይነት በሽታ ሊቋቋ ሙት የሚያዳግት ወይም ጨርሶ የማያቋርጥ አይደ ለም ፤ ወሰን ያለው መሆኑን ካልዘነጋንና ከስሜት በሚመነጭ ፍርሃት ካላባባስነው በቀር ።

«ስለ አካላችን እንዳንጨነቅ ሕሊናችንን መግ ራት የምንችል መሆናችንን መገንዘቡ በቂ ነው .....» የሚለውን በጥሞና አነበበ ።

ወደ ሌላ ገጽ ገልበጥ ሲያደርግ ፡ «ማንም ሰው ከአቅሙ በላይ የሚመጣበት ምንም ነገር የለም ፡ የሚደርስበትን ጣጣ እንዲቋቋም አድርጋ ተፈጥሮ ገንብታዋለችና» ከምትል ደግሞ ፡ ደጋግሞ ካነበባት ዐረፍተነገር ላይ ዐይኖቹ ዐረፉ ።

ሐድሰን የተባለ ሰው «ወዲያ ማዶ ፡ በጥንት ዘመን» የተሰኘ ጽሑፉን የደረሰው የአልጋ ቁራኛ ሆኖ ሳለ እንደነበረ ታወሰው ። ለዚያ ሰው ብርታት የሰጠውም ከእርሱ ቀደም ባለ ጊዜ ስቲቨንሰን የተ

ባለው ዕውቅ ደራሲ «የሲሳይ ደሴት» የተሰኘ ተወ ዳጅ ሥራውን ያበረከተው በሳምባ ነቀርሳ በመሰቃ የት ላይ እንዳለ መሆኑን በመገንዘቡ እንደ ነበር ቤክር አንብቧል ። ከነዚህ ተጨባጭ ሁኔታዎች በመንደር ደር በራሱ ደካማነት ተቆጭቶ፣ «ውጋቴን ለመቋቋም የሚያስችለኝ አንድ ዘዴ ማግኘት አለብኝ» አለ ለራሱ ። ማርከስ ኦሬሊየስ ከዘመናት በፊት እንደ ጠቆመው ዓይነት በመንፈስ ብርታት ላይ የሚያተ ኩርና እፎይታን የሚለግስ አንድ ዘዴ መኖር አለበት የሚል እምነት አደረበት ።

በሆስፒታል አልጋው ላይ እንዳለም ፣ የሚሰማ ውን ውጋት ችላ ብሎ የተለመደ የመጻፍ ተግባሩን ለመቀጠል ወሰነ ። ደወሉን ተጭኖ አስታማሚውን ወረቀትና እርሳስ እንድታመጣለት ነገራት ። ያሠፈ ራቸው የመጀመሪያዎቹ ጥቂት መሥመሮችም እፎይ ታን ሰጡት ። መንፈሱን አረጋግቶና ረዘም ላለ ጊዜ ሥቃዩን ዘንግቶ መጻፉን ቀጠለበት ።

«በጐ ነገር ያለ ክፉ ጐኑ ይገጥመናል ብላችሁ ታስባላችሁ?» የምትል ዐረፍተ ነገር ጻፈ ። «ደስታ ያለ ሐዘን ይመጣልናል ትላላችሁ?...... ይፍጠንም ይዘ ግይም ፣ ሰው ምንም ያህል ጥበበኛ ቢሆን መታመሙ አይቀርም ። ይህ ገሃድና የማያመልጡት የሕይወት ገጽታ ነው ። ታዲያ ለመቋቋም የሚያስችለንን አንድ ዓይነት መርሕ ካልጨበጥን ምን ይውጠን!» በማለት ልምዱን ማካፈል ጀመረ ።

ማታ ገደማ ውጋቱ እንደገና ቢቀሰቀስበትም «ማቆሙ አይቀርም ። እንዲህ አይቀጥል ። እስቲ ነገ

ደግሞ ስለምጽፈው ላሰላስል......» እያለ ጊዜውን ገፋው ።

ዘዴው በእርግጥ ሠመረለት ። ሕመሙን እንዴት እንደሚቋቋም ተማረ ።

«ወደ ሆስፒታል በገባሁ ስሞን ቶሎ ቶሎ እየተነሣብኝ ያጣድፈኝ የነበረውን ውጋት እምገታው አልመሰለኝም ነበር ። ለመቋቋም የሞከርኩትም ጥርሶቼን በመንከስ ፣ ጡንቻዎቼን በማፈርጠምና ትንፋሼን በማመቅ ፣..... እንዲህ በመሰለ ጭፍን ትግል ነበር ። ይፈላብኝ የነበረውን እሳት እንዲያ በመሰለው የመንፈስ ብርታት ለማቀዝቀዝ መሞከሬ ያኮራኛል ። ግን በውነቱ ትግሌ የጭንቀት ነበር ። የሕመም ዓይነቱ ብዙ ነውና ለዚያ ሁሉ መከላከያውም እንደሆነ አላውቅም ። በበኩሌ ግን ፣ የደረሰብኝ ህመም የማይቀርልኝ ጣጣ እስከሆነ ድረስ ለዚያ የማፈሰው ጉልበትና በፊቴ ላይ የማንቆረቆረው ላብ እስከናካቴው ኃይሌን አሟጦብኝ ለሞራል ውድቀት እንዳይዳርገኝ ሠጋሁ ።

«'ሕመም ለመቋቋም የሚያዳግት ወይም ጨርሶ የማያቋርጥ አይደለም ።..... መንፈስ ራሱን በራሱ የማረጋጋት ኃይል አለው ።'

«ይህ ነጥብ እንደ ብርሃን ብልጭ ባለልኝ ቅፅበት የማይቀርልኝን ዕዳ በጸጋ ተቀብዬ በጭፍን ልታገለው መፍጨርጨሬን ችላ አልኩኝ ። የበሽታዬ ባሕርይ እንዲያ ከሆነ ሌላ ምን ማድረግ እችላለሁ? በዚህ አዲስ አስተሳሰብ መመራት እንደ ጀመርኩ

በእርግጥ ውጋቴ ሊያቆምልኝ ቀርቶ ጭራሹን እየባ
ሰበት የሚሔድ መሰለኝ ። ውስጥ ውስጤንም ጨረ
ሰኝ ። ግን እንዴ ለራሴው ዕጣ ራሴን በሙሉ ፈቃደ
ኝነት ተካፋይ አድርጌ ሕሊናዬን መቆጣጠሩ መፍ
ትሔ እንደሆነኝ ታወቀኝ ። እንደ ጋለ ብረት የሚሸ
ቀሽቀኝ ውጋትም ወደ ቀድሞው ድካሜ ሊመል
ሰኝ ደግሞ ደጋግሞ ቢፈታተነኝም ፣ ከዚህ አቋሜ
ፈቀቅ ሳልል አንድ መከረኛ ሌሊት አነጋሁ ። ዶክ
ተሮቹ ያዘዙልኝ መድኃኒት ምርጥ ቢሆንም አካሌ
ዛለ ። ሆኖም የራሴው የሆነ አዲስ ፈውስ ማግኘቴ
ብርታት እየሰጠኝ ሔደ ።

«ለተወሰነ ጊዜ በዚሁ እምነቴ ገፋሁበት ።
እያደርኩም በልበ ሙሉነት እየተጠናከርኩ
መጣሁ ።...... ይሰማኝ የነበረው ውጋት ከቀድሞው
መባሱን እርግጠኛ አይደለሁም ። የድግግሞሹን
መጠን መቀነሱን ግን ዐውቃለሁ ።...... ለብርታቴም
ምንጩ ሕሊናዬ ነበር — በጭንቀት በመዋጥ ፋንታ
ሚዛናዊ አስተሳሰብ ለግሶኝ ፣ ያን አስከፊ ሁኔታ
ራሴን በራሴ በመቆጣጠር ለመወጣት ያስቻለኝ ።

«ይህን መርሕ በጨበጥኩ በመጀመሪያዎቹ ሌሊ
ቶችም ‘በአካሌ ላይ የፈለገው ጣጣ ይምጣ ፤ ምንም
አልሆን!’ ማለቴ ይታወሰኛል ።»

ሬይ ስታናርድ ቤከር ተሸሎት ፣ «ዴቪድ ግሬይ
ሰን» በሚለው የብዕር ስሙ ስለ ተፈጥሮ ፣ ስለ ጓደኛ
ነት ፣ ስለ ደስታና እፎይታ አስደሳች መጻሕፍት

ማበርከቱን ቀጠለ ። ይህ ሕመምን የመቋቋም ዘዴ የሚጠቁመው ጽሑፉም የተወሰደው ፣ «በዛሬ ጥላ ሥር» ከተሰኘው መድበሉ ነው ።

የአልጋ ቁራኛ ሆኖ ሳለ የጻፈውና ሕመሙን የተቋቋመበት ዘዴው እንዲ መሆኑ ሥፍር ቁጥር የሌላቸውን ሕሙማንን ረድቷል ። «ማንም ሰው ከአቅሙ በላይ የሚመጣበት ምንም ነገር የለም ፣ የሚደርስበትን ጣጣ እንዲቋቋም አድርጋ ተፈጥሮ ገንብታዋለችና» የሚለውን ፣ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት የተሰራጨውን የማርክስ ኦሬሊየስ ቀስቃሽ መልእክት እንደገና በሚገባ አስተጋብቷል ።

ለሚፈታተነው የነፋስ ማዕበል
ዓይነተኛ ማማ ጉንበስ እንደማይል
ተጠናክረህ ግፋ ፣ አንተም አታዘምብል ።

ዳንቴ

☆ ☆ ☆

አእምሮአችን በአካላችን ላይ ለማመን የሚያዳግት ሥልጣን አለው ።

አንድሬ ሞርዋ

☆ ☆ ☆

ትግል የሚደቀነው ለጉልበተኞች ብቻ አይደለም — ለጥንቁቆች ፣ ለንቁዎችና ወኔ ላላቸው ሁሉ እንጅ ።

ፓትሪክ ሄንሪ

☆ ☆ ☆

ኒውተን ቤከር የተባለ አንድ የአሜሪካ ባለሥልጣን በአንደኛው የዓለም ጦርነት ማግሥት ከባድ የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን ወታደሮች በየሆስፒታሉ እየዞረ ይጐበኝ ነበር ። ሁለት እግሮቹን ፤ አንድ እጁንና ሁለት ዐይኖቹን ቢያጣም ፣ ብሩህ ገጽታና የጋለ መንፈስ ሳይለየው በተሽከርካሪ ወንበር ላይ ተቀምጦ የሚንሸራሸር አንድ ሰው በአንድ ሆስፒታል ውስጥ በድንገት አጋጠመው ። ያ ሰው በሕይወት ይቆያል ብሎ የገመተ አልነበረም ።

ከጊዜ በኋላ ቤከር በዚያው ሆስፒታል የነበረ አንድ ሌላ ሰው አገኘና ፤ «ለመሆኑ ያ የአካል ጉዳተኛ በሕይወት አለ?» ሲል ጠየቀው ።

«በሕይወት አለ? በሚገባ እንጅ! አስታማሚውን አገባትኮ!» አለው ። ቤከር የጀመረውን ነጥብ ችላ ብሎ የፍቅርን ኃያልነት እያሰላሰለ ጉዞውን ቀጠለ ።

ጥቂት ዓመታት እንዳለፉም ፤ቤከር የጆን ሆፕኪንስ ዩኒቨርሲቲ የበላይ ጠባቂ ሆኖ ሳለ ከዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት አንድ ደብዳቤ ደረሰው ። ዩኒቨርሲቲው ከከማቻቸው ዕውቅ ሥራዎች ጋር የሚዳመር ግሩም ተግባር ላከናወነውና ከባድ የአካል ጉዳተኛ ለሆነ አንድ ሰው — ያውም በግማሽ ሴሚስተር ላይ- የዶክተር ኦፍ ፊሎዞፊ ዲግሪ ቤከር ተገኝቶ እንዲያበረክት የሚጋብዝ ነበር ፤ ያ ደብዳቤ ። በዚያ ደብዳቤ ውስጥ የተጠቀሰው ስም የዚያ የጦር ጉዳተኛ ቢሆንም ቤከር ተጠራጥሮ ሊያረጋግጥ ሞከረ ። አዎ ፤ ያው ሰው ሆነ! ሁለት እግሮቹን ፣ አንድ እጁ

ንና ሁለት ዐይኖቹን ያጣው ያ ሰው ለካስ የዓለማች ንን ችግር ከሚያባብሱት ሳይሆን ከሚያሻሽሉት መሐል አንዱ ለመሆን በቅቷል ።

ሁሉም አካለ ስንኩላን እንዲህ ለመሰለ የድል ውጤት ይበቃሉ ማለት አይደለም ። ግን ወኔ ፣ እን ዲህ ያለው የማይበገር ወኔ ፣ ሙሉ አካልና ጥንካሬ ያለንን ሁሉ ቀበቶዎችንን ጠበቅ አድርገን ተግባ ራችንን በጋለ መንፈስ እንድንገፋበት ያበረታታናል።

ሄሬ ፎስዲክ

☆ ☆ ☆

ሜሪ ሮበርትስ ራይንሃርት

«ከካንሰር በሽታ አብዛኞቹ ዓይነቶች ምንም አያስ ፈሩም — ምንም ፡ ከመዘግየት በቀር!»

ቃለ ምልልሱ የተካሔደው በሁለት ሴቶች መካከል ነበር ፤ ጠያቂዋ ጋዜጠኛ ፡ መላሿ ደግሞ ዕውቅ ደራሲ ።...... በስሙ ብቻ ሰውን ስለሚያሸብረውና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ስለሚያስጨንቀው ካንሰር ስለሚባለው በሽታ ነበር ውይይታቸው ። ከዚህ በሽታ ፈውስ ያገኙት እንኳን ቢሆን ስለምን ነቱ በየሆዳቸው አምቀው በምስጢር ይይዙታል እንጂ ስሙን ሊያነሡ አይፈልጉም ። እንደገና እን ዳያገረሽባቸው የሚሠጉ ይመስላሉ ።

«አዎ ፡ ካንሰር ይዞኛል » አለች ሜሪ ያላን ዳች ፍርሐት ፡ ልክ ስለ ራስ ምታትና ስለ ጉንፋን እንደምታወጋ ሁሉ ።

ግድግዳው በመጻሕፍት የተለበጠ የሚመስለው ክፍሏ የፍሬያማ ሕይወት ማዕከል ነበር ። የምትሠራበት ጠረጴዛ በወረቀቶች ተጣብቧል ።በዚያንወቅትም አንድ ልቦለድ ሥራ በማጠናቀቅ ላይ ነበረች ። ሊጠይቋት በየሰዓቱ ብቅ የሚሉ እንግዶቿን የምታ

ስተናግድባቸው የሻይ ስኒዎችም በአትራቢያዋ ከሚ ገኝ አንድ አነስተኛ ጠረጴዛ ላይ ተኮልኩለዋል ያች ሽንቅጥና ውብ ወይዘሮም ትኳኩላና አሽብርቃ እንደ ጤናማ ሰው ትፍለቀለቃለች ። በዶራሲነቷም ሌሎች የተቀዳጁትን ማዕረግ ደርሳበት ስለነበር በደ ስታ ተውጣለች ።

«አዎ ካንሰር ይዞኛል ።»

«ታዲያ ስለዚህ በሽታሽ ልታዋይኝ ፣ ስሜት ሽን ለሌሎች ለማካፈል ፈቃደኛ ነሽ?» ስትል ጠየ ቀቻት ጋዜጠኛዋ ።

«ደስ ይለኛል» በማለት መለሰችላት ሜሪ ። «ይህ በሽታ ስሙ እንኳን መነሣት የለበትም በሚል አጉል እምነት ሰዎች ለብዙ ዘመናት ሲደብቁት ቆይተዋል ። የካንሰር በሽታ በአመዛኙ ለሞት አያበ ቃም ፤ መፍራት ፣ መሸሸግና ፣ ማዘግየ እያባኙባሱት እንጅ ። ልምዴ ሌሎችን የሚረዳ እስከሆነ ፣ በሽታ ቸውን በወኔ ለመቋቋምና ሕይወታቸውን ያለጭንቀት ለመምራት እስካስቻላቸው ድረስ ዝም ማለት የለብ ኝም ።

«በአስቸጋሪ ወቅት የግላችን የምናደርገው ምንም ነገር የለምኮ!» ስትል ሜሪ አስተያየቷን ቀጠለች ። «ሐዘናችንንና ሥቃያችንን እንኳ በየልባ ችን ጓዳ ሳናምቅ ይፋ ለማውጣት የምንገደድበት ጊዜ አለ ።

«ካንሰር ከትክትክና ከጨጓራ መቁሰል በሽታ ዎች ይበልጥ አስከፊ ተደርጐ የሚታይበት ምክንያት

አይገባኝም ። ከሁሉም በበለጠ እንደሚሰቀጥጥ በሽታ የሚቆጠርበትን ምክንያት አልቀበለውም ።

«ካንሰር ከበሽታዎች ሁሉ የሚያስከፋ ቢሆንማ በቤተሰብና በወዳጆቼ ዐይን እኔም አስጠሊታ ፍጡር ሆኛለሁ ማለት ነውኮ! ካንሰር ከያዘኝ ቆይቷል ። ይህንንም ገና ድሮ ዐውቄዋለሁ ። ዛሬ ከበሽታዬ ሙሉ በሙሉ ፈውስ አግኝቻለሁ ለማለት አፌን ሞልቼ ባልናገርም የግሌ አድርጌው በልቤ ጓዳ የደበቅሁበት ጊዜ ፈጽሞ የለም ።

«ካንሰር ከፉኛ ያስደነገጠኝና ሆደ ባሻ ያደረገኝ ፤ ያለ የሌለ ኃይሌን ሊያሟጥጥብኝ የቃጣው ዱብዳ ነበር ። አሳሳቢነቱ አሌ አይባልም ። በካንሰር በሽታ ኦፕራሲዮን መሆንን እንደ ቀላል ነገር ማየት እውነትን መሸፋፈን ነው ። የብዙ ሰዎችን ሕይወት በሚቀሥፍ በዚህ በሽታ መጠመድን ማውጠንጠኑ አካል ይጨርሳል ። ታዲያ ዋነኛ መፍትሔው አእምሮን መግዛትና መንፈስን መቆጣጠር ነው ።

«ካጋጠሙኝ ከሌሎች እክሎች ጋር ሳነጻጽረው በካንሰር በሽታ ኦፕራሲዮን መሆንን ከሁሉም የባሰ ጣጣ አድርጌ አላየውም ።...... ሌሎች እንደሚገምቱትም ቅስሜን አልሰበረውም ። እስኪ ተመልከችኝ ፤ ሕይወቴ አክትሞላታል?

«በጭራሽ!...... ከካንሰር በሽታ አብዛኞቹ ዓይነቶች ምንም አያስፈሩም ፤ ምንም ፤ ከመዘግየት በቀር!»

«ሜሪ ሮበርትስ ራይንሃርት በካንሰር በሽታ አፕራሲዮን በሆነች በዓመቷ አንድ መጽሐፍ አሳትማለች ። ከዚያም ወዲህ ሌሎችንም ደርሳለች ፤ ብዙ አገሮችንም ጐብኝታለች ።...... አፕራሲዮን መደረጓ ለጊዜው ቢያስደነግጣትም ቅስሟን አልሰበረውም ። ተግባሯን እርግፍ አድርጋ ባካበተችው ዝና ብቻ መኩራራትም አልፈለገችም ። ወይም ራሷን በሐዘን ስሜት አሽማቅቃ የመንፈስ ሽባ አልሆነችም ።

«እያንዳንዱ የሕይወት መሰናክል እንደ መልካም አጋጣሚ ወይም ለእድገት እንደሚያመች አዲስ ትልም መታየት አለበት» የሚል እምነት ነበራት ። ይህንኑም እምነቷን የሕይወቷ መመሪያ አድርጋዋለች ።...... ይህ እምነቷ ለሌሎችም ወኔንና ተስፋን እየለገሳቸው የሚገጥሟቸውን ፈተናዎች በልበ—ሙሉነት እንዲቋቋሙ ረድቷቸዋል ።

«የምን ተስፋ መቁረጥ!» በልና ተነሣ ፤
ሕይወት መኾርኰርኰሯን በፍጹም አትርሳ ።
ችግር ሲደራረብ ፣ መከራ ዐይኑን ሲያፈጥ ፣
መፈክርህ ይሁን — «የምን ተስፋ መቁረጥ!»

ማርቲን ታፐር

☆ ☆ ☆

ሮበርት ፋልከን ስኮት

«ደህና ሁኑ ። ስንብቴን አልፈራውም ። »

ነፋሱ ያለማቋረጥ የሚያፏጭበትንና በረዶ የተ ነጠፈበትን አውላላ ሜዳ ሲያቋርጡ ትክ ብሎ ለሚ ያያቸው ጥቁር ነጥቦች ይመስላሉ ። በበረዶው ነጸ ብራቅ ታውረውና በውሽንፍሩ ደንዝዘው በዝግታ ፡ በጣም በዝግታ ሲንከላወሱ ከሰንበት በኋላ ቀጥ ለሉ ። በዚያ በረዶ በተከመረበትና ውሽንፍሩ በሚጋ ረፍበት ሕይወት አልባ ዓለም ድንኳናቸውን ተከሉ ። በሕይወት የመቆየት ተስፋቸው የደበዘዘ ሕልም መሆኑን ልባቸው ቢያውቀውም ፡ እርስ በእርሳቸው ለመጽናናትና ለመደጋገፍ ጥረት አደረጉ ።

ሮበርት ፋልከን ስኮት የተባለው አገር አሳሽ አራት ሰዎች አስከትሎ የምድርን ደቡብ ዋልታ ለመጐብኘት ተነሣ ። አምስት ሆነውም ያንን የማይ ታሰብ ፡ ከባድ ፈተና የሞላበት የብቸኛ ጉዞ ለብዙ ወራት ተጋተሩት ። ደቡብ ዋልታን ለመርገጥ የመ ጀመሪያዎቹ ሰዎች እንደሚሆኑ በነበራቸው ተስፋ እየታገዙ ትግላቸውን በቆራጥነት ተያያዙት ። ግን ከዚያ ሲደርሱ ያልጠበቁት ምሬት ጠበቃቸው ። በጣም ዘግይተዋል ። አማንድሰን የተባለ ኖርዌጂያዊ አገር አሳሽ ለካስ ቀድሟቸው ስሙን አስከትቦ ባለድ

ልነቱን አስመዝቧል ። ቅስማቸው ተሰብሮና ከልባ
ቸው አዝነው የመልስ ጉዞዋቸውን ጀመሩ ።

ወደ ሥለጠነው ዓለም ሲመለሱ የገጠማቸውን አስከፊ ፈተና ለመቋቋም ያሳዩት ወኔያቸው ፥ ከሕ
ሊና የማይፋቀውና ጥልቅ የሆነው የወንድማማች
ነት ፍቅራቸው ከዘመናችን ዕውቅ ቀስቃሽ ታሪ
ኮች አንዱ ሊሆን በቅቷል ። ለሳምንታት በብርድና
በነፋስ እየተንገዋለሉ ፥ ድካም ፥ ረኃብና ሕመም
እያንጠራወዛቸው በዚያ በመከራ ጐዳና ቃተቱ ።

ከመካላቸው አንዱ ደከመ ሊያበረታቱት
ሞከሩ ፤ ግን ተሸንፈና በሞት ተለያቸው ። ሌላ ጓደኛ
ቸው ደግሞ ጉዳት ደረሰበትና ለተቀሩት ሸክም ከም
ሆን ብሎ እያዘገመ ተለይቷቸው በበረዶ ውሽንፍር
ተውጦ ቀረ ።

የተረፉት እያቃሰቱና እየተንገዳገዱ ፥ አንዱ
ሌላውን እየደጋገፈ ጉዞዋቸውን ቀጠሉ ። በመጨረ
ሻም ፈቀቅ ሊሉ ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ደረሱና
ድንኳናቸውን ተከሉ ። አየሩ እንደሚሻሻልላቸው
ምኞት ነበራቸው ፤ ግን እየባሰበት ሔደ ። ሌት ተቀን
የሚያፏጭባቸው ነፋስ ባሉበት አስሮ አስቀራቸው ።
ነዳጃቸውን አንጠፈጠፉ ፤ ምግባቸውን አሟጠጡ ፤
ማከተሚያቸው ተቃረበ ። ተራ በተራ መሰናበታቸ
ውን ተገነዘቡ ።

ካፒቴን ስኮት የሥቃይና የሐዘን ጉዞውን እንደ
ተቋቋመው ሁሉ ሞትንም በድፍረት ተቀበለው ።
በብርድ ተጨብጦና ጣቶቹ ተቆልፈውበት ብዕር

ለመጨበጥ ቢሳነውም ፣ እንደ ምንም ብሎ የመጨ ረሻ ሀቅታውን ለዓለም ሕዝብ እንዲሆ ሲል አስ ተላልፏል ።

«በጉዞዋችን ፍጻሜ አላዝንም ። ገና ስንጀምረው እክል እንደሚገጥመን ገምተናል ። ስለዚህ አሁን እምንመረርበት ምንም ምክንያት የለንም ። የሚደርስ ብንን ችግር ሁሉ እየተቋቋምን እቅማችን እስከ ፊቀ ደልን ድረስ ለመታገል ቆርጠናል ። ልንዘልቀው ብን ችል ጥረታችንና ወኔዎችንን በዝርዝር እያወጋሁዋ ችሁ እንጀታችሁን ባንሰፈስፍኩት ። ግን......ቀሪ ውን......ሬሣዎቻችንና ይህች ማስታወሻ ያውሷችሁ» ይላል ትቶት የሔደው መልእክቱ በከፊል ።»

በካፒቴን ስኮት ማስታወሻ ደብተር ውስጥ በመ ጨረሻ ገደማ የሰፈሩት ቃላት ፣ «አበቃልኝ ። ከእን ግዲህ ወዲያ ለመጻፍ የምችል አይመስለኝም»...... የሚሉ ነበሩ ፤ ጣቶቹን በመጠኑ ለማንቀሳቀስ እንኳ ጣር እንደ ሆነበት ሲጠቁሙ ። ቀጥሎም ራሱን ችላ ይልና ስለቤተሰቡና ከጉኑ ስለ ወደቁት ጓደኞቹ ቤተ ሰቦች አሰብ አድርጎ ፣ «ቤተሰቦቻችንን አደራ!» በማለት ይማፀናል ። መደምደሚያውም ይኸው ነበር ፣ ቆፈን ከሸመቀቃቸው ጣቶቹ ብዕሩ ለዘላለም ሳያመልጠው በፊት ያሰፈረው መልዕክት ።

ካፒቴን ስኮት ከተዋቸው ወኔን ከሚቀሰቅሱት መልዕክቶች ሁሉ ለጓደኛው ለሰር ጀምስ ባሪ የጻፈው ደብዳቤ ይበልጥ ልብ የሚነካና የማይዘነጋ ነው ። ስኮትና ጓደኞቹ በረኃብ እየጠወለጉና በአንታርክቲክ

ውሽንፍር እየተገረፉ ሞትን በደቂቃዎች በሚጠባ በቁበት ወቅት የተጻፈ ደብዳቤ መሆኑን እናስተውል ።

«በአንድ አስቸጋሪ ቦታ ላይ ሠፍረናል ። ይህች ደብዳቤ ከአንድ ሰው እጅ ገብታ እንደምትደርስህ በማመን የስንብት ቃሌን ጽፌልሃለሁ ። እስከ መጨረሻዋ ደቂቃ በልበ ሙሉነት እየታገልን ለሞት መዘጋጀታችንን ልናሳውቅ እንሻለን ። የደቡብ ዋልታን በመርገጥ ግባችንን ለማሟላት የተቻለንን ሁሉ ማድረጋችንም ይታወቅልን ።

«ደህና ሁን ። ስንብቴን አልፈራውም ። ግን በእቅድ የያዝኩትን የወደፊት የፍሥሐ ዘመኔን ማጣቴ ይቆረቁረኛል ።......በሞት አፋፍ ላይ ነን ። እግሮቻችን ቀዝቅዘዋል ።...... ነዳጅ የለንም ፤ ምግባችንም ተሟጥጧል ። ግን በድንኳናችን ተገኝተህ እንጉርጉሮዋችንንና ቀልዶቻችንን ብትሰማ ምንኛ በተደሰትክ!

«መጨረሻችን ተቃርቧል ። ግን መንፈሳችን ገና አልጨለመም ። ራሳችንን ለመግደል አስበን ነበር ። ሆኖም የተለመደውን ዕጣችንን ለመጠበቅ ወስነናል ። በጓደኝነት አስበኝ ።...... ውድ ጓደኛዬ ሆይ! የሚስቴንና የልጄን ነገር አደራ እልሃለሁ!»

......ሮበርት ፋልከን ስኮት የሞተው ዓላማውን አሟልቶ ነው ። የመጀመሪያው ሰው ባይሆንም የምድርን ደቡብ ዋልታ ረግጧል ። ስለዚያው ጉዞው ያጠናቀራቸው ማስረጃዎችም ፣ ዛሬ ስለ አካባቢው የሚደረ

ገውን ጥናትና ምርምር አዳብረዋል ። ግን ከሁሉም የሚበልጠውና ዘለቄታነት ያለው ገጽ በረከቱ በከፍ ተኛ የሥቃዩ ወቅት ከሞት ጋር ከሚደረገው ፍጥሚ እኳያ የሰው ልጅ ወኔና የመንፈስ ጥንካሬ ምን እንደ ሚመስል ማሳየቱ ነው ።

ፈሪዎች ሳይሞቱ ፣ ሲሞቱ ሲኖሩ መልሰው መላል ሰው ፣
ጀግና ግን ፣ የሞቱን የሞተለታ ነው ጣዕሙን የሚቀ ምሰው ።
በጣም ይገርመኛል ሰዎች መፍራታቸው ፤
ሞት የማታ ማታ ፣ ለተፍጻሚ ኩሉ ፣ መምጣቱ እን ደማይቀር እየታወቃቸው ።

ተገኘ በቀለ

(ዩልዮስ ቄሳር ፣ ኮከብ ጽባሕ ማ/ቤት—

አሥመራ ፣ በ1949 የታተመ የሼክስፒር ትርጉም ሥራ)

ክፍል ሦስት

ጥረትና ውጤታማነት

«ዛሬ ልታከናውነው የምትችለውን ተግባር በምንም
አኳኋን ለነገ አታሳድር ።»

ሎርድ ቼስተርፊልድ

ውጤታማነት ከሰው ልጅ መሠረታዊ ግቦች ዋነኛው ነው ። የደስታ ምንጭነቱም አያጠያይቅም ።

«ውጤታማነት የአዕምሮንና የአካል ጥንካሬን ፣ የሥራ ፍቅርንና ትዕግሥትን ይጠይቃል» ሲል ኤመርሰን 'በራስ መተማመን' በተሰኘው መጣጥፉ ውስጥ የሰነዘረው አባባል ሥፍር ቁጥር በሌላቸው ሰዎች አዕምሮ የሚመላለስ ነው ።

«ብዙ የጽጌረዳ አበቦች ለመሰብሰብ ከፈለግን ብዙ የጽጌረዳ ዛፎች መትከል ይኖርብናል» ብላለች ጆርጅ ኢሊየትም የውጤታማነትን ምስጢር ስትገልጽ ።

«በቅድሚያ የሥራህን ምንነት ተገንዘብ ፣ ከዚያም ሸንጥህን ገትረህ ተያያዘው ...... ሥራ ሕይወት ነውና» እንዳለው ቶማስ ካርላይል ። የሚከተለውም ግጥም ይህንኑ ሐቅ የሚያጕላ ሆኖ እናገኘዋለን ።

በልቦናህ ማኅደር ዛሬን ቀን አኑራት ፤
ምኑን ሕይወት ብቻ—የሕይወት ሕይወት ናት ።
የጉዞ ርቀቷ ምንም አጭር ቢሆን —
 የዕድገት እልልታህን ፣
 የትግል ችቦህን ፣
 የድል አክሊልህን ፣

አቅፋ ትንንጉዳለች እውኑ አንተነትክን ።
ትናንት እንደሁ ዐልፋ ሆናለች ትዝታ ፤
ነገም ራዕይ ናት የምኞት ብልጭታ ።
ግን የዛሬዋ ዕለት በወግ ከተያዘች ፣
እያንዳንዷን ትናንት በውል ታደምቃለች ፤
ነገንም በተስፋ ቦግ ታደርጋለች ።
ለማለዳ ስማይ አቅርበህ ሰላምታ
የዛሬዋን ዕለት ተጠቀምባታ!

ካሊዳሳ

ጥረትንና ውጤታማነትን አስመልክተው ሌሎ ችም ምን እንዳሉ በሚከተሉት ገጾች ላይ እንመል ከት ።

☆ ☆ ☆

ጆውኩይን ሚለር*

«እንደሚያፏጭ ሰይፍ በሚያስፈራው ቃሉ ፣ ኮስተር ብሎ አላቸው ቀጥሉ! ቀጥሉ! አሁንም ቀጥሉ!»

ኮለምበስ የአትላንቲክ ውቅያኖስን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያቋርጥ ያጋጠመውን ችግር በማስታወሻ ደብተሩ ላይ ያሰፍር ነበር ። «እንዲህ ያለ ጣጣ ገጥሞን ፣ በእንዲህ ያለ መንገድ መክተናው ፣ በዚህ ቀን ጉዞዋችንን ቀጠልን ......» እያለ ኮለምበስ ያሰፈራቸውን ቃላት ጆውኩይን በተመስጦ ያነብባል ። መርከበኞቹ ተስፋ በመቁረጥ በየዕለቱ እያንገራገሩ እንዴት ያውኩት እንደ ነበርና ኮለምበስም በወኔ «ቀጥሉ! ቀጥሉ! አሁንም ቀጥሉ!» እያለ እንዴት ይመራቸው እንደ ነበር ወለል ብሎ ታየው ።

ጆውኩይን ሚለር ዐይኖቹ እየተንቦገቦጉና ጭንቅላቱ እንደ እሳት እየጋለበት ከተቀመጠበት ተነሥቶ ይንጐራደድ ጀመር ። የኮለምበስ መርከቦች በማዕበል

---

* ደምበኛ ስሙ ሲንሲናስ ሃይነር ሚለር ነበር ። ጆውኩይን ሙሪየታ ለተባለ ሜክሲካዊ 'ሽፍታ' አጋር በመሆኑ «ጆውኩይን» የሚለውን ቅጽል ስም አትርፎየብዕር ስሙ አደረገው ።

ተጉድተው ፤ መርከበኞቹም ለዓመፅ ተነሣሥተው ችግራቸው እየተባባሰ ሲሔድ.....ኮለምበስ ግን፡ ተስፋ በመቁረጥ ፈንታ በዓላማው ጸንቶ ከዕለት ወደ ዕለት መጉልበቱ ፤ ለአደጋና ለረኃብ ፤ ለበሽታና ለሞት ቢጋለጡም ግባቸውን ባለመዘንጋት ጉዞዎቸውን እን ዲቀጥሉ ማድረጉ ጆውኮይንን በእጅጉ አስገረመው። «ምን ዓይነት ትዕግሥት ቢኖረው ነው!» ሲል አሰበ ።

«.....ቀጥሉ!.....ቀጥሉ!.....» የሚሉት ቃላት በጆ ውኮይን ሚለር ሕሊና ደግመውና ደጋግመው ያቃጭሉ ጀመር ። እነኮለምበስ ወደሚንሳፈፉበት አትላንቲክ ውቅያኖስ በሐሳቡ ዘለቀ ። የማዕበሉ ማስገምገም ተሰማው ፤ የውቅያኖሱ ጨው ጉንጮቹን ቆጠቆ ጠው ፤ የኮለምበስ ጀግንነት በሠራ አካላቱ ሠረፀ በት ። ለቆራጥነቱም ግጥም ሊደረድርለት ብዕሩን ከወረቀት አገናኝቶ ወኔ ቀስቃሽ ቃላትን አመነጨ ። ከቀየሰው አቅጣጫ ፊቱን ሳያዞር በዓላማው ለጸናው ለዚያ ዕውቅ ባሕረተኛ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ግጥ ሙንም «ኮለምበስ» የሚል ርዕስ ሰጠው ።

ኮ ለ ም በ ስ

ወደ ኋላ ቢያዩ ባሕሩ ተንጋሏል ፤
ወደፊት ቢቃኙ ያው ባሕር ተንጣሏል ።
መርከባቸው ገፋች ጉዞዋቸው ቀጠለ ፤
ግና ፍርሃት ውጦት መንፈሱ የዛለ
ከመካከላቸው አንዱ ብድግ አለ ፡—
«የፈጣሪ ያለህ! ኧረ ምን ይሻላል?
ብርሃን ደብዛው ጠፍቶ ጨለማ ውጦናል »
ብሎ ቢዘላብድ አቋርጦት በመኻሉ ፤

«ቀጥሉ! ቀጥሉ! አሁንም ቀጥሉ!»
አለዋ ኮሎምበስ በሚያስፈራው ቃሉ ።
መርከበኛው ፊዝዞ አፉን እያበሰ ፤
ኮሎምበስን አለው እያለሳለሰ ፦
«ሰዎቹ እንደሆኑ ማመፅ ጀምረዋል ፤
አካላቸው ዝሎ ፤ አጥንታቸው ገጧል ።
ነገ ማለዳ ላይ የብስ ሳናይ ብንቀር ፤
ምን እንደምላቸው ንገረኝ — በእግዚአብሔር!»
«ታዲያ ምን ቸገረህ? ምንስ ያደርጋሉ?
ብለህ እዘዛቸው 'ቀጥሉ! ቀጥሉ! አሁንም ቀጥሉ!»
ሔደች መርከቢቱ በነፋስ ተገፍታ ፤
መርከበኛው አለው እያመነታታ ፦
«ነፋሱ እንደሆነ አቅጣጫውን ስቷል ፤
እግዜርም አላየን እንገር ጥሎ ጠፍቷል ።
ኧረ አንድ ነገር ባል! አለቅንኮ ጌታው!
ከዚህ ሰጥመን ብንቀር ፈጣሪ እንኳ አያውቀው ።»

ምላሹ ያው ሆነ ፤ አልቀየረም ቃሉ ፤
ብሏቸው ዐረፈው — «ቀጥሉ! ቀጥሉ! አሁንም ቀጥሉ!»
ነጐዱ ወደፊት ፤ ሔዱ ጭልጥ ብለው ፤
መርከበኛው አለው ትንፋሽ እያጠረው ፦
«ዛሬስ ይኸ ባሕር ጥርሶቹን አግጧል ፤
አፉን ወለል አርጎ ሊውጠን አድብቷል ።
ሊነክሰን ከጅሎት ያፋጫል ጥርሶቹን ፤
ምናርጉ ትላለህ ሲጨልም ተስፋችን?»
እንደሚያፏጭ ሰይፍ በሚያስፈራው ቃሉ ፤
ክስተ፣ ብሎ አላቸው ፤ «ቀጥሉ! ቀጥሉ! አሁንም ቀጥሉ!»

ኮለምበስ ቢዝልም ጠውልጐ እንደ ቅጠል ፤
አሻግሮ እየቃኘ መለስ ቀለስ ሲል ፤
የብርሃን ጭላንጭል ጽልመቱን ስንጥቃ ፤
ድንገት ከዐይኑ ገባች ከአድማስ ላይ ፈንጥቃ!
ጨለማው ተገፍፎ ፀሐይ ስትወጣ ፤
ባሕሩ እየሟሸሸ የብስ ጐልቶ መጣ!
የወኔው ነበልባል ፤ የዓላማው ውሉ ፤
«ቀጥሉ! ቀጥሉ!.....» የሚል መሪው ቃሉ ፤
ታላቅ ትምህርት ነው ላስተዋለው ሁሉ ።

«ኮለምበስ» ከጆውኩይን ሚለር ግጥሞች መካ ከል በጣም ታዋቂውና ተወዳጅም ነው ። በቀስቃሽ ነቱ አድናቆትን ያተረፈለት ፤ ትልግና ተስፋ የሚን ጸባረቅበት ፤ መልዕክቱም ፤ «ወኔና ትዕግሥት ካሏችሁ ግባችሁን ትመታላችሁ ። ዓላማ ይኑራችሁ ። የመ ጣው ቢመጣ እጃችሁን አትስጡ — ግፉበት ። ፈጠ ነም ዘገየም ፤ ድል የእናንተው ይሆናል» የሚል ነው ።

የየዕለት ዕቅዴን ልወጣው በተግባር ፤
በማሳ ላይ ይሁን ወይ እልም ካለው ዱር ።
ብረት ማንጠር ይሁን ወይም ሸማኔነት ፤
የየዕለት ተግባሬን ልወጣው በትጋት ።
ከቢሮዬ ልዋል ስሥራ በርጋታ ፤
ወይ አራዳ ልግባ ካለበት ጋጋታ ።
የሚያደናቅፍ ኃይል ቢገጥመኝ እንቅፋት ፤
ወደኋላ አልልም እንደዚህ ከማለት ፤

«ሞያዬ ነውኮ ለእኔ መመኪያዬ ፤
መከበሪያዬ እንጅ አይደለም መጥፊያዬ ።
ራሴው ነኝና ጠንቅቄ የማውቀው ፤
ተዉኝ እባካችሁ እኔው ላሰማምረው ።»
ይህን ካወሳልኝ አጣርቶ እንደበቴ ፤
ይመሰክራሉ ጠንካራው መንፈሴ ፤ ትኩሱ ጉልበቴ ።
እያንዳንዷን ሰዓት ሸኝቼ በደስታ ፤
ጀንበር ስትገባ ተንፍሼ በርካታ ፤
መኝዝ ጀምራለሁ በንጹሕ ሕሊና ፤
ፍቅርን ተሳብሽ ላርፍና ልዝናና ።

ሄንሪ ቫን ዳይክ

☆ ☆ ☆

ጤና እማገኘው የድንጋይ መፈልፈያ መሣሪያዬን ስጨብጥ ብቻ ነው ።

ማይክል አንጀሎ

☆ ☆ ☆

ታላላቅ ተግባራት የሚከናወኑት በጉልበት ሳይሆን በትዕግሥት ነው ።

ሳሙኤል ጆንሰን

☆ ☆ ☆

ትዕግሥት የውጤታማነት አስኳል ነው ። ረዘም ላለ ጊዜ ጫን እያደረገ በር የሚያንኳኳ እንግዳ ከቤቱ ኗሪው አንዱን መቀስቀሱ አይቀርም ።

ሄንሪ ዎድስዎርዝ ሎንግፌሎ

☆ ☆ ☆

አርኖልድ ቤኔት

«ማለዳ ስትነሱ ልብ በሉ! ከሀብት ሁሉ የሚ ልቁት ሐያ አራት ሰዓታት የናንተው ናቸው......»

በለንደን ከተማ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ ገቢ በሚ ተዳደርበት ወቅት አርኖልድ ቤኔት አንድ ሕልም ነበረው ፤ ስመጥር ደራሲ የመሆን ። ከዚያ ግቡ እን እንዴት እንደሚደርስም ነጋ ጠባ ያሰላስል ነበር ። ራሱን በሚገባ እየመዘነና ለዚያ ሞያ የሚያበቃውን ንም መሠረታዊ ዕውቀት ባላሰለሰ ጥረቱ አካብቶ እንደ ተመኘው ሁሉ ደራሲ የሚባልበት ጊዜ መጣ ።

ጊዜ የሕይወት ክቡር አስኳል ፤ ጊዜ ከምንም የምትበልጥ የሕይወት ደም ሥር እንደ ሆነች ተገን ዝቦና እያንዳንዷን ሰዓት እንዴት እንደሚያጠፋት መዝግቦ ጊዜውን በሚገባ በመጠቀሙ ፤ ራሱንም ለተነሣበት ዓላማ በማስገዛቱ ነበር ሕልሙ የሠመረ ለት ።

ከማይነጥፈው ብዕሩ በየጊዜው የሚያፈልቃቸው ጽሑፎቹ ጠረጴዛውን እስከ ማጣበብ ደረሱ ። ብሩህና አመርቂ የሆነ የደራሲነት ዘመኑን በጋለ መንፈስ ተያያዘው ። ጊዜን በአግባቡ መጠቀምን ልምድ አድርጓልና እንደውም ጊዜ እየተረፈው የሥዕል

የሙዚቃና የቲያትር ዝንባሌዎቹን ለማዳበርና መንፈሱን ለማደስ ፣ ጓደኞችም ለማሰባሰብ ቻለ ።

ታዲያ እንዲያ ያለውን የሕይወት ዳገት ወጥቶ ታዋቂነቱን ባስመሰከረ ማግሥት ፣ «እንዴት ይህን ሁሉ ማድረግ ትችላለህ? ጊዜስ ከየት ታገኛለህ?» የሚሉ ጥያቄዎች ይጐርፉለት ጀመር ።

«ጊዜ ከየት ታገኛለህ!»...... ይህን ጥያቄ መስማት አርኖልድ ቤኔትን ያበሳጨው ነበር ። «ጊዜ ከየት ታገኛለህ የሚሉ ፈሊጥ!» ይሳል በመገረም ። «ሁሉም ሰው እኩል ጊዜ አለው—ሐያ አራት ሰዓታት ፤ ለአንዱ አይበልጥ ፣ ለአንዱ አያንስ! ልዩነቱ የሚመነጨው ከአጠቃቀም ነው ። ውድነቷን ተገንዝበ እያንዳንዷን ሰዓት በዋዛ አለማባከን ። ሰዎች ገንዘባቸውን በበጀት መልክ እንደሚይዙት ሁሉ ጊዜያቸውንስ ለምን በበጀት መልክ አይጠቀሙበትም?» ይል ነበር መልሶ መላልሶ ።

በዚህ ነጥብ ላይ ቢጽፍ እንደሚበጅ አርኖልድ ቤኔት አንድ ቀን ወሰነ ። ይህን በአእምሮው ሲያጉላላ የቆየውን ነጥብ በወረቀት ላይ ለማስፈር ጊዜ አልወሰደበትም ። የጽሑፉንም ርዕስ ፣ «በሐያ አራት ሰዓታት እንዴት መኖር እንደሚቻል» አለው ።......

«ጊዜ ለገለጻ የሚያዳግት ፣ የሕልውና ጥሬ ዕቃ ነው ። ጊዜ ካለ ሁሉም አለ ። ያለጊዜ ምንም ነገር አይኖርም ።......

«ማለዳ ስትነሡ ልብ በሉ! በፋብሪካ የማይመረቱና የሕይወት ደም ሥር የሆኑ ሐያ አራት ሰዓታት አሏችሁ ። ከማንኛውም ሀብት ይልቃሉ ።...... ሌባ አይሰርቃቸውም ። ማንም ከሌላው በበለጠ ወይም ባነሰ መጠን አይደርሰውም ።

«በጊዜ ዓለም ውስጥ የጊዜ ክበርቱ በመሆኑ የአእምሮ ባለጸጋነትንም ለማካበት የቢቃ ማንም የለም ። ጊዜ ለጠቢባን እንዲት ትርፍ ሰዓት አትለግስም ወይም ከሌላው አትቀንስም ።...... ውድ ጊዜ አችሁን እንዳሻችሁ አባክኑት ። ምንጩ አይደርቅ ባችሁም ። ጊዜ መበደርም አትችሉም ፤ ስለዚህ ዕዳ እንገባለን ብላችሁ አትሥጉ — ነገን ቀርቶ የምትቀጥለውን ሰዓት እንኳን በቅድሚያ ማግኘት አትችሉምና አይዟችሁ!

«የየዕለቱን ሐያ አራት ሰዓታት የሕይወት ጥሬታችሁ አድርጋችሁ ከነርሱው ጤንነትን ፡ ፍሥሐን ፡ ሀብትን ፡ ርካታን ፡ ክብርንና የመንፈስ ልምላሜን ገብዩ ።...... ደስታ ፡ ያች ልትጨብጧት የምትጣጣሩት የሕይወት ፍሬ ፡ መሠረቷ ጊዜ ነው ።

«የየዕለቱን ሐያ አራት ሰዓታት በገቢነት መዝግቦ እንዳስፈላጊነቱ በወጭነት በትክክል መመደብ የማይችል ሰው ሕይወቱን ያበላሻታል ።

«ካለን በላይ ጊዜ ከቶውንም ሊኖረን አይችልም ። ሁሌም የሚኖረን ይኸው ብቻ ነው ።»......

«በሒያ አራት ሰዓታት እንዴት መኖር እንደሚቻል» በሚለው ድርሰቱ አርኖልድ ቤኔት የተመኘውን መልእክት በሚገባ አስተላልፏል ። ሰዎች የጊዜን ዋጋ ፤ በተለይም ከመደበኛው የሥራ ሰዓት ውጭ ያለ ጊዜን ፤ በአልባሌ መንገድ ከማባከን ይልቅ በጠቃሚ ተግባር ላይ ማዋል አስፈላጊነቱን በጥራት አስገንዝቧል ።

ይህ ጽሑፍ በጊዜው ተወዳጅ እንደ ነበረ ሁሉ ዛሬም ወዳጆች እያፈራ ነው ። ምክንያቱም «አንዲት ትርፍ ደቂቃ እንኳን የለኝም» ወይም «ጊዜ የት ተገኝቶ!» እያሉ ለሚያጉተመትሙ ተፈላጊውን ምላሽ ይሰጣል ። ጊዜ ለማንም እንደማተሰወር ፤ የየዕለቱ ወርቃማ ሰዓታት በሁሉም ሰው እጅ እንዳሉ ያረጋግጣል ። ስለዚህ ከእነርሱው ደስታንና ርካታን መገብየት የእያንዳንዱ ፋንታ ነው ።

ምን ብልህ ብትሆን ነገን አታውቃትም ፤
እቅጩን ድባቧን አጉልተህ አትሥልም ፤
እናም ዛሬን አትናቅ በመሆን ዳተኛ ፤
አታያትምና ከእንግዲህ ዳግመኛ ።

አማር ካያም

☆ ☆ ☆

የጠፋ! ፡— በዛሬዋ ዕለት ጀምበር ወጥታ እስከምትጠልቅ ፤ ሁለት ወርቅ ሰዓቶች እያንዳንዳቸው በስ

ድሳ ዕንቁ ደቂቃዎች የተንቆጠቆጡ ጠፍተውብ ኛል ። አግኝቶ ሳመጣልኝ ወሮታውን አልከፍልም ፤ ለዝንተዓለም አምልጠውኛልና ።

ሆራስ ማን

☆ ☆ ☆

ብሩህ ቀን ሲወለድ ፤
ተመልከት ጉህ ሲቀድ!
እስኪ ልብ በለው ፤
ሳትጠቀምበት ከእጅህ ሊያመልጥህ ነው?
ከዘላለም ማሕፀን ይኸ ቀን ተወልዷል ፤
ጨለማን ተክቶም ከዚያው ይመለሳል ።
ገና በውል ሳይሠርፅ ወደ ዐይን ልቦና ፥
ጥሎህ ይሰወራል ላይመጣ እንደገና ።
ብሩህ ቀን ሲወለድ ፤
ተመልከት ጉህ ሲቀድ!
እስኪ ልብ ብለው ፤
ሳትጠቀምበት ከእጅህ ሊያመልጥህ ነው?

ቶማስ ካርላይል

☆ ☆ ☆

ሌሎችን ድል የሚያደርግ በእርግጥ ጉበዝ ነው ። በራሱ ላይ ድልን የሚቀዳጅ ግን፡ብኃያልነቱ ከማንም ይልቃል ።

ላዎ ፂ

የአጉል ማወላወል አደገኛነት፡
በጅ ያስገባነውን ድል አርገን በወቅቱ ፣
እስነጥቆን ያርፋል ፍርሃት በማምጣቱ ።

ዊሊያም ሼክስፒር

☆ ☆ ☆

ኤድዋርድ ሮውላንድ ሲል

«እስኪ ያለንን እንኳ በሚገባ እንጠቀምበት!»

ለኤድዋርድ ሲል ሕይወት ቸር ወይም ርኅሩኅ አልነበረችም ። ልዩ ዕጣዋ ቀርቶበት የተለመዱ በረ ከቷን እንኳን ነፍጋዋለች ። እንዲያውም ገና ከጅምሩ ኑሮውን የተያያዘው በአካል ስንኩልነት ነበር ።

ሁሉቱንም ወላጆቹን በሕፃንነት ዕድሜው ከማ ጣቱም በላይ ሕመምተኛም ስለ ነበር ከሚያቅዳቸው አያሌ ተግባራት ተደናቅፏል ። ተስማሚውን የሕይ ወት ጎዳም ለማግኘት ብዙ ደክሟል ። ቅስናን ሞክሮ በጠባብ አስተሳሰብ የሚተበትበው ስለመሰለው ተወው ። ጋዜጠኝነትንም ገብቶበት በአካልም ሆነ በመንፈስ ሊቋቋመው ባለመቻሉ ገሸሽ አደረ ገው ። በመምህርነትም ሞያ ተሰልፎ ነበር ። ግን ውጤትና ርካታን ቢለግሰውም ፣ በጤንነቱ መጓደል ምክንያት እርሱንም ለመተው ተገደደ ።

እንዲህ የመሰሉ እንቅፋቶች ከሚጋረጡባቸው ሰዎች አብዛኞቹ ተስፋ እየቆረጡ ትግላቸውን ያቀዘቅ ዙና ምክንያታቸውን ብቻ በመደርደር የሌላውን የድካም ወዝ በልመና መካፈል ይቀናቸዋል ። ኤድ ዋርድ ሲል ግን ፣ እንዲያ የሚያላዝን አልሆነም ።

ምክንያቱን እየደረደረ ከመኖር ይልቅ ሥርቶ ለማ
ደር ወሰነ ። ባለው አቅሙም የማችለውን ለማድረግ
ቆርጦ ተነሣ ።

ያም እምነቱ ምርኩዝ ሆኖት አካለ ስንኩልነቱ ሳያግደው ጠቃሚና ፍሬያማ ሕይወት ለመምራት በቃ ። ከመምህርነት ሙያው እንደ ተገለለ የተሰለፈው በደራሲነት ነበር ። «እስኪ ያለንን እንኳ በሚገባ እንጠቀምበት!» የሚለውን መመሪያውን ለሌሎችም ለማስጨበጥ በነበረው ጽኑ ዓላማ እየተገፋፋ ይህን እምነቱን ከጽሑፎቹ በአብዛኞቹ ውስጥ ማን ጸባረቁን ቀጠለበት ።

«ዕጣ» የተሰኘው ከዕውቅ ግጥሞቹ አንዱ ይህንኑ ማዕከላዊ ጭብጡን በሚገባ አሳምሮና አጉልቶ ያሳያል ።

ዕ ጣ

አንድ ነገር አየሁ ፣ በሕልም ይሁን በእውን ፣
በአውላላ መስክ ላይ ትቢያ እንደ ጉም ሲተን ።
ድምቡልቂኙን ጥሶ ጨኸት ያስተጋባል ፣
ፍልሚያ ተፋፍሞ ጐራዴ ይፋጫል ።
ምድር ቀውጢ ሆና ሲጋፈጥ ጦረኛው ፣
አየሁኝ አንድ ሰው ለመውደቅ የቃጣው ።
ጠላት አሰፍስፎ ዙሪያውን ከብቦታል ፤
አሞራም በላዩ ያንዣብብበታል ።
«ጐራዴ ቢኖረኝ ያንን የመሰለ ፣
እንዲህ ዱልዱም ሳይሆን በደንብ የተሳለ ......»
ብሎ ባመቆጨት ጥሎ የያዘውን ፣

ያ ምስኪን አሰበ ሊሮጥ የምብርክኩን ።
የጠላት ጦር መሪ ቆስሎ እያቃሰተ ፣
እንደ ምንም ብሎ እየተጐተተ ፣
ደረሰበትና ቀረበው ሊቀላው ፣
የተቃጣበትን አየውና ያም ሰው ፣
እልሁ ገንፍሎ ሲቃው እየናረ ፣
ያሽቀነጠረውን ፍሊጋ አማተረ ።
ተንደርድሮ ሔዶ ቶሎ ብድግ አርጐት ፣
ቀንጥሶ ጣለበት የጠላቱን አንገት ።
በጣለው ጐራዴ ታላቅ ታሪክ ሠራ ፤
ግዳጁን ተወጥቶ ወገኑን አኮራ ።

ባዚህ ደማቅ ሥዕላዊ መልዕክት ውስጥ የሚንጸባረቀው የራሱ የገጣሚው ሕይወት ነው ። ኤድዋርድ ሲል አቅሙን ተገንዝቦ ደካማነቱን ተቀብሎታል ። ባልሞት ባይ ተጋዳይነት ድልን እንደ ተቀዳጀው ጦረኛ እርሱም ባለው አቅሙ ተጠቅሞ ጥረቱን ፍሬ ያማ ለማድረግ በቅቶአል ።

ጨለማን ሲረግሙ ከመኖር አንዲት ቁራጭ ሻማ መለኮሱ ይበጃል ።

ኮንፊሺየስ

☆ ☆ ☆

በሕይወት የሚያጋጥም እውነተኛ ድክመት አንድ ብቻ ነው ፤ ያም ልብ የሚያውቀውን እንደማያውቁ መምሰል ይሆናል ።

ክነን ፍሬዲሪክ ፋራር

☆ ☆ ☆

ብቃትን የሚያስገኘው ዓይነተኛ መንገድ የማያቋርጥ ትግል ነው ። በአሸናፊንትና በተሸናፊነት መሐል ያለችው መስመር እንደ ጸጉር የቀጠነች ከመሆኗ የተነሣ ስናልፋትም ሆነ ቆም ስንልባት አናስተውላትም ። ጥቂት ተጨማሪ ጥረት በማድረግ ፣ ጥቂት ተጨማሪ ትዕግሥት በማሳየት ፋንታ እጃቸውን እየሰጡ አሸናፊነታቸውን የተነጠቁ ስንቶች ይሆኑ?...... ጥረትን ከማቋረጥ በቀር ሽንፈትን የሚወልድ ምንም ነገር የለም ። መንፈሳችንን እስካላዳከምንና የገዛ ዓላማችንን እስካላኮላሸን ድረስ የማንዉጣው ዳገት አይኖርም ።

ኤልሣቤጥ ሃባርድ

☆ ☆ ☆

ትምህርት ከሚለግሳቸው ምግባራት ሁሉ የሚልቀው መከናወን ያለበትን ተግባር — ተወደደም ተጠላም— በተመደበለት ጊዜ ውስጥ ማከናወን መቻል ነው ። ባቅድሚያ መጤን ያለበትም ይኸው ይሆናል ።

ቶማስ ሃክስሊ.

☆ ☆ ☆

ዛሬ አዲስ ቀን ነች ። የምትሰጥህም በስጠሃት መጠን ነው ። ብትሳሳትና ስሕተትህም ቢከፋ ለማረም ሰፊ ዕድል አለህ ። ደግመህ ደጋግመህ ሞክረህ ቢከሽፍብህም እንኳ እንደገና በአዲስ መንፈስ ለመጀመር ጊዜ እንደሚኖርህ ልብ በል ። «መሸነፍ» የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉሙ «መውደቅ» ሳይሆን «ወድቆ መቅረት» ነውኮ!

ሜሪ ፒክፈርድ

☆ ☆ ☆

ኤ. ጄ. ክሮኒን

«ከውጤቶች ሁሉ የሚልቀው በራስ ላይ ድልን መቀዳጀት ነው ። ይህን ድል የቀመሰ ከቶውንም ሽንፈትን አያውቅም ።»

ጠረጴዛውን ደገፍ ብሎ ይጽፋል ። በስተኋለኛው ዘመኑ በልቦለድ ሥራዎቹ ዝናን ያተረፈው ክሮኒን ፣ በዚያን ወቅት ያሰፍረው የነበረው ጽሑፍ እውነተኛ ታሪክ እንጂ የፈጠራ አልነበረም ። ትዕግሥትን ምርኩዙ አድርጎ ሽንፈትን እንዴት እንዳመለጠ ፣ ከጠበቀው በላይ እንዴት ለድል እንደበቃ የሚያወሳ የራሱን የሕይወት ገጠመኝ ነበር የሚጽፈው ።

ክሮኒን በአንድ ወቅት በለንደን ከተማ የሚኖር ታታሪ ዶክተር ነበር ። ነገር ፣ ግን በሠላሳ ሦስት ዓመቱ ጤንነቱ በመታወኩ ምክንያት ሞያውን ለመተው ተገድዶ በስኮትላንድ ግዛት ወደምትገኝ አንዲት የገጠር መንደር ተሰደደ ። ከዚያም እያለ በደራሲነት ሊሰለፍ ወሰነ ።

መጀመሪያ ላይ የደራሲነት ሞያ ቀላል ሆኖ አገኘው ። ለመጻፍ የሚፈልገው ታሪክ ፈልቆለት ፣ ገጸ ባሕርያት ተደርድረውለት በሥራው ተመሰጠ ። ግን ቀደም ሲል እንዲያ ያለ ተግባር ካለመሞከሩም

በላይ መሠረታዊ የአጻጻፍ ስልት ዕውቀት አልነበረ ውም ። ስለዚህም ለማለት የፈለገውን በሚገባ ለማስተላለፍ በእጅጉ ተቸገረ ። በአንዲት አንቀጽ ላይ ብዙ ሰዓታት ማባከን ግድ ሆነበት ። ጽሑፉ እየሰፋ በሔደ መጠንም ፡ ትረካው ትጓጉል እየተወሳሰ በበት ተስፋ ስላስቆረጠው ለሞያው ብቃት እንደ ሌለው ራሱን ገምቶ እስከናካቴው ሊተወው አሰበ ።

የዚያን ጊዜ ብስጭቱን ፡ ከዕለት ወደ ዕለት እየደ በተው ይሔድ የነበረውን ተስፋቢስነቱን በውል ያስታውሰዋል ። ያን ሁኔታውን በወረቀት ማስፈሩ ቢያሳፍረውም ፡ እንደርሱ ግራ የተጋቡ ሌሎች ሰዎች ትምህርት ሊያገኙበት ይችላሉ በሚል እምነት እው ነታውን በገሃድ ለማሳየት ቆርጦ ተነሣ ።

«የጽሑፍ ሥራዬን እንዳጋመስኩ ነበር ችግር የገጠመኝ ። በተስፋ መቁረጥ ስሜት ተዋጥሁና፡ ‘ምን ነቱን ጭራሽ ባልተገነዘብሁት በዚህ ከባድ ተግባር ተጠምጄ ለምን ራሴን አደክማለሁ? ምን ሊጠቅመኝ? ያለ የሌለ ኃይሌን ከማሚጥጥ ይልቅ ዐርፌ ብቀመጥ ይበጀኛል’ አልሁ ። ብዕሬንም አስቀመጥሁ ። ያስ ተየብኳቸውን የመጀመሪያ ምዕራፎች በጥሞና አን ብቤ ከእኔ ጭንቅላት የፈለቁ መሆናቸውን ማመን አዳገተኝ ። ያስፈርሁት ሁሉ ቅብዥርጅር ያለ ቅዠት ሆነብኝና ከሩቅ ጠልቼው ‘ማን ሊያነብልኝ!’ ከሚል መደምደሚያ ላይ ደረስሁ ። ራሴንም እንደ እብድ ሰው ገምቼ የቀድሞውንም ሆነ የወደፊት ሙከራዬን ዋጋ አሳጣሁት ። ‘ከንቱ ድካም!’ በንዴት እየተብ ሰከሰክሁ የጻፍሁትን ሁሉ ሰብስቤ ቆሻሻ ማጠራቀ ሚያ ዕቃ ውስጥ ከተትሁት ።

«በአድራጐቴ ረክቼና መንፈሴን አረጋግቼ ነፋስ ለመቀበል ከቤት ወጣ አልሁ ። ዝናብ ያካፋ ነበር ። ጥቂት እንደ ሔድኩ እንገስ የተባለ በዕድሜው የገፋ ገበሬ ደረቅና ድንጋያማ በሆነ ማሳው ላይ ሲማስን አገኘሁት ። መላ ጉልበቱን ያፈሰሰበት ነብረቱ ነበር። ስቀርበው ቀና ብሎ አየኝ ። በ«ደራሲነት» ሞያ እንደ ተሠለፍኩ ያውቅ ነበርና ከአክብሮቱ የተነሣ አፍ አውጥቶ ባያበረታታኝም እንድገፋበት ሳይመኝልኝ አልቀረም ። እኔ ግን ውሳኔዬን ነገርኩት ። ምን እንዳደረግሁ ምክንያቱን ጨምሬ በዝርዝር ስገልጽለት ብሩህ ዐይኖቹን ተክሎብኝ ከእግር ጥፍሬ እስከ ጸጉሬ ገላመጠኝ ። በትፈጥሮው ዝምተኛ ስለ ነበር ለመናገር ጊዜ ወሰደበት ። ለዚያውም ቢሆን ቃላቱ ጡሱን ነበሩ ።

‹እርስዎ ትክክል ለመሆንዎ ጥርጥር የለውም ፤ ዶክተር ። ስሕተተኛው እኔ ሳልሆን አልቀርም ። ......› በማለት አተኩሮ ቢመለከተኝ በዐይኖቹ ሰርስሮኝ ወደ ልቤ የገባ መሰለኝ ። ‹ምኞቱ ባይሳካለትም ፤ አባቴ ዕድሜ ልኩን ይህን መሬት ሲጐደፍር ኖሯል ። ያሰብሁት ባይሞላልኝም ፤ እኔም ይኸው እማስና ለሁ ። ምኞታችን ተሟላ አልተሟላ ከድካም አላመ ለጥንም ። ጥርሳችንን ነክሰን እንዲህ ደፋ ቀና ካልን አንድ ቀን ይህ ጠፍ መሬት ለም እንደሚሆን አባቴ ተስፋ ነበረው ፤ እኔም ይኸው ተስፋ አልቆረጥሁም› አለኝ ።

«አባባሉ ገባኝ ። ድክመቴን ላለመቀበል ቁጣ ቢቀድመኝም እንደምንም ውጩው ያን ጐንበስ ቀና የሚል ታታሪ ሰው በውል አጤንሁት ። እኔ ያጣሁትን

አንድ ቁምነገር እርሱ በመጨበጡ አስቀናኝ ። ሕል ሙን እውን ለማድረግ የሚገፋፋው የቁርጠኝነት መንፈሱ ፣ በእንዲያ ያለ አድካሚ ሥራ ሕይወቱን ሙሉ ቢጠመድም ፣ አለመታከቱ ራሴን በራሴው እንድገመግም ረዳኝ ። ከመቅጽበት ድክመቱ ወለል ብሎ ታየኝ ። ያገኘሁት ትምህርት ለማንም ሰው መመ ሪያ ሊሆን እንደሚገባ ፣ 'ይህን አገኘበታለሁ' በሚል ጉጉት ብቻ ሳይሆን ፣ ሥራን በሥራነቱ ለማፍቀር የሚያግዝ ዓይነተኛ መጽናኛ ወይም ጊዜ የማይሽ ረው የጥራል ምርኩዝ እንደሚሆን ተገነዘብሁ ።

«ቁጣውም ፣ ዕፍረቱም እየተናነቀኝና ዝናብ እየወረደብኝ ወደ መኖሪያዬ ተመልሼ ያን በርጥበት የላሸቀ ጥቅል ወረቀት ከቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ አወጣሁ ። ከማብሰያ ክፍል ወለል ላይ አንጥፌውም አንቃቃሁት ። ከዚያም ወደ ጠረጴዛዬ ወስጄው እንደገና ልጽፈው በሙሉ ስሜቴ ተያያዝሁት ። ዓላማዬን እያስተዋልኩ በሙሉ መንፈሴ ተመስጥ ሁበት ። 'ከእንግዲህ ወዲያ ልሸነፍ!...... እጄን አልሰ ጥም!' በሚል ወኔ ከንዴን አፈርጥሜ ከምንጊዜውም በበለጠ ጊዜዬን ሠዋሁበት ። በመጨረሻም ፣ ከሦስት ወራት ገደማ በኋላ ፣ «ተፈጸመ» የምትል ቃል ለማስ ፈር በቃሁ ። የተሰማኝን እፎይታና ኩራት ለመግ ለጽ ያዳግተኛል ። ለራሴው በራሴው የገባሁትን ቃል ኪዳን ጠብቄያለሁ ። አንድ መጽሐፍ አፍርቻለሁ ። ጥሩ ይሁን መጥፎ ደንታ አልነበረኝም ።

«ዐይኖቼን ጨፍኖ ዕጣ በማውጣት አንድ አሳ ታሚ ድርጅት መረጥሁ ። ጽሑፌንም ሳልውል ሳላ ድር ወደዚያው ከላክሁ በኋላ ልረሳው ሞከርሁ ።

«በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ ጤንነቴ ቀስ በቀስ ተመለሰልኝ ። ያለ ሥራ መቀመጤም እያስጠላኝ ስለመጣ ወደ ጥንቱ ሞያዬ ለመመለስ ወሰንሁ ።

«ወደ ቀድሞው ቦታዬ የምገባበት ቀን ተቃረበ ። የቅርብ ወዳጅ ሆነው ያስተናገዱኝን የዚያችን መንደር ቅን ነዋሪዎች በየቤታቸው እየተዘዋወርሁ ተሰናብቼ ወደ ፖስታ ቤት ጉራ ስል የፖስታ ቤቱ ሹም ከአሳታሚ ድርጅት የተላከልኝን የአስቸኳይ ጥሪ ቴሌግራም አስጨበጠኝ ። ያን ቴሌግራም በቀጥታ ወደ እንገስ ዘንድ ወስጄ አሳየሁት ።

«ያ የወረወርኩት ጽሑፍ ለሽልማት ተመረጠ ። ለመድረክ ተውኔት ታጨ ። ወደ ዐሥራ ዘጠኝ ቋንቋዎች ተተረጐመ ። ለፊልም ትርዒትነት በሆሊውድ ተገዛ ። ወደ ሦስት ሚሊዮን የሚጠጉ ቅጂዎች ከአንባቢ እጅ ገቡ ። ያ መጽሐፍ ባልጠበቅሁት ሁኔታ የሕይወቴን አቅጣጫ ለወጠው ። ታዲያ ለዚህ ሁሉ መንሥዔው ትዕግሥትን ምርኩዜ እንዳደርግ የገፋፋኝ የዚያ ሰው ወቅታዊ ትምህርት ነበር ።

«ዛሬም ትምህርትነቱ ጐልቶ ይታያል ። የሽንፈት ለቅሶ ከየአቅጣጫው በሚያስተጋባበት ፤ ከዓለማችን ነዋሪ ክፊሉ 'መሥራት...... መቆጠብ...... መኖር ......ምን ዋጋ አለው...... ምጽአት እየተቃረበ?' የሚል የተስፋቢስነት ዋይታ በሚያሰማበት በዛሬው ዘመን ያን ትምህርት ሳስታውስ መንፈሴ ቦግ ይላል ። በዚህ በውዥንብር ወቅት በብሩህ ተስፋ ካልተመራን ወደ

ድቅድቅ ጨለማ መሣሪያዎችን ነው ። ከእንዲህ ያለው ጨለማ ማምለጫው መንገድም የጀመርነውን ተግባር አጥብቀን መያዝ ፣ አልባሌ ቢመስል እንኳ በትጋት ገፍተንበት ከፍጻሜ ማድረስ እንደሚገባን በውል ያስገነዝበናል ።

«የሎያላው ኢግናሽየስ የተባለ ፣ አክራሪ የካቶሊክ እምነት ተከታይ ፣ በተማሪነት ዘመኑ ከጓደኞቹ ጋር በሚጫወትበት ወቅት ከመኻከላቸው አንዱ በድንገት ብድግ ብሎ ‘በሒያ ደቂቃ ውስጥ እንደምንሞት ብናውቅ ምን እናደርጋለን?’ ሲል እያንዳንዳቸውን ይጠይቃል ። ከኢግናሽየስ በስተቀር ሁሉም ‘አሁኑኑ ወደ ቤተክርስቲያን ሔደን እንጸልያለን’ ሲሉ ፣ ኢግናሽየስ ግን ፣ ‘በቅድሚያ ጨዋታችንን ማጠናቀቅ አለብን’ የሚል ምላሽ ሰጠ ይባላል ።

«ከውጤቶች ሁሉ የሚልቀው ፣ ለኢግናሽየስና ለዚያ የዕድሜ ጌታ ገበሬ እንደ ተገለጸላቸው ፣ በራስ ላይ ድልን መቀዳጀት ነው ። ይህን ድል የቀመሰም ከቶ ሽንፈትን አያውቅም ።»

ክሮኒን ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ ከጣለው በኋላ እንደገና እንዶሥቶት አስማምሮ የጻፈው ሥራው «ሐተርስ ካስል» (የሐተር ግምብ) የተሰኘው ነው ። መጽሐፉ ያተረፈለት ሀብትና ዝናን ብቻ ሳይሆን ድሉንም በራሱ ላይ ለመቀዳጀት አብቅቶታል ።

ሌሎች ተወዳጅ ልቦለድ መጻሕፍትን ያበረከተ ቢሆን ንም ፡ ሲታወስ የሚኖረው በዚያ ሥራው ነው ።

ከላይ የቀረበው የሕይወት ታሪኩ የተወሰደው «ዘ ተርኒንግ ፓይንት ኦፍ ማይ ከሪየር» (የሙያዬ ለውጥ መንሥኤ) ከተሰኘና በ«ሪደር ዳይጀስት» ላይ ካሰፈረው መጣጥፉ ሲሆን አባባሉም ፡ በመርሕነት በብዙ ሰዎች ሕሊና ሲመላለስ ይኖራል ።

ማድረግ የምትችለውን እናንቀህ ጭራሹኑ ምንም አለማድረግህ ከከፋ ስሕተት ላይ ይጥልሃል ። ስለ ዚህ የምትችለውን አድርግ ።

ሲደኒ ስሚዝ

የድል አድራጊነት ግርማ ሞገስ የሚመዘነው ፣ ጭራሽ ባለመውደቅ ብቻ ሳይሆን በወደቁ ቁጥር ለመነሣት በሚደረገው ጥረትም ጭምር ነው ።

ኦሊቨር ጐልድስሚዝ

እንደገና መሞከር ውርደት አይደለም ። እንደውም መልካም አጋጣሚነቱ ያመዝናል ።

ጆርጅ ማቲው አዳምስ

☆ ☆ ☆

ክፍል አራት

ሥነ ምግባርና ሰብዕና

«የግዛ ሰብዕና ለሕይወት ዕጣ ወሳኝ ዳኛ ነው ።»

ሳይረስ

«ሌላን በመብለጥ ታላቅነት አይኖርም ። እውነተኛ ታላቅነት የሚንጸባረቀው ራስን በየጊዜው ልቆ በመገኘት ነው» የሚለውን ጥንታዊ የሂንዱ አባባል «ሰው ከራሱ ጋር ትግል ሲጀምር ከሰው ቁጥር ገባ ይባላል» በማለት ሮበርት ብራውኒንግ ከዘመናት በኋላ መልሶ አስተጋብቶታል ።

ብዙዎቻችንም ይህን እንገነዘባለን ። ራሳችንን ለማሻሻል ፣ ስሕተታችንን ለማረም ፣ ከአጉል ልምዶች ለመቆጠብና ችሎታችንንም በሚገባ ለመጠቀም ሳናውልስ እንጥራለን ። ዋንግ ያንግ ሚንግ የተባለ ምሁር እንዳስቀመጠው ፣ «የሰው ልጅ ታላቁ ችሎታ፣ ስሕተቱን እያረመ ሳያውልስ ራሱን አዲስ ሰው ማድረግ መቻሉ ነው ።»

ግን ራስን ለሥርዓት ማስገዛት ቀላል አይደለም ። ከፕሌቶ እስከ ዊሊያም ጀምስ ያሉ ምሁራን እንደሚያስረዱን ፣ ራስን ማሸነፍ ከድሎች ሁሉ የሚልቅ ድል ነው ። «ከሌሎች ጋር ካደረግሁት ትግል ሁሉ በይበልጥ ፍዳዬን ያሳየኝ፣ከራሴው ጋር የገጠምሁት ግብግብ ነው» ብሏል ድዋይት ሙዲ የተባለ አንድ ካህንም ።

ከባዱ የስብዕና ፈተና የገዛ ራስን ሕይወት መምራት መቻል ላይ ያተኩራል ። ሰው ዕርቃኑን እንደ

ተወለደ ሁሉ ዕርቃኑን አይኖርም ፤ የሕይወት ዕጣ ውን ፣ አቅጣጫና ግቡን የመጨበጥ ኃይል አለውና ። ስለሆነም ነው ፡ «ሰው የገዛ ራሱ ወዳጅም ጠላትም ነው» በማለት ባጋቫድ ጊታ የሚያስተምረው ።

ቀጥሎም ራስን ለሥርዓት ለማስገዛትና ሰብዕ ናንም ለማዳበር የሚረዱ ምርጥ አባባሎች ቀርበዋልና በጥሞና እናጢናቸው ።

☆ ☆ ☆

ቀን እንደሚተካ ሌሊቱ ሲያከትም ፥
ሐቀኛነትህን እሚከድ አይኖርም ።»

ይህ አባት ለልጁ የሚያካፍለው ምክር ተደጋግሞ የሚጠቀስ ፣ ከአንባቢ ልቡና የሚያስገባው ብስለትና ምሉዕነት ያለው እንደመሆኑ በመልካም ወላጆችና ልጆች መኻል ያለውን ፍቅርና መተሳሰብ አጉልቶ ያሳያል ።

ቃልህን ከሚያሳጥፍህና ክብርህን ከሚያጐድፍብህ ድርጊት እንዳች ጠቀሜታ አገኛለሁ ብለህ አታስብ ።

ማርክስ ኦሬሊየስ

☆ ☆ ☆

የትምህርት ሁሉ ዓላማና ግብ ሰብዕናን ማዳበር ነው ።

ፍራንሲስ ፓርከር

☆ ☆ ☆

ጥራትና ዘለቄታ ያለው ክብር የሚመነጨው ሰው በጐረቤቱና በጓደኞቹ ዘንድ ከሚያተርፈው መልካም ስም ነው ።

ቻርልስ ኢሊየት

☆ ☆ ☆

ቀን እንደሚተካ ሌሊቱ ሲያከትም ፣
ሐቀኛነትህን እሚክድ አይኖርም ።»

ይህ አባት ለልጁ የሚያካፍለው ምክር ተደጋግሞ የሚጠቀስ ፣ ከአንባቢ ልቦና የሚያስገባው ብስለትና ምሉዕነት ያለው እንደመሆኑ በመልካም ወላጆችና ልጆች መካል ያለውን ፍቅርና መተሳሰብ አጉልቶ ያሳያል ።

ቃልህን ከሚያሳጥፍህና ክብርህን ከሚያጐድፍብህ ድርጊት አንዳች ጠቀሜታ አገኛለሁ ብለህ አታስብ ።

ማርከስ ኦሬሊየስ

☆ ☆ ☆

የትምህርት ሁሉ ዓላማና ግብ ስብዕናን ማዳበር ነው ።

ፍራንሲስ ፓርከር

☆ ☆ ☆

ጥራትና ዘለቄታ ያለው ክብር የሚመነጨው ሰው በጐረቤቱና በጓደኞቹ ዘንድ ከሚያተርፈው መልካም ስም ነው ።

ቻርልስ ኢልየት

☆ ☆ ☆

ለገዛ ራስህ ክቡር ዓላማዎች ታማኝ ሁን ።

ዊሊያም ቻኒንግ

☆ ☆ ☆

ምንኛ ደስ ይለው —
ዕድገቱ ያረቀው
ትምህርት ያነፀው ሰው!
ሕሊናውን ሽጦ የማያደገድግ ፣
እውነተኛነቱን መከታው እሚያደርግ ፣
ምን ቅንጣት ብታክል በሐቅ እሚመካ ፣
በሳልነቱንም በዚሁ እሚያስለካ ፥
ምንኛ ደስ ይለው —
እንደዚህ ያለው ሰው!

ሰር ሄንሪ ዎተን

☆ ☆ ☆

ጀምስ ሌን አለን

«ግባችንን የሚያሠምርልን መለኮት ያለው በውስጣችን ነው ።»

ጀምስ ሌን አለን «ሰው ያሰበውን ይሆናል ። የአንድ ሰው ግልጽ ባሕርያት የስውር ስሜቶቹ ዓይነተኛ መግለጫዎች ናቸው» በሚለው ፍልስፍና ይመሰጥ ነበር ።

«የአንድ ሰው ሰብዕና የውስጣዊ ስሜቶቹና ድብቅ ምኞቶቹ ነጸብራቅ ነው ።» ጀምስ አለን የዚህን አባባል እውነታነት በራሱ ሕይወት ላይ አረጋግጧል ። በችግር ያደገ እንደ መሆኑ የዘመኑ ወጣቶች ያግበሰብሷቸው ከነበሩ ብዙ ነገሮች አንዱን እንኳን ለማግኘት አልታደለም ። ሕይወቱን ለማበልጸግ በውስጡ ከታመቀው ብሩህ ምኞቱ በቀር ምንም አልነበረውም ። ምኞቱን እንዴ ምን አድርጐ በእውን እንደሚተረጕመው ከማውጠንጠን ተቆጥቦ አያውቅም ነበርና ዘዴውን ጠንቅቆ ተረዳ ። እንደሚያልመው ለመኖርም ፣ ጥረቱን ባለማቋረጡ ሕልሙ ወደ እውን ተለወጠለት ።

«ሰው ያሰበውን ይሆናል» የሚል እምነቱን ፣ ይህን ቀላልና ግልጽ እውነታ ሰዎች እንዴት እንደ

ማይገነዘቡ ፡ ለሚደርስባቸው በጉም ይሁን ክፉ ገጠመኝ ከራሳቸው ውጭ የሆነን ኃይል ማወደሳቸው ወይም መኮነናቸው ይከነክነው ነበርና ፣ አእምሮን እንደ አትክልት ሥፍራ በመቁጠር እያንዳንዱ ሰው ለገዛ ሕይወቱ የሚበጀውን መትከልና መኮትኮት እንደሚገባው ለማሳሰብ ሲል የሚከተለውን ቁም ነገር አሰፈረ ።

«ሰው የገዛ ራሱ አትክልተኛ ነው ። በመልካም አስተሳሰቡ መልካም ፍሬን ፣ በዕኩይ አስተሳሰቡም መጥፎ ፍሬን ያፈራልና ።

«ያልበሰሉ ሰዎች ‘ዕድል’ ወይም ‘ዕጣ’ በሚባል ጣጣ ያሳብባሉ ። ግባቸውን የሚያሠምርላቸው መለኮት በውስጣቸው ያለ መሆኑን የሚያስገነዝባቸው ኮርኳሪ ይፈልጋሉ ። አስተሳሰብና ሰብዕና የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው ። በለም አፈር በሚመስለው የአእምሮዋችን ጓዳ የምንኮተኩተው ዘር ለማንኛውም አቅጣጫ ፣ ለድል ይሁን ለሽንፈት ፣ መሠረት መሆኑን መገንዘብ አለብን ።

«ሰብዕና የአስተሳሰብ ድምር ነውና ሰው እንዳ በሰው ይሆናል ። ተክል ያለ ዘር እንደማይጸድቅ ሁሉ ድርጊትም ያለ ዓላማ አይመነጭም ። ድርጊት ፣ የግልጽ ይሁን የስውር አስተሳሰብ መግለጫ ነው ። ውጤቱም ደስታ ወይም ሐዘን ይሆናል ። ስለዚህ ሰው እንዳመለካከቱ ነው ፣ ጣፋጭ ወይም መራር ፍሬን የሚያመርተው ።

«የሰው አእምሮ በአትክልት ሥፍራ ይመሰላል ። በጥበብ ይኮተኮታል ፤ ወይ ዳዋ ይለብሳል ። የሚያበቅ

ስውም የሰጡትን ነው ። ጠቃሚ ዘር ካልተዘራበት ዐረም ይውጠዋል ።»

«አንድ ትጉኅ አትክልተኛ መደቡን ከዐረም እያጸዳ ሳይታክት የሚፈልጋቸውን አበቦችና ፍራፍሬዎች እንደሚንከባከብ ሁሉ ሰውም ከተዛቡ ፣ ከፋይዳቢስና ከግርድፍ አስተሳሰቦች አእምሮውን ነጻ ማድረግ አለበት ። ይህን ተግባር ሳያቋርጥ ካከናወነ ይፍጠንም ይዘግይም ፣ የመንፈሱ ዕውቅ አትክልተኛ ፣ የሕይወቱ ባለቤት ራሱ መሆኑን ይደርስበታል ። አስተሳሰቡንና ሰብዕናውን በዚህ ዘዴ ለማጣጣም ከተጣጣረ የዕድገት መሥመሩን ይጨብጣል ።»

«ሰው ሰው የሚባለው በአሸናፊነት ተውጥቶ የጥረቱን ስኬታማነት ሲያስተውል ነው ። ለዚያ ግብ የሚያበቃውም አስተሳሰቡን ባሳደገ መጠን ነው ። ዳተኛ ከሆነ በዚያው ልክ ደካማና ጐስቋላ ሆኖ ይቀራል ።......»

ጀምስ አለን በቋንቋ መምህርነት ረጅም ጊዜ አሳልፏል ። በደራሲነት ሞያም ዕውቅ ለመሆን በቅቷል ። ብዙ መጻሕፍትን ቢያበረክትም ሲታሰብ የሚኖረው ኮላይ ቀንጨብ ተደርጐ በቀረበውና «ሰው እንደሚያስበው» በተሰኘው መጣጥፉ ነው ።

የጽሑፉ ንዝረት ዛሬም የብዙ ሰዎችን ስሜት ስልሚኮረኩሩ ተዘውትሮ ይጠቀስለታል ። መልእክ

ቱም ባጭሩ ፣ «መልካም አስተሳሰብ መልካም ፍሬን ፣ እኩይ አስተሳሰብ እኩይ ፍሬን ይሰጣልና በጐ ምኞታችሁን ተንከባከቡ ፤ ካሰባችሁበት ግብ ለመድረስ ተጣጣሩ ፤ ሰው እንደሚያስበው መሆን ይችላልና » የሚል ነው ።

ጥሩ ወይም መጥፎ የሚባል ነገር የለም ፤ አስተሳሰብ የሚፈጥረው እንጂ ።

ዊሊያም ሼክስፒር

☆ ☆ ☆

እያንዳንዱ ሰው ፡ በትምህርት ዓለም ቆይታው ምቀኝነት አላዋቂነት መሆኑን የሚያምንበት ፣ እርሱነቱን መዝኖ ለበጐ ዓላማ የሚያሰልፍበት ፡ ምንም እንኳ ምድራችን በጸጋ ብትሞላም ፡ላቡን እስካላንጠፈጠፈ ድረስ ክበረከቷ የሚያረካ ድርሻ እንደማያገኝ የሚገነዘብበት ምዕራፍ ይገጥመዋል ። በውስጡ የታመቀውን የኃይል ግለት መጠንና ያን ኃይሉንም በምን ዓይነት ተግባር ማዋል እንደሚገባው ማጤንየእያንዳንዱ ሰው ፋንታ ነው ። ከርእሱ በቀር ይህን የሚያውቅለት ማንም የለም ። እርሱ ራሱም ቢሆን በተግባር እስካልፈተነው ድረስ ሊደርስበት አይችልም ።...... ስለሆነም ሁሉም «በራስ መተማመን» በሚል የሙዚቃ ምት መንፈሱን መቀስቀስ አለበት ።

ራልፍ ዋልዶ ኢመርሰን

☆ ☆ ☆

ሌሎችን አውቃለሁ የሚል ብልጣብልጥ ፣ ራሱን የሚያውቅ ግን ብልህ ነው ።

ላዎ ፂ

☆ ☆ ☆

በራሱ ለራሱ አመኔታ ከሌለው ሰው ቁምነገር መጠበቅ ሞኝነት ነው ።

ጀምስ ራስል ሉዌል

☆ ☆ ☆

ከራስህ በበለጠ ለማንም ባለዕዳ አትሆንም ። ወደ መልካም ሕይወት የሚያመሩህን በሮች ፣ የጥረትህንና የውጤትህን መዛግብት ፣ የትግልህንና የድልህን መድረኮች የጨበጥክ አንተው ነህና ራስህን ከዕዳ በማውጣትህ ግለኛ የሚልህም አይኖርም ። እንዲያውም በመንፈስ ጠንካራነትህ ራስህን ለመቻል በመብቃትህ ለፈጠረህና ላስመዘገበህ ኅብረተሰብ ውለታውን በሚገባ ከፈልህ ማለት ነው ። ስለዚህ በውስጥህ የታመቀውን በጎ ምኞትህን ለማሟላት በራስህ ለራስህ ቃል ግባ ።

ዴቪድ ሃሮልድ ፊንክ

☆ ☆ ☆

ዝናን ለማትረፍ ዓይነተኛው መንገድ መስለህ ለመታየት የምትመኘውን ሆነህ መገኘት ነው ።

ሶቅራጥስ

☆ ☆ ☆

ሰብዕናው ደምቆ ሰው ሰው እሚባለው
እርሱነቱን አውቆ በወግ ሲያርቀው ነው ።

ፔርሲ ሼሊ

☆ ☆ ☆

ልብህን ብሩህ አድርገው ፤ ዓለምን የምትመለከትበት መስኮትህ ነውና ።

ጆርጅ በርናርድ ሾ

☆ ☆ ☆

ሂጶቅራጥስ

በ460 ዓ. ዓ. በኮዝ ደሴት የተወለደው ሂጶቅራጥስ ዕድሜውን በሙሉ ለሕክምና ሳይንስ ዕድገት የሠዋ ፤ ስለ ሕክምና ዘዴዎች ፣ ስለ መድኃኒቶች ፣ ስለ ሕክምና መሣሪያዎች ...... ሰፊ ጥናት አካሒዶም የመጀመሪያውን የሕክምና መጽሐፍ ያቀነባበረ ታላቅ ፈላስፋ ነው ። እስከ ዛሬም ፣ «የሕክምና አባት» በመባል ይጠራል ።

በሕይወት ዘመኑ ማክተሚያ ላይ በእርሱና በደቀመዛሙርቱ ብርታት የሕክምና ሞያ የቱን ያህል እንዳደገ ፣ ወደፊትም የቱን ያህል እንደሚዳብር እያሰላሰለ በደስታ ተዋጠ ። በሕክምና ሞያ ለመሠልጠን ወደ ክበቡት ወጣቶች ሲያማትር አብዛኞቹ ግባቸውን ለመምታት የሚታገሉ ፣ ትምህርታቸውንም በንቃትና በሥርዐት የሚከታተሉ ሆነው አገኛቸው ። ግን አንድ የቀረው ጉዳይ ያለ መሰለው ። የሕክምና ሞያ በጥበበ መካንን ብቻ ሳይሆን ሚዛናዊ ሰብዕናንና ጠንካራ ሞራልንም አጥብቆ የሚጠይቅ ማኅበራዊ ግልጋሎት በመሆኑ ፣ በሞያው የተሠማሩ ሁሉ መመሪያቸው የሚያደርጉት አንድ ጽሑፍ ማዘጋጀት እንዳለበት አመነ ። ሐኪሞች ለሞያቸው ሊኖራቸው የሚገባቸውን ታማኝነትና ከታካሚዎቻቸው ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት ፣

ክብቃትና ከቅልጥፍና ባላነሰ ደረጃ መኮትኮት እንዳ ለባቸው የሚጠቁም ቃለ—መሐላ አወጣ ።

በዘመኑ የነበሩ ፣ ዛሬም ያሉና ለወደፊትም በሞያው የሚሠማሩ ሁሉ ለተጠጉዋቸው ሕሙማን አገልጋይና ተቆርቋሪ የሚያደርጋቸው ፣ ሕሙማንን በቅንነትና በርኅራኄ እንዲያገለግሉ የሚገፋፋ ነበር ፣ ያ መመሪያ ። የሚታወቀውም «የሂጶቅራጥስ ቃለ—መሐላ» በመባል ነው ።

ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች በተለያዩ መንገዶች ተተ ርጉሟል ። ከዚህ በታች የቀረበው ቅጅ ከዋነኛው የግሪክ ጽሑፍ ወደ እንግሊዝኛ የተመለሰው ሲሆን የአማርኛው ቅጂውም የእንግሊዝኛውን ጽሑፍ ቃል በቃል እንዲወክል ጥረት ተደርጓል ።

የሂጶቅራጥስ ቃለ—መሐላ

ከማንም አብልጬ በማከብረው ስም በሐቅ እምላለሁ ።
ለሕክምና ሞያ ታማኝ ፣ ለአባላቱም ግልጽና ርኅሩኅ እሆናለሁ ።
ሕይወቴንና ተግባሬን በቅንነትና በብቃት እመ ራለሁ ።

በደል ከመፈጸም ፣ ምግባረ—ቢስ ከመሆንና ሌሎችንም ወደ መጥፎ ተግባር ከመገፋፋት ራሴን አርቄ ያለኝን ችሎታ ሁሉ ለሕመም ተኞቼ በጐነት አውላለሁ ።
ሕመምተኞቼን ለማዳን ብቻ እንጂ፣መድኃኒትን

በመስጠትም ሆነ አፕራሲዮን በማድረግ የወን
ጀል ዓላማን ራሴው ላራምድ ቀርቶ ብገደድ
እንኳ ሳልተባበር ተግባሬን አከናውናለሁ ።
የማየውም ሆነ የምሰማው፡የአንድ ሕመምተኛ
የሕይወት ታሪክ ፥ ለሌላ የማይነገር እስከሆነ
ድረስ ተጠንቅቄ በምስጥር እጠብቃለሁ ።
በእነዚህ ሁሉ ቃል እገባለሁ ። የመሐላ ቃሌን
እንደ መጠበቄ ደስታና መልካም ስም አይለ
ዩኝ ፤ መሐላዬን ባፈርስ ተቃራኒው ይድረስ
ብኝ ።

ከሐያ ምዕተ ዓመታት በፊት የተጻፈው ፥ «የሂጶቅ
ራጥስ ቃለ—መሐላ» ሐኪሞችን ለዘመናት ሲያነቃቃ
እንደቆየ ሁሉ የዛሬዎቹም ምሩቃን እየተቀበሉት
ከዲፕሎማዎቻቸው ጋር በክብር ይይዙታል ። ያ
«የሕክምና አባት» ባወጣላቸው መመሪያ መሠረ
ትም ተግባራቸውን ያከናውናሉ ።

«የሂጶቅራጥስ ቃለ—መሐላ» ለሐኪሞች የወጣ
መመሪያ ቢሆንም ፥ ሌሎችም ባለሞያዎች ተግባራቸ
ውን እንዲያፈቅሩና ለሚያገግሉት ኅብረተሰብ ታማኝ
እንዲሆኑ በምሳሌነቱ ይጠቅማል ።

የአንድን ሰው ታላቅነት የሚያጐላው መከበሩ ሳይሆን «ያ ክብር ይገባኛል ወይ?» የሚለው ግንዛቤው ነው ።

አሪስጣጣሊስ

☆ ☆ ☆

ነጻነቴን ስጡኝ ወይ ግፈፉኝ ፤ ግን ከሕይወት መሥመሬ ፈቀቅ እንደማልልላችሁ ዕወቁልኝ ፤ ወይ ፍንክች — ደጋግሜ ብሞት እንኳ!

ሶቅራጥስ

☆ ☆ ☆

መልካም ስም ለሰው ልጅ የመንፈስ ቀንዲል ናት ፤
ልማደኛ ሌባ ቦርሳዬን ቢሰርቃት ፥
ትራቅምቦኮ ነው የሚነጥቀኝ ዕቃ ፤
የኔ የነበረው ዛሬ የእሱ ሆነ ፥ ለአዕላፍ ተብቃቃ ።
ያችን መልካም ስሜን ግና የሰረቀኝ ።
እርሱ ላያልፍለት እኔን አደኸየኝ ።

ዊሊያም ሼክስፒር

☆ ☆ ☆

እንዲህ ያለ ጊዜ አበክሮ እሚሻው
እጃቸው የማይዝል ፥ ጭንቅላት ያላቸው ፥
በንጹሕ ልቦና በዓላማ እሚፀኑ ፥
ሥልጣን አስክሯቸው በድን እማይሆኑ ፥

የቢሮ ካዝናቸው እማይደልላቸው ፤
ሐሳብ በማመንጨት እርእያ እሚሆኑ በጽኑን
ታቸው ፤
ለክብራቸው ሲሉ ከውሸት የራቁ ፤
ያለማወላወል ሽንገላን የናቁ ፤
አወናባጆችን እሚያወግዙ አፍጥጠው ፤
እንደ ፀሐይ ጮራ ጭጋጉን ሰንጥቀው
በሥራቸው ሆነ በአስተሳሰባቸው እሚታዩ ልቀው ፤
እንዲህ ያሉትን ነው ፤
ያለንበት ዘመን አበክሮ እሚሻው ።
አለበለዚያማ ታስሮ በአሮጌ እምነት ፤
በጉራ ተሞልቶ በተግባር መደህየት
መታወር ይመጣል በስግብግብነት ።
እንደዚህ ከሆነም ነጻነት እንባች ፤
በደል ነግሣ ስትኾር ፍትሕ እንቀላፋች ።

ጆሺያህ ሆላንድ

☆ ☆ ☆

ኃላፊነቴን በሚገባ ተወጥቼ ሥልጣኔን ሳስረክብ ቀድሞ ከነበሩኝ ባልደረቦቼ ቢያንስ ፥ ቢያንስ አንድ አይዞህ ባይ አላጣም — ያም በውስጤ አብሮኝ የሚኖረው ንጹሕ መንፈሴ ነው ።

አብርሃም ሊንከን

☆ ☆ ☆

ሥውር ምግባርህን አውጥቶ አደባባይ ፣
እቅጩ እንቶኔንትክን አጉልቶ የሚያሳይ ፣
እንደ ጥላህ ሁሉ ክቶ እማይለይህ ፣
ሌላ ገጸባሕርይ አለኮ በውስጥህ!

ዊሊያም ሼክስፒር

ክፍል አምስት

ፍቅርና ማኅበራዊ ኑሮ

«በቤት ውስጥ ደስታን መሻት የምኞት ሁሉ ቁንጮ ነው ።»

ሳሙኤል ጆንሰን

ከጐጆና ከቤተሰብ ይበልጥ የሚሞቅና ዘለቄታ ያለው ምንም ዓይነት ማኅበራዊ ግንኙነት የለም ። ፍቅርና ጋብቻ ፣ ወልዶ መሳምና በቤተሰብ መታቀፍ የሕይወት ጣፋጭ ፍሬዎች ሁሉ መሠረት ፣ ከፍተኛው የደስታ ምንጭ ነው ።

«ጐጆ ግዛት ነው» ብሏል ሲሰሮ የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመታት ገደማ ። «ከገዛ ጐጆ ወዲያ የሚያረካና እፎይታን የሚለግስ ዓለም የለም ። በቤቱ ሰላምን የሚያገኝ ከማንም ይበልጥ ደስተኛ ነው» በማለት እንዳስተማረው ሁሉ ፣ ጎተ የሚባል ፈላስፋም «የትምህርት ሁሉ ተቀዳሚው ምዕራፍ አብሮ የመኖርን ጥበብ መቅሰም ነው» ይላል ። ዊያሊያም ላዮን ፊሊፕስ «ጋብቻ» በተሰኘው ዝነኛ መጣጥፉ ውስጥ «ከጥበባት ሁሉ የሚልቀው ፣ አብሮ የመኖር ጥበብ ነው» ሲል ይህንኑ አባባል ይደግማል ።

እንደ ማንኛውም ማኅበራዊ ግንኙነት ለልብ ወዳጅነትም ዋናው መመሪያ «ለመወደድ ከፈለግህ ሰው ወዳድ ሁን» የሚለው ነው ። «ፍቅርን ልትላበስ ከፈለግህ» ይላል ዴል ካርኒጊም በበኩሉ ፣ «ብቸኛው መንገድ እንዲያፈቅሩህ መወትወትህን ትተህ ፍቅርህን ለግስ ፣ ፍቅርን ስትሰጥ ብቻ ነው ፍቅርን የምታገኘው ።»

......ዶግነትና መተሳሰብ አስፈላጊ ባሕርያት መሆ ናቸው የተዘነጋበት ዘመን ከቶ አይገኝም ። «ስለራሱ ብቻ የሚያስብ ሰው ፣ ራሱን በራሱ የጠቀለለ ኢምንት ቋጠሮ ነው» ያለው ሃሪ ፎስዲክም ይህንኑ እውነታ ከልብ በማጤን ነው ።

«ለራስህ እንዲደረግልህ የምትሻውን ለሌላውም አድርግ» የሚለው አባባል ፣ የሰዎችን ግንኙነት ከሚ ያዳብሩ ጥንታዊና ጊዜ የማይሽራቸው ድንጋጌዎች መካል አንዱ ሲሆን ፣ በግብረ ገብ መመሪያነቱ ዛሬም ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ። ኢመርሰን «ጓደኛ ለማፍራት ጓደኛ ሁን» በማለት ይህንኑ ሐቅ እንዳስ ተጋባ ሁሉ ፣ ሌሎችም ምን እንዳሉ እስቲ በጥሞና እንመልከት ።

☆ ☆ ☆

ኤልሳቤጥ ባሬት ብራውኒንግ

«የማፍቀር ስሜቱን እንዴት ልግለጽልህ?
ያይነቱን አበዛዝ ስማኝ ልቁጠርልህ ።......»

ኤልሳቤጥ ብራውኒንግ እጅግ በጣም ተደስታ ለች ። በብርዳማውና ጭጋጋማው የለንደን ከተማ በጠና ታምማ ፣ ሽባ ሆና ማለቱ ይቀላል ፣ ትኖር ነበር ። በድንገት ወደ ፀሐያማውና ሞቃታማው ጣሊ ያን አገር ፣ ከምታፈቅረው ባለቤቷ ጋር ተሰድዳ አዲስ ሕይወት ፣ አዲስ ሕልም በመኮትኮት አይታ የማታውቀውን ደስታ ተጐናጸፈች ።

«ተሽሎኛል ፡ ተጠናክሬያለሁ» ትለዋለች ደግማ ደጋግማ ፤ የሚጨነቅላት ባሏን ስታረጋጋው ።

ሮበርት ብራውኒንግ ነበር ለጤንነቷ ሲል አባ ብሎ ከተሸከርካሪ ወንበሯ በማላቀቅ ወደ ጣሊያን አገር ያስኮበለላት ። የአየር ለውጥና ፍቅር ተአምራ ቸውን ሠሩ ። ገና ደካማና ገመምተኛ ብትሆንም ሸባ ከመሆን ድና ዓለምን ለማየት ፣ ከልቧ ለምታ ደንቀውና ለምታፈቅረው ባሏ እውነተኛ ሚስትና ጓደኛ ለመሆን በቃች ።

«የማፍቀር ስሜቴን እንዴት ልግለጽልህ?
ያይነቱን አበዛዝ ስማኝ ልቁጠርልህ ።
ወደ ህዋ ብትመጥቅ ነፍሴ ተመንጥቃ ፤
ወይ ብታሽቆለቁል መሬትን ሰንጥቃ ፤
ብትከንፍ እንደ ነፋስ ካድማስ ማዶ ርቃ »
የሚለውን ግጥሟን ከዕለታት በአንደኛው ቀን ብልጭ አደረገችለት ።

ለንደን በነበረችበት ወቅት ሮበርት ብራውኒ ንግ ብቅ እያለ ሲያጫውታት የጻፈቻቸው ስንኞች ነበሩ ። ያኔ ሕመምተኛ ፣ ብስጩና ሆደ ባሻ ፣ ልጆቹ ባል እንዳያገቡ በሚከላከል ጨካኝ አባቷ መዳፍ ውስጥ ነበረች ። ግን ባልተቆጠበ ፍቅሩ ሮበርት ብራ ውኒንግ እየተመላለሰ ይጠይቃትና ክፍሏን በአ በቦች ያስጌጥላት ነበር ፣ ፍቅሩን እየገለጸላትና እን ድታገባው እየለመናት ።

እንዲያ በተጨነቀችበትና የምታደርገው መላ ቅጡ በጠፋባት ፤ በሮበርት ብራውኒንግ ፍቅርና

በአባቷ ቁጣ ፍዳዋን በምታይበት በዚያ ወቅት የፍ ቅር ግጥሞቿን የምትጽፈው በድብቅ ነበር ፣ ካለርሷ በቀር ማንም እንዳያይባት ተጠንቅቃ ።

«አሁን ላሳየው እችላለሁ» አለች በልቧ ። «አሁን ላሳየውና የቱን ያህል እንደማፈቅረው ይረ ዳልኝ!»

ስለዚህ በአንድ ፀሐያማ ቀን ፣ አየሩ መንፈስን በሚያማልልበት በጸደይ ወቅት ሮበርት ብራውኒንግ የሚስቱን ተደብቀው የኖሩ የፍቅር ግጥሞች ለማ ንበብ በቃ ። በውበታቸውና በብስለታቸው ጥራት ያላቸው ሥራዎች መሆናቸውን ተገንዝቦ በሙሉ ስሜቱ ተማረከ ። «ከሼክስፒር ወዲህ ከተጻፉት ግጥሞች ሁሉ ውቦች እኒህ ናቸው» በማለትም አከ ራራት ።

ለፍቅሯ ሲል ዳኝነቱን እንዳዛባ ብትጠረጥርም ምስጋናው እንደ ሕፃን አፍነከነካት ። የዎርድስ ዎርዝ ወደር የለሽ ግጥሞች ከእርሷ በዐሥር እጅ እንደሚበልጡና ምንጊዜም እንደዚያ መግጠም እን ደማትችል ገመተች ። ቢሆንም ምስጋናውን ወደደ ችለት ። ስመጥር እንግሊዛዊት ባለቅኔ መባሏ አስደ ሰታት ።

«የትኛውን ነው በይበልጥ የምትወደው?» አለ ችው ፈራ ተባ እያለች ፤ ውስጣዊ ስሜቷን አጉልተው የሚያሳዩባት ሥራዎቿ መሆናቸውን ታውቃለችና ።

«ሁሉንም እወዳቸዋለሁ!» አላት ። «ግን ፣ 'እን ዴት ልግለጽልህ?' የሚለውን በተለይ እወደዋለሁ ። እስኪ ደግሜ ላንብበው ።»

ደስ አላት ። «እኔም የምወደው እርሱኑ ነው ፣ ሮበርት!» አለችው ።

እንዴት ልግለጽልህ?

የማፍቀር ስሜቴን እንዴት ልግለጽልህ?
ያይነቱን አበዛዝ ስማኝ ልቁጠርልህ ።
ወደ ህዋ ብትመጥቅ ነፍሴ ተመንጥቃ ፣
ወይ ብታሽቆለቁል መሬትን ሰንጥቃ ፣
ብትከንፍ እንደ ነፋስ ካድማስ ማዶ ርቃ ፣
የምጥቀት ፣ የጥልቀት ፣ የስፋቱ መጠን ይቅር
አይወጋ ፤
የምትዋትትበት አንተኑ ፍለጋ ።
የሕልም ጉዞ ነው ፣ የሐሳብ መቅነት ፤
ግና ሥገነቷ ደርሳ እምታርፍበት
የሰው ቁንጮ አንተ ነህ ፣ የሞገስ አብነት ።
ለየዕለት ሕይወቴ ፍላጐቴ አንተው ነህ ፤
በመብራት በፀሐይ ሌት ተቀን የምሻህ ።
ሰዎች ለመብታቸው እንደሚታገሉ ፣
አፈቅርሃለሁኝ ባለኝ አቅም ሁሉ ።
ገሸሽ እንደሚሉ ከአጓጉል ሽንገላ ፣
መዝንልኝ አንተው የፍቅሬን ወለላ ።
እወድሃለሁኝ በሙሉ ስሜቴ ፤
በንጹሕ ልቦና እንደ ልጅነቴ ።
አፈቅርሃለሁኝ እስኪጠፋኝ ውሉ ፤
በዕድሜዬ ፈገግታ ፣ በእስትንፋሴ ሁሉ ።

ፍቅሬን ይለካ እንደሁ የእንባዩ ጠብታ ፣
እስኪ ድረስበት ቆጥረህ በትዝታ ።
ልክ እንደ መላዕክት የነፍሴ ክለላ ፣
ወድሃለሁ ይበልጥ ከ—ሞ—ት—ኩ—ም
በ—ኋ—ላ !

ሮበርት ብራውኒንግ ፣ በሚስቱ የፍቅር ግጥሞች ልቡ ከመነካቱ የተነሣ እሳትማ ለዓለም ኅብረተሰብ እንድታበረክታቸው አበረታታት ።

«እንዲያ ማድረግ አልችልም!» ነበር መልሷ ። «የጻፍኳቸው ለማንም አይደለም ሮበርት ፣ ለአንተ እንጂ—ላንተው ብቻ!»

«ጠቃሚ ናቸውና በድብቅ ሊያዙ አይገባቸ ውም» ሲል ወተወታት ። ማሳተም አለብሽ ። »

በምስጢር መጠበቃቸውን ብትመርጥም ፤ በመ ጨረሻ ተስማማችና ለኅትመት በቁ ። ሮበርት ብራው ኒንግ እንደገመተው ሥራዎቿ ዝናዋንና የባለቅኔነት ሞገስዋን በሚገባ አሳድጉላት ። ሒያሲያንም ግጥሞ ቿን «እንከን የማይወጣላቸው ውብ ሥራዎች ፣» ......«በእንግሊዝኛ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ከፍተኛውን ሥፍራ የሚይዙ የፍቅር ግጥሞች ...... «እንደ ፍቅር ሕያው የሆኑ ሥነ—ግጥሞች »...... እያሉ አወደሱ ላት ።...... በነዚያ ውብ ሥራዎቿም ስትታወስ ትኖራ ለች ።

አንድ ወንድ አንዲት ሴት ሲያፈቅርና ያችም ሴት ያን ወንድ ስታፈቅር ፣ መላእክት ከሰማየ ሰማያት ወርደው በጉጀዋቸው እየኖሩ የደስታ መዝሙራቸውን ያንቆረቁራሉ ።

ብራህማ

☆ ☆ ☆

ተፋቅሮ መለየት ምን አንጀት ቢያሳርር ፣
ሳይሻል አይቀርም ጭራሽ ካለማፍቀር ።

አልፍሬድ ቴኒስን

☆ ☆ ☆

ፍቅር ባክኖ ቀረ ብላችሁ አታውሩ ፤
ተኖ እንደማይጠፋ አትጠራጠሩ ።
ላንዱ ቢንጠፈጠፍ ለሌላው ይዘንባል ፤
ወይ እንደ ምንጭ ውሃ ሲንፎለፎል ውሎ ሲንፎ
ለፎል ያድራል ።

ሄንሪ ዎድስዎርዝ ሎንግፌሎ

☆ ☆ ☆

ቤተሰብ የሥልጣኔ እስኳል ነው ።

ዊል ዲዩራንት

☆ ☆ ☆

ጆን ሃዋርድ ፔይን

«ድግስ በማነፍነፍ ሲዞሩ ከማደር
በባዕዳን ጐራ ፤
ሆኖ እንደ ነገሩ በእናት አገር መኖር ነውኮ
እሚያኮራ!»

የጥቅምት ወር ጆን ሃዋርድ ተወልዶ ባደገበት መንደር ዛፎች በቀይና በወርቅማ ቅጠሎቻቸው የሚንቆጠቆጡበት ፤ ለስለስ ያለ ነፋስ ከአቅራቢያው ባሕር ሽው እያለ ፊት ዳሰስ በማድረግ የሚያነቃቃ በት ወቅት ነው ።

በዚያን ወቅት ጆን በመንደሩ ሳይሆን ደመና ማና የሚደብት አየር በሰፈነባት በፓሪስ ከተማ ነበር የሚገኘው ። ከቤተሰቡና ከባልንጀሮቹ ፤ ከሚያፈቅ ራትና ከልጅነት እስከ ዕውቀት ከኖረባት በሐረግ ከተጀቦነች ቤቱ ርቋል ። ከአገሩ ከወጣ ዘጠኝ ዓመ ታት አልፈውታል ። ታዲያ ምንም እንኳ ተዋናይና የድራማ ደራሲ ለመሆን በመብቃቱ በኑሮው ቢሻ ሻል ፥ ብዙ አገሮችን ቢጐበኝና አዳዲስ ባልንጀሮ ችን ለማፍራት ቢችልም ፥ ብቸኝነት ክፉኛ ያጠቃው ነበር ።

ከሚኖርባት አፓርተማ መስኮት ላይ ቆም ብሎ ከበታቹ መንገዱን አጨናንቀውና በደስታ ተሞል

ተው የሚጐርፉትን ሰዎች ተመለከተ ።እንዲያ በሚ ደብት ቀን እንኳ ፓሪስ ትፍለቀለቃለች ። ሁሉም ሰው የሚሔድበት ፣ የሚሠራው ተግባር አለው ። ሁሉም ይሥቃል ፤ ሰላምታ ይለዋወጣል ። ከቤቱ ከዘመዱ ፣ ከፍቅረኛው ዘንድ ለመድረስ ሁሉም ይጣደፋል ።...... እርሱ ብቻ የሚሔድበት ጨንቆት በክፍሉ ውስጥ ታስሮ ቀርቷል! ጭጋግማው አየር የቆሰለ መንፈሱን በይበልጥ አደማበትና የአገርና የወገን ናፍቆቱን ቀሰቀሰበት ።

ትዕግሥቱ ተሟጠበትና ከመስኮቱ ዘወር አለ ። ስለ ድሮው ሕይወቱ ማሰላሰሉ ፣ ስለ ቀየው በትዝታ መዋጡ ፣ ያች ያደገባት ቤት ዛሬ ምን እንደምትመ ስል በዐይነ ሕሊናው መቃኘቱ ፣ ስለ ከበቧት ዕፀዋት መዐዛ ማውጣት ማውረዱ የሚገታለት አልሆነም ። አንድ በአንድ ቁልጭ ብለው እየታዩት የልቡንና የአዕምሮውን ጓዳዎች በማጣበብ ስለሌላ ነገር ማሰብ ጨርሶ እስኪሳነው ድረስ አስጨነቁት ።

«ይህ 'አገር' የሚሉት ቃል ምን ዓይነት ምት ሐት አለው!» አለ በልቡ ። አስደሳችና አጽናኝ ትዝታዎቹን ፣ የቤተሰቡን ፍቅርና ጥንት ያዳምጣ ቸው የነበሩትን የምድጃ ዙሪያ ወጐች ሁሉ አኘሮ ጐደጐደበት — ያ'አገር' የሚሉት ቃል ።

ወዲያው «እኔም ሥራ አለኝ!» አለና ብዕሩን አንሥቶ ለሙዚቃ የሚስማማ ግጥም ማንቆርቆር ያዘ ። የሰቀዘውን የብቸኝነት ስሜቱን ፣ ብኸ ብኸ የሚሉበትን የልጅነት ትርዒቶች ፣ ከየዛፉ ቅርን

ጫፎች የሚያስተጋባውን የወፎች ዕልልታና ፉቱን ይዳስስለት የነበረውን የባሕር ሽውታ ...... በጨበ ጠው ወረቀት ላይ ለማፍሰስ ሞከረ ። የግጥሙንም ርዕስ «አገሬ ፣ እምዬ አገሬ» አለው ።

አገሬ ፣ እምዬ አገሬ

ድግስ በማንፍነፍ ሲዞሩ ከማድር
በባዕዳን ጐራ ፣
ሆኖ እንደ ነገሩ በእናት አገር መኖር
ነውኮ እሚያኮራ ።
የአገር ሰማይ ጥሪ ጐልቶ ያስተጋባል
«ኑ ወዲህ!» እያለ ፤
ዓለምን ቢዞሩ ደስታ የት ይገኛል
ይህን የመሰለ!
ከእናት አገር ወዲያ የሚበጅ ለጤና
ሰላም የሚለግስ ከወዴት ሊመጣ ፣ ከቶ የት አለና!
ከአገር ርቆ በሰው ምድር መኖር
ምንም ፋይዳ የለው ፣
ሀብቱም አይጨበጥ ዐይን ቢያጥበረብር
የሕልም እንጀራ ነው ።
እምዬ አገሬ ፍቅሯን እንዳትነፍገኝ
ብያለሁ አደራ ፤
የሚዘምሩልኝ ወፎቿም ይክበቡኝ
ስምተውኝ ስጣራ ።
የአዕምሮ ሰላምን ፣ የወፎች ዝማሬን ፣
ቀን ተሌት እሻለሁ ፤
በምድር ላይ ከሚገኝ ፣ ከምን ይሁን ከምን
አብልጬ እወዳለሁ ።

ከእናት አገር ወዲያ የሚበጅ ለጤና
ሰላም የሚለግስ ከወደጌት ሲመጣ ፡ ከቶ የት አለና!
በጠፍ ጨረቃ ወቅት ሳቋርጥ ባድማ ፤
እናቴ ተጨንቃ ——
ስለ እኔው ስታምጥ ከበር ላይ ቆማ —
ያችኑ ጨረቃ —
እየተማጠንች በዛፎች መካከል በዐይኗ ስትፈልገኝ
ዛሬም ይታየኛል ፤
ግና መዓዛዋ በደስታ እሚያውደኝ
ካጠገቤ ርቋል ።

ከእናት አገር ወዲያ የሚበጅ የጤና
ሰላም የሚለግስ ከወደጌት ሲመጣ ፡ ከቶ የት አለና!
ፍቅርን ከሚያላብስ ከአባት ፊት ፈገግታ
በድምቀት የሚልቅ ፤
ሰመመን ከሚያፈልቅ ከእናት እጅ አለኝታ
ምናለ የሚሞቅ?
ከአገራቸው ወጥተው በየድግሱ ቤት
ያሻቸው ይዘሩ ፤
እኔስ በአገሬ ፡ ድሃ በቆምኩበት
ልባል እሸሩሩ ።

ከእናት አገር ወዲያ የሚበጅ ለጤና
ሰላም የሚለግስ ከወደጌት ሲመጣ ፡ ከቶ የት አለና!
የትም ደረስኩ የትም ፤ አገዬ ችግሬን
ወዳንች አዘግማለሁ ፤
ዐይኔ የራበውን የአለኝታ ጸዳልሽን
በጣም ናፍቄአለሁ ።

ካጠገብሽ ላልርቅ ምን ችግር ቢመጣ
ቃል ገባልሻለሁ ፤

ምንም ልሁን ምንም ከጉያሽ ላልወጣ
እምልልሻለሁ ።

ይህን ግጥም በጻፈ በዓመቱ ጆን ፔይን ወደ አገሩ ተመለሰ ። በአገሩ ምድር ላይ ባቀረበው የመጀመሪያው ድራማ ውስጥ ይህ ግጥሙም በሙዚቃ ተቀንባብሮ በአንዲት ዝነኛ ድምፃዊት አቀንቃኝነት ለመድረክ በቃ ። ሴትየዋ ስታዜመው ዐይኖቿ በዕንባ ተሞልተውና ድምጿ ተስረቅርቆባት አልቅሳ አድማጮቿን አስለቅሳባቸታለች ።

ዜማው ተወዳጅነትን ወዲያውኑ አተርፎ...... መርከበኞች ወደብ ሲለቁ ፣ እናቶች ልጆቻቸውን ሲያስተኙ የሚያንጐራጉሩት ፣ ተማሪዎች በት/ቤት ፣ እስረኞች እንኳ በየጓዳቸው የሚያወርዱት ዜማ ለመሆን ቻለ ።

ወደ አገሩ ከተመለሰ ከአሥራ ስምንት ወራት በኋላ ጆን ፔይን ዐረፈ ። በሕይወት ዘመኑ ብዙ ድርሰቶችን ቢያፈራም ፣ ስሙን ሲያስጠራለት የሚኖረው ይህ «ሆም ስዊት ሆም» የተሰኘው ዓይነተኛ ሥራው ነው ። ወደ ብዙ ቋንቋዎች ተተርጉሞ በአያሌ አገሮች ውስጥ ሲዘመር ከመቶ ዓመታት በላይ ቆይቷል ። አገራቸውንና ቤተሰባቸውን የሚያፈቅሩ እስካሉ ድረስም ግለቱ አይቀዘቅዝም ።

ደስታ የምትገኘው በገዛ ጐጆ ምድጃ ዙሪያ ነው ። ከሌላ ሰው የአትክልት ሥፍራ እንደ አበባ አትቀጠፍም ።

ዳግላስ ጀሮልድ

☆ ☆ ☆

የዕለቱ መራወጥ ጋብ ሲል ላንዳፍታ ፣
የእፎይታ መንፈስ ሲሠፍን ወደ ማታ ፣
«ቤቴ! ቤቴ!» እያለ የሰው ልብ ያዜማል ፣
ከቤት ወዲያስ ፈዋሽ ከቶ የት ይገኛል!

ቶማስ ሁድ

☆ ☆ ☆

የትፈጥሮ ጓዳ ልጅነት ያሰሰው ፣
የደኑ በረከት ፣ የወንዙ ፣ የሜዳው ፣..........
ያ ደማቅ እይታ የሩቅ ዓለም ትርዒት ፣
ፀትዝታ ታዝሎ ድቅን ይላል ከፊት ።

ሳሙኤል ውድዎርዝ

☆ ☆ ☆

ሳም ዎልተር ፎስ

«ሁሉ እንዲያጋጥመኝ ሁነኛ ጓደኛ
ልኑር ጐዳና ጠርዝ እንደ መንገደኛ ።»

ሳም ፎስ የእግር ጉዞ ይወዳል ። በአንድ ሞቃት ዕለት በሐሳብ ተውጦ ያለ ወትሮው ብዙ ተጓዘ ። የፀሐይዋ ግለት የተሰማውና ርቆም መሔዱን የተገነዘበው በድንገት ነበር ። ከመንገዱ ጠርዝ ላይ አንድ የኮራ ዛፍ ጥላ ማረከውና ከሥሩ ዐረፍ ሊል ወሰነ ።

እንደ ደረሰም ከዛፉ ግንድ ላይ ማስታወቂያ ተለጥፎ በማየቱ ተገረመና ጠጋ ብሎ አንብቦት በደስታ ተፍነከነከ ። «እዚህ ግቢ ውስጥ እንደ ኩል የጠራች ምንጭ አለች ። ከጠማዎት ጐራ ብለው ይጐንጩላት» የሚል ነበር ያ ማስታወቂያ ።

ፎስ ወደ አጥር ግቢው ገብቶ ምንጭዋን አግኝቶ ፥ ከቀዝቃዛ ውሃዋ እያፈሰ እስከሚበቃው ከተጐነጨ በኋላ ፥ ዘወር ዘወር በማለት ሲቃኝ ከምንጭዋ ባሻገር አንድ አግዳሚ ወንበር ተመለከተ ። «ከደከመዎት ዐረፍ ብለው ይዝናኑ» የሚል ጽሑፍ ተለጥፎበት ነበርና ሳያቅማማ ቁብ አለበት ። በአቅራቢያውም ፥ «ከአሰኘዎት ከምርቱም ይቅመሱ» የሚል

እንዴት ፍጡር ካዳንሁ
ባዘን የምትደማ
ኖሬያለሁ እላለሁ
ምንም ሳላቅማማ።
ውጋት የሰቀዛት
እንዲት ነፍስ አግኝቼ ፤
ከስቃይ ባወጣት
እጆቼን ዘርግቼ ፤
ወይም እንዲት ድምቢጥ
ከመሬት አንሥቼ
ጐጆዋ ባስቀምጥ
እስትንፋስ ዘርቼ ፤
ምንም አላፍርበት
ኖሬአለሁ ለማለት ።

ኤሚሊ ዲክንሰን

☆ ☆ ☆

በዚህ መዲናችን በየዕለት በሚያድገው
አለኝ አንድ ጓደኛ ካንጀት እምወደው ።
በልጅነት ጊዜ በየዋሁ ዘመን
የንጹሕ ልቦና ፍቅር እያባነነን ፤
የእኔ እርሱ ቤት መሮጥ ፤ የእርሱ እኔ ቤት መብረር
ሲያበራ ይኖራል በልባችን ማኅደር ።
ልክ እንደዚያው ዘመን ዛሬም ‘ወደዋለሁ ፤
ስለእርሱ ማሰቤን እንደሚያውቅልኝም እተማመናለሁ ።
ግና ምን ያደርጋል!......ሩጫ ያዝንና በየባኩላችን

ሌት ተቀን ስንዳክር ለመቋቋም ኑሮን ፡
ስንቧጥጥ አቀበት ለዝና ስንማስን ፡
ዛሬ ነገ ስንል ቀርቶ መጠያየቅ ፤
መብስከስክ አተረፍን አጉል መነፋፈቅ ።
እንደ ደራሽ ውሃ ጊዜ እየጐረፈ ፡
ጭራሽ ሳንተያይ አንድ ዓመት ዐለፈ ።

«እስቲ ነገ ሔጄ ዐይኑን አየዋለሁ ፤
ስለ እርሱም ማሰቤን አጫውተዋለሁ»

በነጋ በጠባ እያልኩኝ ብመኝም
ከሕልም ሩጫዬ ፋታ አላገኘሁም ።
ቀኑ ሳምንት ሆኖ፡ሳምንቱ ወር ወልዶ ሔደ እየነጐደ ፤
ያለያየን ጉድባም ሰፋ ፡ ጐደጐደ ።
ታዲያ አንድ ቀን መጣ ሳላስበው ማልዶ

«......እገሌ ሞተ!......»

እሚል አሠቃቂ መርዶ ።
ይኸው ነው ዕጣችን—በመጨረሻ ላይ የሚገጥመን
አሳር ፡
የቅርብ ሩቅ ሆኖ ያንጀት ባልንጀራ በድንገት
ሲሰወር ።

ቻርልስ ሐንሰን ታውን

☆ ☆ ☆

ባልንጀራ ለሌለው ሰው ዓለማችን ጭልጥ ያለ በረሃ
ትሆንበታለች ።...... ደስታውን ለባልንጀራው የሚ

ያጋራ ይበልጥ እንደሚደሰት ሁሉ ሐዘኑንም ለባል ንጀራው በማካፈሉ የማይጽናና ሰው የለም ።

ፍራንሲስ ቤከን

☆ ☆ ☆

ወደ ባልንጀራህ ቤት አዘውትረህ ተመላለስ ። አለበ ለዚያ መንገድህን ዳዋ ይውጠዋል ።

ራልፍ ዋልዶ ኢመርሰን

☆ ☆ ☆

ክፍል ስድስት

እርጅናና የጉዞ ፍጻሜ

ባሕር ጸጥ እንደሚል ወጀቡው ሲጠፋ
እኛም እንሰክናለን ስሜት ሲያንቀላፋ ።
ይታየናል ያኔ የጉራ ባዶነት ፣
ላላፊ ለጠፊው የተከራራንበት ።
ያንገፐብብ በነበር የፍቅር ዳመና
ተጋርዶ የነበር የወጣት ሕሊና
ሁሉንም ያየዋል በዕድሜ ብልጽግና ።
ቀፎ መስሉ አካል ፊራሹ ሥጋችን
ሰውነት ተብዬው የነፍስ ጓዳችን
እንደ እና ጉጆ ጽልመት ቢውጠውም
መሠረቱ ከድቶት ግድግዳው ቢያዘምም
የብርሃን ጭላንጭል ዕድሜ እሚለግሰው
አለው ልዩ ጸዳል እሚገናጸፈው ።
በሕይወት ማብቂያ ላይ ከሽለብታ በፊት
ድክመት ኃይልን ወልዶ ፣ ብስለት ታክሎበት
ያለፈው ከመጪው እሚመዘንበት
እርጅና መድረክ ነው ቆም እሚባልበት ።

ኤድመንድ ዋለር

በዘመን ርዝማኔ መደናገጥ አይገባም ። ዕድሜ ታላቅ ጸጋ ነው ። ኢያሴ በረከቶችም አሉት ። «እያንዳንዱ የሕይወት እርከን ሰፊ አዝመራ አለው ። ከሁሉም የሚልቀው የመከር ዘመንም እርጅና ነው» ብኋል ሲሰሮ ።

ሰው በዕድሜው እየገፋ ሲሔድ አዕምሮው በይበልጥ እየዳበረ ችሎታውም በዚያው መጠን እንደ ሚበለጽግ ታሪክ ይመሰክራል ። ማይክል አንጀሎ ዕውቅ ሥራዎቹን በሰማኒያ ዘጠኝ ዓመቱ ይደረድር እንደ ነበር ሁሉ ገተ የተባለውም ደራሲ «ፎስት» የተሰኘውን ጽሑፉን ሁለተኛ ክፍል ያጠናቀቀው በሰማኒያ ሁለት ዓመት ዕድሜው እንደሆነ ይነገራል ። ዋግነር «ፖርሲፋል» የተሰኘውን ሙዚቃውን ያንቆረቆረው በስድሳ ዘጠኝ ዓመቱ ሲሆን ፣ ቮልቴርም «ካንዲድ»ን የጻፈው በስድሳ አምስት ዓመቱ ነበር ። ሃንድል ጣፋጭ ዜማዎችን ፣ ሎንግፌሎም ሕያው ሥነ ግጥሞችን በሰባ ዓመታቸው ገደማም ያፈልቁ እንደነበር ይወሳል ።

ዋልተር ፒትኪን «ሕይወት የሚጀምረው ከ40 ዓመት ዕድሜ በኋላ ነው» በሚለው ጽሑፉ ውስጥ ከዓለማችን ዕውቅ ሥራዎች ከ0ሥሩ እጅ ዘጠኙ የተከናወኑት በዕድሜያቸው በገፉ ሰዎች እንደሆነ ይጠቁማል ። በመሆኑም አንድ ያልታወቀ ባለቅኔ ፦—

«እርጅና ጥላ ነው ፤
አዕምሮ እሚፈጥረው ።
ሕልም ሲደባዝዝ ፤
ተስፋ ሲቀዘቅዝ ፤

ወደፊት እንዳያይ ሕሊና ሲጋረድ፥
የምኞት ነበልባል ሲለወጥ ወዳመድ ፤
ያኔ እርጅና መጣ ፤
አስከትሎ ጣጣ ።
ከሕይወት ዛፍ ፍሬ ቢለቀም ጣፋጩ ፤
ሣቅና ጨዋታ ዘዋትር ቢመነጩ ፤
በፍቅር እየሞቀ
ጎጆ ከደመቀ ፤
ዕድሜ ቢጋልብም በአቀበት ጎዳና ፤
ጭራሽ ዝር አይልም—አይመጣም እርጅና »
በማለት ያሠፈረውን መልእክት በውል ማጤኑ ተገቢ ነው ። በዚህ ርዕስ ላይ ሌሎችስ ምን ይላሉ?

☆ ☆ ☆

ማርኩስ ቱሊዩስ ሲሰሮ

«ተውኔት በመደምደሚያ ትርዒት እንደሚዘጋ ሁሉ የሕይወት ጉዞም በእርጅና ምዕራፍ ይቋጫል ።»

ጥንታዊት ሮም በሞራል ድቀት በተበከለችበትና ዩሊዮስ ቄሳር በተገደለበት ዘመን ይኖሩ ከነበሩት ዕውቅ ሰዎች መኻል አንዱ ሲሰሮ ነበር ።

ማኅበራዊ ተሳትፎውን የጀመረው በወጣትነት ዕድሜው እንደ መሆኑ በሐያ አምስት ዓመቱ ዝነኛ ንግግር ዐዋቂ ሆነ ። በዓቃቤ ሕግነት ፡ ኋላም በሕግ አማካሪነት ከሥልጣን ወደ ሥልጣን በፍጥነት እየተሸጋገረ በሪፐብሊካኑ ፓርቲ ውስጥ ታላቅ ሥፍራ ለመጨበጥ በቃ ።

ሆኖም በሞያው ተክኖ ድምፁ በሚያስተጋባበት ወቅት ብዙ ጠላቶችን አፈራ ። ምንም እንኳ በአድማው ተካፋይ ባይሆንም ፡ ዩሊዮስ ቄሳር ሲሞት በፖለቲካ ተፃራሪዎቹ ግፊት እርሱም ከሥልጣኑ እንዲወርድ ተገደደ ።

ከሥራው ቢገለልም እንዶበቱ አልታሰረም ። ወደ ሥነ ጽሑፍና ፍልስፍና አዘንብሎ ያካበተውን ዕውቀት በማዳበር በረከቱን በወረቀት አሠፈረ ።

ካፉ የተሰኘ አዛውንት በፈጠረበት ባአንድ ዕውቅ ሥራው ውስጥ እንዲህ ይላል ።

«ሰማኒያ አራተኛ ዓመቴን ይዣለሁ ።...... እንደ ምታዩኝ ዕድሜ አላሸመደመደኝም ፤ ወይም ቅስሜን አልሰበረውም ። ከአደባባይ ፣ ከወዳጆቼ ...... ወኔዬ አልተሰወረም ። ምክንያቱም 'ረጅም የአዛውንት ዕድሜ እንዲኖርህ ቀደም ብለህ እርጅናን ተያያዘው' የሚለውን የሞኝ ፈሊጥ አልቀበለውም ። በበኩሌ ከጊዜዬ በፊት ሽማግሌ እየተባልኩ ዕድሜዬን ከም ገፋ የሽምግልናዬ ዘመን አጠር ቢልልኝ እመርጣ ለሁ ።

«በሕይወት ጉዞ ላይ የመሽቀዳደሚያው ክልል ጠባብ ነው ። አቅጣጫውንም ተፈጥሮ አንድ ወጥ ብቻ አድርጋዋለች ። ለእያንዳንዱ እርከንም የየራ ሱን በረከት ለግሳዋለች ። ስለሆነም የልጅነት ጮር ቃነት ፣ የጉርምስና ግለት ፣ የመካከለኛ ዕድሜ ቆፍጣ ናነት ፣ የሽምግልና ዘመን ብስለት — እያንዳንዱ እርከን የሚያፈራው የተፈጥሮ ጸጋ በየወቅቱ መሰብ ሰብ አለበት ።

«የእርጅናን ደካማ ጐን በሥራ በመጠገን ፣ እንደ በሽታ ሁሉ ፣ እርሱንም መቋቋም ይኖርብናል ። በመ ጠነኛ እንቅስቃሴ ጤንነታችንን መንከባከብ ይገባ ናል ። ለጥንካሬ መልካም ምግብና መጠጥ አስፈ ላጊዎች ናቸው ። ታዲያ ጉልበት ብቻውን ፋይዳ የለውም ፤ አእምሮና መንፈስም ከዚያ በበለጠ ደረጃ መጐልበት አለባቸው ። አለበለዚያ ሕይወት ፣ ላም

ባው እንዳለቀበት ኩራዝ ፡ ጭል ጭል ማለት ትጀም ራለች ።

«በሊጋነቱ ወቅት ብስለት የሚታይበት ጉል ማሳ እንደሚማርከኝ ሁሉ ባሽምግልናው ዘመን የወ ጣትነት ግለት የሚሰማው አዛውንትም ይስበኛል ። ይህን አባባል በውል የሚያጤን ሰው በእካል እንጂ በመንፈስ አያረጅም ።

«ተውኔት በመደምደሚያ ትርዒት እንደሚዘጋ ሁሉ የሕይወት ጉዞም በእርጅና ምዕራፍ ይቋጫል።»

«ቅንና አስደሳች ሕይወትን በውስጡ ማካበት ለሚሳነው ፍጡር ማንኛውም የዕድሜ እርከን ገደል ይሆንበታል ።»

ዩሊዮስ ቄሳር በሞተ በዓመቱ ሲሰሮም ተገደለ ። ወርቅ እንደበቱን እስከ ምንምጊዜም የዘጉ መስሏ ቸው ጠላቶቹ ራሱንና እጆቹን ቆርጠው በአደባባይ ከንቸሯቸው ።

ግን ተሳስተዋል ። ከንግግሮቹ ፤ ከደብዳቤዎቹ ፤ ከመጣጥፎቹና ከማስታወሻዎቹ ጥቂቶቹ ቢጠፉና ጥቂቶቹ ደግሞ በተንኮል ቢወድሙ አብዛኞቹ ተሰ ባስበው በቤተመዘክር ውስጥ በእንክብካቤ ተይዘ ዋል ። የኖረበትን ዘመን ገጽታ ቦግ አድርገው ያሳ ያሉ ። እስከ ዛሬም አያሌ ትውልድን ያወያያሉ ።

ክረምትን ቢጠቁም የጸጉሬ መሸበት
በልቤ አምቄያለሁ የጸደይን ውበት ።

ቪክቶር ሂዩጐ

☆ ☆ ☆

ዝግተኛ ሒደት ከመሆኑ የተነሣ ፡ ከአንቀልባ እስከ መቃብር የሚኖረንን ለውጥ ፤ ልክ ከንጋት እስከ ምሽት እንደምናሳየው ዕድገት እምብዛም ልብ አን ለውም ።

ቻርልስ ዲክንስ

☆ ☆ ☆

በዕድሜ ማከተሚያ ላይ የሚፈልቅ ስሜትን መግለጽ በጣም ያዳግታል። ግን ብልጭ ያለልኝን አንድ ሐሳብ ልሰንዝር ።...... በፈረስ ግልቢያ የተሠለፉ ተወዳዳሪ ዎች ከመጨረሻው ግባቸው እንደ ደረሱ ቀጥ አይ ሉም ። ከማረፋቸው በፊት በሶምሶማ ወዲያና ወዲህ እንደሚንቀራጠጡ ሁሉ ፤ ሰውም በሕይወት እስካለ እንቅስቃሴውን መቀጠል ይኖርበታል — መኖር መሥራት ነውና ።

ኦሊቨር ዌንዴል ሆምስ

☆ ☆ ☆

ሳልገባ አጉል እልህ
ከዚያም ሆነ ከዚህ ፤

ተፈጥሮን አቅፌ ፤
ጥበብን ደግፌ ፤
ከሕይወት እሳት ዳር እጄን አሙቂያለሁ ፤
እሳቱ ሲጠፋ ፤
ብርዱ ሲያንሰራፋ ፤
ጨርቄን ማቄን ሳልል እሰናበታለሁ ።

ዋልተር ሳቬጅ ላንዶር

☆ ☆ ☆

እርጅና የሚያስከትለውን ትካዜ ፡ ጭንቀትና ድካም ለመከላከል ዓይነተኛው መድኀን አእምሮን እንደ ላስቲክ በመለጠጥ የአስተሳሰብ አድማስን ማስፋት ነው ።......

ቤራን ዎልፍ

☆ ☆ ☆

ስር ዊሊያም መሎክ

«የምሽት ጥላ በዙሪያዬ እየረዘመ ቢሔድም ልቤ ማለዳን እንዳረገዘ ነው ።»

በዕድሜ የገፋው ዊሊያም መሎክ ለሚደረግለት ክብሬታ አጸፋውን ለመመለስ ከተቀመጠበት ወን በር ረጋ ብሎና ፈገግታ ተላብሶ ብድግ አለ ። ዕለቱ፡ ዕውቅ ሰዎች ተሰባስበው የሚያከብሩለት ሁነኛ የሕይወት ምዕራፉ ነበር — የልደት ቀኑ ። ዘጠና አምስተኛ ዓመቱን ተቆናጥጧል ።

«ዘጠና—አምስት» በማለት የጀመረውን ንግ ግር አቋርጦ በሐሳብ ተዋጠ፣ ጭብጨባው ጋብ እስ ከሚልለት ድረስ ። «አዲስ ነገር ይመስላል ። ለብዙ ዎቻችሁም ሳላረጅ አልቀረሁም ። ግን ባይገርማ ችሁ እርጅና ፈጽሞ አይሰማኝም ። ለእኔ የዛሬው ዕለት ከሌሎቹ የልደት ቀኖቼ እምብዛም የተለየ አይደለም ። አንድ ሌላ ዓመት ወደኋላዬ ጣል እንዳ ደረግሁ ሁሉ ብሩህ ዓመታት ከበስተፊቴ ይታዩ ኛል ።......»

ይኸው ነበር የዘወትር እይታው ። «ጣፍጭ ሕይ ወት ያለው ምንጊዜም ወደፊት ነው — ፊቀቅ ሲሉ»

የሚለው ፍልስፍናው ነበር ብርታት የሚሰጠው ፤ በወጣትነት መንፈስ በየጊዜው የሚያድሰው ።

መናገር ሲጀምር አዳራሹ ረጭ አለ ። ሰር ዊሊያም መሎክ ከረጅም ዘመን ልምዱ ምን ያፈልቅ ይሆን? ከዘጠና አምስት ዓመት የዕድሜ ባለጸጋነቱ ለወዳጆቹና ለሥራ ባልደረቦቹ የሚያበረክተው ምን ይሆን?

የድምፁን ጥራትና ቃና ሕይወት አፍቃሪነቱን ፣ ሥራና ሰው ወዳድነቱን በሚገልጽ አኳኋን ቃኝቶ «አሁንም እየሠራሁ ነው — እጄን ከእርፍ ፣ ግን ባሬንም ፊት ለፊቴ ከማየው የሕይወት ምዕራፍ አቶ ጠፍኩም ። የምሽት ጥላ በዙሪያዬ እየረዘመ ቢሔድም ፣ ልቤ ማለዳን እንዳረገዘ ነው ። ከአንድ ምዕተ ዓመት ወደ ሌላው ለመሸጋገር በቅቻለሁ ። በተለያዩ ተግባራት ተሰልፌያለሁ ፤ ከተፈጥሮና ከሰዎች ጋር ተዋሕጃለሁ ። የሕይወትን አሳት ሞቂያለሁ ።

«የምስክርነት ቃሌም ይኸው — የደስታ አዳራሽ ከበስተፊቴ እንጂ ፣ ከበስተኋላዬ አይደለምና በየዕለቱ ቀና እያልኩኝ ጉልላቱንና ከፍክፋቱን አሻግሬ አያለሁ ። በልቤ ማኅደር ያመቅሁት ትዝታ የእኔው ነው ። የአካባቢዬ የተፈጥሮ ጸጋ ፣ አበቦቹ ፣ መጻሕፍት ፣ ሥዕሎች ...... እነዚህ ሁሉ የኔው ናቸው ። ከማንኛውም ነገር ሁሉ የሚልቀው የአንድነት ባልንጀርነት በረከትም አልተለየኝም ። የጊዜ ጉብታ እየጋረደን ለመገንዘብ ይሳነን ይሆናል እንጂ ፣ ከሕይወት

ጣዕም በእጅጉ ጣፋጭ የሆነው ሁላችንንም የሚጠ ብቀን ወደፊት ነው ።»

«የሰር ዊሊያም መሉክ ቁምነገር የተሞላበት ንግግር የእያሌ አዛውንትን ሸክም አቃልሏል ። መን ፈሳቸውን በማደስ የተበተባቸውን የፍርሃት ወጥ መድ በጣጥሶላቸው የመኖርን ትርጉም በውል እንዲገ ነዘቡና አዲስ ሕልም እንዲያጠነግኑ ረድቷቸዋል ።

የግንባራችንን መሸብሸብ ልባችን አይወቀው ።

ጀምስ ጋርፊልድ

☆ ☆ ☆

ብዙ ሰዎች የመጀመሪያ ሽበታቸውን ሲያዩ ይደነግጣሉ ። የጸጉር ግራጫ መሆን ሊያስደነግጥ አይገባም ። አረንጓዴ ወይም ሰማያዊ ከሆነ ግን ሐኪም ማማከሩ ይበጃል ። በሽበታችሁ አትፈሩ በት ። በኩራት ተጎናጸፉት—እንደ ክብር ዓርማ ። ቅስፈት በሰፈነባት ዓለማችን ረጅም ዘመን አቋርጣ ችሁ ለዚህ በመድረሳችሁ ዕድለኞች ናችሁ ።

ዊሊያም ላዮን ፊሊፕስ

☆ ☆ ☆

ጉዞዬን እገፋለሁ ካመት ዓመት እያልኩ ፤
ግንባሬን ሳላጥፍ መንፈሴን እያደስኩ ።
ብዙም ሳልጣደፍ ፤ ካሳማዬም ሳልርቅ ፤
ላመለጠኝ ጉዳይ ብዙም ሳልጨነቅ ።
ምን ይገጥመኝ ይሆን በሚል አጉል ሥጋት
ከፊቴ ያለውን ሳልጋርድ በፍርሃት ።
ልቤን ሰፋ አድርጌ በደስታ ሞልቼ ፤
እንጻጽራለሁ የጥንቱን ከዛሬው ሚዛኔን አንሥቼ ።
መንገዱ ጨርቅ ይሁን ፤ ቢሻው ይሁን ዳገት ፤
ወይ ተዳፋት ይሁን አሳር የበዛበት ፤
ሁሌም ይታየኛል የልጅነት ሕልሜ
ከጓደኞቼ ጋር በአዲስ ጉልበት ቆሜ ፤
እርጅናን ሳልፈራ ሕይወቴን መራለሁ ፤
ግቤም እንደሚሠምር በሚገባ ዐውቃለሁ ።

ሄንሪ ቫን ዳይክ

☆ ☆ ☆

የውሽንፍር ግፊት ወፍ እንደማትፈራ ፤
ለዕድሜ ማዕበልም አልሰጠውም ሥፍራ ።
መንገድ ጠቋሚዬን በትኩረት እያየሁ ፤
ሰንጥቄው እንደማልፍ እተማመናለሁ ።
የነበረኝ ስሜት በአፍላ ልጅነቴ ፤
ዛሬም አብሮኝ አለ አልጠፋም ከሕይወቴ ።
ጉዞ ቀጥላለሁ ያለምንም ሥጋት ፤
ወደቤ እስክምደርስ እሮይ ከምልበት ።

ራልፍ ዋልዶ ኢመርሰን

☆ ☆ ☆

እኔ አረጀሁ የምለው በያዝኩት ዕድሜዬ ላይ ምን ጊዜም በሥራ አምስት ዓመት ካከልኩበት በኋላ ነው ።

በርናርድ ባሩክ

☆ ☆ ☆

ሕይወት የምትመዘነው ፣ ኪፍ ያለ ዋጋ እንደሚያወጣ አልማዝ ፣ ባስፋቷ ሳይሆን በክብደቷ ነው ። ስለዚህ ሕይወታችንን በተግባር እንጂ በዘመን ብዛት አን ለካ ።

ሴኔካ

☆ ☆ ☆

ያብከነከኑኝን ጥቃቅን ሐሳቦች ትናንት በተንኳ ቸው ፤ ባውላላ መስክ ላይ ፣ በባሕር ፣ በደን ውስጥ
እርግፍ አረግኋቸው ።
ለስለስ ያለ ነፋስ ከዛፍ ቅጠሎች ጋር ከሚጫወትበት ፤
እምቦሳና ጊደር እየተጠራሩ ከሚቦርቁበት ፤
የንቦች ዝማሬ ፣ የወፎች እልልታ ከሚያስተጋባበት ።
ምኼ ቀብሬያለሁ ጭፍት ፍርሃቴ የጫነኝን ዕዳ ፤
አፍሳለሁ በየዕለት የመንፈስ ቀለቤን ከተፈጥሮ ጓዳ ።
ሚዶው ወንዛወንዙ ፣ ጋራው ሽንተረሩ ከሚያማል ልበት ፤
የከሴ ፣ የጦስኝ ፣ ያደስ ፣ ያልባብ መዓዛ ከሚመነ ጭበት ፤

የእንኮይና ኮሽም ፥ ያጋም ቀጋው ጥቅሻ ከሚማ ርከበት ።

ያልታወቀ ባለቅኔ ፤

☆ ☆ ☆

«ኖሮ ኖሮ ከቤት ፥ ዞሮ ዞሮ ከመሬት የሚቀር የለም» እንዲሉ ፥ የመጨረሻው ምዕራፍ ስለዚሁ የጉዞ ፍጻሜ የሚያወሳ ይሆናል ። ሞት ወይም ዕረፍት ስለሚባለው ስለዚህ ዓቢይ ጉዳይ ብዙ ተብሏል ።

«እያንዳንዱ አንቀልባ 'ከየት?' ፥ ሲል እያንዳዱ ቃሬዛም 'ወዴት?' እያለ ይጠይቃልና ተንሰቅስቆ የሚያለቅስ ፡ ማይም ሆነ ምሁር ፥ ምላሹን ይስጥ!» ሲል ሮበርት ኢንገርሶል እንዳስቀመጠው ሁሉ የአ መለካከት ልዩነትም ይኖራል ።

ሆኖም ብዙ ሰዎች የሚስማሙበት አንድ ነጥብ አለ ። ይኸውም የሚከተለው ነው ።

«......ማንም ሰው ከቀኑ በፊት አይሞትም ። ከል ደትህ በፊት የነበረው ጊዜ ያንተ እንዳልሆነ ሁሉ ትተኸው የምትሔደውም ያንተ አይደለም ። ሌሎች እንዳደረጉልህ ሁሉ፥አንተም ሥፍራ ልቀቅላ ቸውና መስተንግዶው እንዳማረለት እንግዳ ወደ ማረፊያህ አምራ ።...... በዓለም—አቀፋዊ ሕግነቱ ሞት ሕይወትም ነውኮ!» እንዲህ ያለው ሚሼል ደ ሞንቴኝ ሲሆን ጆናታን ስዊፍት የተባለ ደራሲም «ሞትን ያህል የተለመደና የማይቀር ዓለም—አቀፋዊ እውነታ ለሰው ዘር ጥፋት እንደ ተደነገገ እኩይ ሕግ

ተቆጥሮ መወገዙ ይገርማል» በማለት ትዝብቱን አስፍሯል ።

☆ ☆ ☆

መጨረሻ ቀኔን እንደው በውል ባውቃት ፤
በአትክልቱ መካከል በተጠባበቅኋት ።
እየተንከባከብኩ የአበቦቹን ጤና ፤
እኔ ከሔድኩ ወዲያ ቀሪ ናቸውና ።
ከዚያም ዐረፍ ብዬ ካንድ ዛፍ ጥላ ሥር ፤
ወፎች ፤ ቢራቢሮች ፤ ንቦችን ስቆጥር ፤
ቀጥሎም ብቅቢሉ ጥቂት ወዳጆቼ ፤
ከገጾናቸው ሆኘ የልቤን አውጋቼ ፤
በአትክልቱ መካከል እየተንሸራሸርን ፤
ስለ አበቦች ውበት ስለ ዓለም ምንነት እየተወያየን......
መጨረሻ ቀኔን እንደው በውል ባውቃት ፤
ምንኛ በረካሁ እንዲህ አሳልፌያት!

አን ሂግንስን

☆ ☆ ☆

የምድር ላይ ቆይታህን ከተፈጥሮ ሕግ አንጻር ተመል ከተው ። አንድ የበሰለ ፍሬ ሕይወት የዘራለትን ዛፍና አቅፎ ያኖረውን ቅርንጫፍ መርቆ እንደሚወድቅ ሁሉ ፤ አንተም ስንብትህን እንደዚያው ቁጠረው ።

ማርከስ አሬሊየስ

☆ ☆ ☆

ጀምስ ጐርዶን ጊልኪ

«የሞትን ምንነት ተገንዝቦ በጸጋ መቀበልና ሐዘ ንን መቆጣጠር ከማንም ሰው የሚጠበቅ ዐቢይ ተግባር ነው ።»

ጀምስ ጐርዶን ጊልኪ በረጅሙ ተንፈሰና ያነብ የነበረውን ደብዳቤ መልሶ ጠረጴዛው ላይ ወረወ ረው ። እንዲያ የመሰለ ደብዳቤ በአንዲት ሳምንት ውስጥ ሲደርሰው ይህ ሁለተኛው ነበር ።

በዚያን ዕለት ያነበበው ደብዳቤ ከአንዲት ወጣት የተላከለት ሲሆን ፡ ዕጮኛዋ በጦርነት ላይ በማረፉ የተሰማትን መሪር ሐዘን ያፈሰሰችበት የእ ራታ ድምፅ ነበር ።

«እለኝታዬን አጣሁ» ይላል ደብዳቤዋ ። «ከእ ንግዲህ ወዲያ መኖር ለእኔ ምንም ትርጉም የለውም ። ከሁሉም አብልጬ የማፈቅረውን ብቸኛ መከታዬን ካጣሁ ምኑን ኖርኩት? ምን ተስፋ አለኝ?.....»

ጀምስ ጐርዶን ጊልኪ የአንድ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ፡ ሲሆን ከሞያው አኳያ ምክሩን አበክረው የሚሹ እያሌ ደብዳቤዎች ይጐርፉለታል ። የዚህች ወጣት ደብዳቤ ግን ፡ ከየትኛውም በበለጠ ልቡን ነካው ። «ኢባክዎ ይርዱኝ!» ብላዋለች ያች በሐዘን

የምትቆራመድ ሲጋ ፍጡር ። «ምን እንደምሆን ፡ ምን እንደማደርግ እባክዎ ይንገሩኝ ።......»

ጥሪዋ ከበደው ። ታላቅ ፈተናም ሆነበት ። የገጠማት የሕይወት እንቅፋት ቀላል አልነበረምና የምትሻውን ምርኩዝ ለማስጨበጥ ማማጥ ጀመረ ።

«ራስሽን አታስጨንቂ» አላት በደብዳቤው መግቢያ ላይ ። «ሐዘን በምሬትና በእልህ አይገፋም ። ዕጮኛሽን ማጣትሽ እውን ነውና ከዚያ አኳያ የነበረሽን ሕልም ፊትሽ ላይ እንደ ተደረገመብሽ በር ቆጥረሽው ወደ ሌላ አቅጣጫ ዞሪ ። እንደ ገና ወደ ወትሮው ተግባርሽ ተመለሽ ። አዳዲስ ጓደኞች ፡አዳዲስ ሕልሞች ፍጠሪ ......» ሲል ምክሩን ለገሣት ።

በዚያ አሠቃቂ የጦርነት ዘመን ሞት በትሩን ያሳረፈባቸውና በሰቀቀን የተሸማቀቁ አያሌ ሰዎች ስለነበሩ ፡ ወደ እነርሱ ጠጋ እንድትል መጠቆሙ ነበር ። ግን ቃላት አጠሩት ። ምክሩ ሚዛን የሚያነሣ መስሎ አልታየውም ።

ከዓመታት በፊት አንድ ሰው ኪጋዜጣ ክርክሞ የላከለት ጽሑፍ ትዝ አለውና ከማስታወሻ ማኅደሩ መዝዞ አወጣው ። ባሏ በድንገት በሞት ስለተለያት አንዲት ሴት የሚያወሳ ታሪክ ነበር ። ለዚህች ወጣትም እስትንፋስ የሚዘራ ወቅታዊ ጽሑፍ መሆኑን ተገንዝቦ ከደብዳቤው ጋር አያይዞ ላከላት ።

ባለ ታሪኳ ጀኮብ ዎከር የምትባል ባልቴት ስትሆን፡የምትኖረውም ብቻዋን ጭር ባለችና ድንጋያማ

በሆነች ትንሽ ደሴት ላይ ነበር ። አንድ ቀንም ታሪኳን ለጋዜጠኞች እንዲህ በማለት አጫውታለች ።

«……የወጣትነት ዘመኔን ያሳለፍኩትና ሞት ከነጠቀኝ ባለቤቴ ጋር የተጋባነው ከዚህ ሩቅ ባለ ፣ በአንድ ጐኑ ከየብስ ጋር በተገናኘ ደሴት ላይ ነበር ። የባለቤቴም ሥራ በዚያ ደሴት ከፍተኛው ጉብታ ላይ የቆመና ማታ ማታ መርከቦችን ወደ ወደብ የሚመራ ባውዛ መቆጣጠር ነበር ። ያኔ እኔም ምግብ ከማብሰ ልና ልብስ ከማጠብ ሌላ አበቦችና የጓሮ አትክልቶች በመኰትኰት ጊዜዬን በደስታ አሳልፍ ነበር ።

«ታዲያ አንድ ቀን ባለቤቴ ወደዚህች ደሴት ተዛወረና ይዞኝ መጣ ። ገና ሳየው ቦታው ቀፈፈኝ ። ዙሪያዬን ስማትር ባሕሩ ተንጣልሎብኝ ሆዴን ባር ባር ስላለው ፣ ገና ከመድረሳችን ሻንጣዬን አንጠል ጥዬ ለመመለስ ሞክሬ ነበር ። ግን አልሆነልኝም ። እንደ ማልኖርበት ደጋግሜ ብዝትም ፣ ሚቼ ባለቤቴ በዚህም በዚያም እያባበለኝ አረሳሳኝ ።

«በዚህች ደሴት ላይ አራት ዓመት ያህል እንደ ቆየን ባለቤቴ ማማው ላይ ወጥቶ ባውዛውን ሲጠግን በብርድ በሽታ ተለከፈ ። ሕመሙ ወዲያውኑ ወደ ሳምባ ምችነት ተሸጋግሮበት ለሆስፒታል አልጋ ዳረገውና ለሕክምና ጥሎኝ ሔደ ። ሥራውን እኔው ሸፍኘለት ከረምኩ ። በአንድ ምሽት አንዲት ጀልባ ጨለማውን እየሰነጠቀች ወደ ጐጆዋችን ስትንኳተት ተመለከትኩ ። ይዛብኝ የመጣችው ዱብዳ ምን እንደ ሆነ መገመቱ አልተሳነኝም ።

«‘ እናዝናለን ፡ እመቤት ፡ ባለቤትሽ ጠንቶበ ታል’ አለኝ ከመጡት ሰዎች አንደኛው ራሱን ደፍቶ። ‘ሞቷል ማለትህ ነው?’ አልኩት እንባዬን እያጐረፍኩና ሲቃ እየተናነቀኝ ። መልስ አልሰጠኝም ።

«ይኸውላችሁ ፤ ባለቤቴን ከዚያ ማዶ ጉብታ ላይ አሳረፍነው ። በየቀኑ ማለዳ ላይ በመስኮት በኩል አንገቴን ብቅ እያደረግሁ መቃብሩን እቃኛለሁ ። አንዳንዴ አረንጓዴ ፡ አንዳንዴ ደግሞ ቡኒ ቀለም ፡ አንዳንዴ ደግሞ በረዶ ለብሶ አየዋለሁ ። ዘወትር የሚያስተጋባልኝም አንድ ቋሚ መልእክት አለው ። ይኸውም ባለቤቴ በሕይወት ሳለ ካጠገቤ ራቅ ባለ ቁጥር በጆሮዬ የሚያንቆረቁርልኝ ትእዛዝ ነው — ‘የመብራቱን ነገር አደራ!’ የሚል ። እኔም እስከዛሬ ያንኑ በመፈጸም ላይ እገኛለሁ ።»

ይህ ነበር የሚሲስ ጀኮብ ምክር ትግስታ ፣ በየምሽቱ እንደምታበራው ባውዛ በሕሊናዋ ፍዋ ብሎ የሚኖረው ትውስታዋ ። ፍቅረኛዋን ያጣችውን ያችን ወጣት ከሚያጠወልጋት የሕይወት ፈተና ያወጣታል ፡ መንፈሷንም እንደገና ሊያንሰራራላት ይችላል ብሎ በመገመት ጀምስ ጌልኪ የላከላት ጽሑፍ ይህ ነበር ።

መጠኑን ያለፈ ሐዘን ከእብደት ይቆጠራል ። ምክን ያቱም ሟች ላይገነዘብለት ቋሚ ራሱን ይጐዳልና ።

ዜኖፎን

☆ ☆ ☆

ሐዘንተኞች ብቸኞች አይደለንም ። የእኛን ጽዋ የሚ ቀምሱ ቤተሰቦች ሁሉ አባል መሆናችንን እንዘንጋ ። በመካከላቸው እንደምንገኝና እጆቻቸውንም ዘርግ ተው ከእቅፎቻቸው በማስገባት ሰቆታችንን ከልባ ቸው እንደሚካፈሉን እንገንዘብ ።

በሐዘን ጨለማ የተዋጠ ሰው ለብጤው የሚያካፍለው አጽናኝ እስትንፋስ አለው ። ከሕይወት ገፈት ተጐን ጭቷልና ከአንጀቱ የሚያመነጨው ምክሩ የሌላውን ውጋት ይቀንሳል ።

ወኔው በመሰለቡና የመኖርን ትርጉም በመሳቱ ሐዘ ንተኛ ሰው ራሱን ሽባና ባዶ አድርጐ ከሌሎች ዘንድ ለመጠጋት ይፈራ ይሆናል ። ታዲያ እንዲያ ያለ ሰው ምን ያህል ቢያዝን ፣ ሰቀቀኑ ምን ያህል ቢሰቅዘው ፣ ከእርሱ የበለጠ አይዞህ ባይ የሚሻና ከእርሱ የበለጠ የአለኝታነትን ጋሻ የሚፈልግ አንድ ሌላ ሰው ያጣል ማለት ዘበት ነው ።

ልባችንን በሐዘን እያደማን ጥቅጥቅ ደን ውስጥ ገብቶ መንገዱ እንደ ጠፋበት ተጓዥ የመንፈስ ክርታታ እንሁን ። ፍርሃት አቅጣጫችንን እንዳያስተን ፣ ትተ

ውን ለሐዱት ማንባቱን በልክ እናድርግ ። ቀናው መንገድም ይኸው ብቻ ነው ።......»

ሄለን ኬለር

☆ ☆ ☆

ሄንሪ ዎድስዎርዝ ሎንግፌሎ

«እናንተ ለቀስተኞች እባካችሁ ተዉኝ ፤
ሕይወትን ባዶ ሕልም አርጋችሁ አታውጉኝ»

ወቅቱ ማለዳ ነው ። ወጣቱ የሐርቫርድ ፕሮፌሰር ወደ ነበረበት ክፍል ብሩህ ፀሐይ በትንድ መስኮት በኩል ገብታ ትፍለቀለቃለች ። እርሱ በሌላ መስኮት አንገቱን ብቅ አድርጎ ቅጥረ ግቢውን እየ ቃኘ በብቸኝነት መንፈስ ተውጦ ይተክዛል ።

ሚስቱ በሞት ከተለየችው ሦስት ዓመታት አል ፈውታል ። ግን ዘወትር ትናፍቀዋለች ። የጊዜው ርዝመት ሐዘኑን ሊያረግብለት ወይም ትዝታዋ የሚ ቀሰቀስበትን ውጋት ሊቀንስለት አልቻለም ። ከመስ ኮቱ ዘወር አለና ኑሮውን እንዴት እንደሚገፋው ማሰላሰል ያዘ ።

ሄንሪ ዕውቅ ባለቅኔ ቢሆንም ፥ በእነዚያ ጨለማ ዓመታት ውስጥ ነገር ዓለሙን ረስቶታል ። እንደውም ለማንም ለምንም ቁቅሩ ደብዝዟል ። ሕይወት ትር ጉም አልባ ሆናበታለች ።

በብቸኝነት ተቆራምዶ የቆሰለ ስሜቱን ሲያስ ታምም እንዳልከረመ ሁሉ፡በአንዲት ዕለት «ሕይወት

ባዶ ሕልም አይደለችም!» የሚል ሐሳብ በድንገት ብልጭ ብሎለት ብዕሩን አነሣ ። ባለቅኔነቱ እንደ ገና ገነፈለለት ። ላወረደው ግጥምም ፣ «የሕይወት መዝሙር» የሚል ርዕስ ሰጠው ።

የሕይወት መዝሙር

እናንት ለቀስተኞች እባካችሁ ተዉኝ ፤
ሕይወትን ባዶ ሕልም አርጋችሁ አታውጉኝ ።
ለሚያንቀላፋ እንጂ እምታከትም ሕይወት ፣
ጭራሽ ሆኖ አያውቅም እንደምታስወሩት ።

ሕይወት ተጨባጭ ናት ፣ ያላት ጣፋጭ ጣዕም ፤
ከርሰ መቃብርም ከቶ አይወስናትም ።
«ሰው አፈር ነህና ግባ መሬት» ቢባል ፣
ተግባሩ አይቀበር ሲያስጠራው ይኖራል ።

መሣቅ ወይም ማልቀስ አይደለም ግባችን ፤
ያን ማብጠልጠል ብቻ አይሁን ዓላማችን ።
ተግቶ መሥራት ያሻል ወገብን ጠፍሮ ፣
ዛሬ ወደ ነገ እንዲለወጥ ሠምሮ ።

ዘመን ወራጅ ውኃ ፣ ጥበብ አቀበት ናት ፤
ልብም ትስፋን አዝሎ ይኖራል ሲዋትት ።
እንደ እርጥብ አታሞ እያለ ድም......ድም......
እስከ መቃብር አፍ ማውተርተሩ አይቀርም ።

በአውላላው መስክ ላይ በትግል ዓለም ውስጥ ፣
ሕይወት መጠጊያ አጥታ ድንገት ብትጋለጥ ፣

ከመንጋፈፍ ይልቅ ተለጉሞ እንደ ከብት ፣
መቋቋም ይበጃል ቆርጦ በጀግንነት ።

ምን አስደሳች ብትመስል ነገን ማመን ይቅር ፤
ትናንትም ከሟች ጋር ገብታለች መቃብር ።
በሚመስጥ ተግባር ያሻል ዛሬን ማጥመድ ፤
በልበ—ሙሉነት ቆሞ ለመራመድ ።

የታላላቅ ሰዎች ገድል እንደሚያሳየን ፤
እንሆናለን ሕያው እኛም በሥራችን ።
ኑሮን መግፋት ከቻልን አሻራ እያስቀመጥን ፤
ብንሞትም አልሞትንም ዘላለማዊ ነን ።

መድረሻ ያጣ ሰው አቅጣጫ ጠፍቶበት ፣
ትካዜ የዋጠው አስሮት ብቸኝነት ፣
የእኛን ዓርማ ሲያገኝ ምርኩዝ ያደርገዋል ፤
ጭንቀቱን ዋጥ አርጐ በድፍረት ይጓዛል ።

ስለዚህ አንቦዝን እንታጠቅ ቁምጣ ፤
ልበ—ሙሉ እንሁን የመጣው ቢመጣ ።
ውጤት በማስመዝገብ እንቁም ለተግባር ፤
በሥራ ተጠምደን መኖርን እንማር ።

ሎንግፌሎ ይህን ግጥሙን ለማንም ሳያሳይ ለረጅም ጊዜ ደብቆት ነበር ። ለምን እንዲያ እንዳደረገ ሲጠየቅም ምላሹ ፣ «ደርሶብኝ ከነበረው ጥልቅ ሐዘን ለመገላገል ስል ራሴው ለራሴው ከልቤ ያመነጨሁት የማጽናኛ እሪታዬ ስለሆነ ነው» የሚል

ነበር ። በኋላ ግን ፤ ኢሳትሞት በሚሊዮን በሚቆጠሩ ሰዎች እጅ እንዲገባ አድርጎታል ። ወደ ብዙ ቋንቋ ዎችም ተተርጉሚል ።

በተስፋቢስነት እንዳልሚሸሽ በሥራ መዋጥ አለብኝ ።

አልፍሬድ ቴኒስን

☆ ☆ ☆

ጉዞው አክትሞለት የተንጋለለ አካል ፤
ጥልቅት እንዳለው ወንዝ ሞገሱ ይከብዳል ።
በሰከነ እፎይታ—የዘለቄታ ዕረፍት ፤
ተቀዳጅቷልና ዘ....ላ....ለ....ማ....ዊ....ነ....ት!

ሳሙኤል ኮልረጅ

በሳል አባባልን ከቶ ማን ችል ይላል?
ሕሊናን ሰርስሮ ያስራል ፣ ያስደምማል ። ወይ ሠርዖ ወዳካል ከደም ተዋህዶ ሰውን ያስመስላል ጉርፍ ያስተኛው ሰርዶ ።

ፊሊፕ ጀምስ ባይሌ

156/2000

ዋጋው ብር 2.75